# በክርስቶስ የተገኘ ነጻነት

## ወደ ድል የሚወስደው መንገድ

ጽሑፍ:- በጁዲ ዌጅ

ትርጉም:- ፈቃዱ ገብሬ

እርማት:- ኃይሉ ልመንህና ሚናስ ብሩክ

Copyright

© 2004 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia.

Originally published in English under the title of
FREEDOM IN CHRIST: The Way to Victory.

© Copyright ECZ 2002. Christian Education Department,
EVANGELICAL CHURCH IN ZAMBIA
P.O.Box 23001, Kitwe, Zambia

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የፖ.ሣ.ቁ 127፣ አዲስ አበባ

# ማውጫ


ገጽ

I. ነጻነት ........................................................ 1
II. በክርስቶስ ........................................................ 7
III. አንዳንድ ልናምናቸው የሚገቡ ጠቃሚ ነገሮች ........................ 15
IV. በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መመላለስ ........................................ 21
ሀ. ሦስት ዓይነት ሰዎች ........................................................ 21
ለ. በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት እንዳልሆነ:-
1) ሕግጋትን መጠበቅ ወይም ሕግ አጥባቂነት አይደለም ............ 26
2) ኃጢአትን ለመሥራት ልቅ መሆን ማለት አይደለም................. 29
ሐ. በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ:- ..................... 30
1) ባሉበት መቆም ሳይሆን መንቀሳቀስ ነው ................................ 30
2) መሮጥ ሳይሆን መራመድ ነው ................................................ 31
3) ከኢየሱስ ጋር በአንድ ቀንበር ሥር ሆኖ መንቀሳቀስ ነው......... 31
4) የኢየሱስን ፈለግ ወይም ምሳሌ ተከትሎ መራመድ ነው ............ 33
5) የእምነት አካሄድ ነው ........................................................ 34
i) እምነት ምንድን ነው? ........................................................ 35
ii) ትክክል ያልሆነ አስተሳሰብ የእምነት ጠላት ነው ................ 39
iii) ጥርጣሬ የእምነት ታላቅ ጠላት ነው ................................... 44
ሀ. ጥርጣሬ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ጥያቄ ውስጥ እንድንገባ ያደርጋል ........................................................ 44
ለ. የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት መጠራጠር ወደ ጥፋተኝነት ወይም በደል ይመራል ....................... 46
V. በሥጋዊ ምኞት ላይ ድል ለመቀዳጀት የሚታለፉ ደረጃዎች ........... 51
VI. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ........................................................ 53
VII. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ .................................... 57
VIII. እውነተኛውን ነጻነት ስለ ማወቅ ........................................ 66
IX. የሚገዙንን ኃጢአቶች ለይተን ማወቅና መቋቋም እንዴት እንደምንችል ........................................................ 70
1. ባሕሎች (ወጎች) ........................................................ 72
2. መተት (ጥንቆላ)........................................................ 76
3. ከዘር የሚተላለፍ ውቃቢ፣ ሙታን መናፍስት፣ ማሟረት እርግማን........................................................ 79
4. ራስን ማሳት (ራስን ማታለል) ............................................. 83
5. ይቅርታ የማያደርግ መንፈስ (መራራ መሆን) ......................... 85
6. ዓመፅ ........................................................ 89
7. ትዕቢት ........................................................ 92
8. የልምድ ኃጢአቶች ........................................................ 93
X. አካሄዳችሁን በሚገባ አድርጉ፣ በነጻነት ጨርሱ ............................ 95
XI. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንድ፣ ጠላታችሁን፣ ወገናችሁንም እወቁ ........................................................ 98
XII. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለት፣ መጓዝ የሚገባንን ርቀት መጓዝ ........................................................ 100

# I. ነጻነት

ነጻነት ምንድን ነው? አንድ ሰው በባርነት ከኖረ በኋላ ጌታው የነበረበትን ባርነት አስወግዶ ቢለቅቀው፣ ያ ሰው ከባርነት እሥራት የተፈታና በነጻነት የሚኖር ይሆናል::

ለምሳሌ፣ ዛምቢያ ነጻነትዋን ከመቀዳጀቷ በፊት በእንግሊዝ አገዛዝ ሥር ነበረች:: በወቅቱ እንግሊዛውያን ዛምቢያን ይገዟት ነበር:: ሆኖም፣ ከ1964 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በኋላ የነጻነት ቀን ሲታወጅ አገሪቱ ከእንግሊዛውያን አገዛዝ ተላቅቃ ነፃ ሆነች:: አሁን የዛምቢያ ሕዝብ የሚኖረው በነጻነት ነው::

ከእግዚአብሔር ደኅንነትን ከማግኘቱ አስቀድሞ፣ ሰው ለሰይጣንና ለኃጢአት ባሪያ ሆኖ ይኖራል:: ሆኖም፣ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳ ኙ አድርጎ በሚቀበልበት ጊዜ ግን ከሰይጣን፣ ከኃጢአትና ከሞት ኃይል ነፃ ይወጣል:: ከዚህ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነጻነትን አግኝቷል ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነጻነት ያገኘ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት መሥርቷል ማለት ነው:: እግዚአብሔር አባቱ ይሆንለታል:: እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል:: ከኃጢአት ኃይልም ነፃ ይወጣል:: ስለሆነም ፍላጎቱ እግዚአብሔር አባቱን ማስደሰት ይሆናል::

*«ነጻነት በክርስቶስ»* በተሰኘ በዚህ መጽሐፍ የቀረቡ ትምህርቶች፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የእኛ ስለሆነው ነጻነት ግንዛቤ እንድናገኝ ይረዱናል:: ክርስቲያኖች ብንሆንም እንኳ፣ ብዙውን ጊዜ በሥጋዊ ነገሮች የታሠርን ያህል እንኖራለን:: በክርስቶስ ኢየሱስ ስላገኘነው ማንነት ስለማናውቅ ወይም ስለማንረዳ የምንኖረው ነፃ እንደ ወጡ ሰዎች ሳይሆን፣ እንደ ባሮች ነው::

ዮሐንስ 8:32፣ «እውነትን ታውቃላችሁ፣ እውነትም ነፃ ያወጣችኋል::» ሲል፣

ዮሐንስ 8:36 ደግሞ፣ «ስለዚህ ወልድ ነፃ ካወጣችሁ፣ በእርግጥ ነፃ ትሆናላችሁ::» ይላል::

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ጠቃሚ ጥቅሶች ናቸው:: በቃላችሁ ልታጠኑዋቸው ይገባል:: እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔር እውነት ከሰይጣን ውሸቶች ነፃ ሊያወጣን ኃይል እንዳለው ያረጋግጡልናል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን በተመለከተ ስላለው የእግዚአብሔርን እውነት ማወቃችን በጣም አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም በክርስቶስ ወደሚገኘው እውነተኛ ነጻነት የሚወስደንን መንገድ የምናገኘው እውነቱን በማወቃችን ነው::

በኤፌሶን 6:10-12 ጳውሎስ በጦርነት ውስጥ ስለ መገኘታችን ይነግረናል:: ይህ ጦርነት የምን ጦርነት ነው? ይህ ጦርነት ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ወይም ከመላእክቱ ጋር የሚደረግ ነው:: ይህ ጦርነት ከሰይጣንና ከርኩሳን የመናፍስት ኃይላትና ሠራዊት ጋር የሚደረግ ውጊያ ነው:: ይህ ጦርነት የተጀመረው አዳምና ሔዋን በኤድን ገነት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነበር (ዘፍጥረት 3:1):: በዚያን ወቅት ሰይጣን ሔዋንን አሳታት:: ሔዋንም ሰይጣንን በማመኗ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠራች:: ታዲያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን ሰዎችን ማሳቱን ቀጠለ:: በክርስቶስ የተቀዳጀውን ማንነት የማይገነዘብ ክርስቲያን በኃጢአት እንደሚጠመድና በእምነቱም ሊያድግ እንደማይችል ሰይጣን ያውቃል:: በክርስትና እምነታችን ማደግ ከፈለግን በክርስቶስ የተቀዳጀነውን ማንነታችንን ማወቅ ይገባናል:: በሰይጣን ላይ ድል መቀዳጀት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይኸው ነው::

## ክርስቲያኖች በእምነታቸው ለማደግና ድል አድራጊ ሕይወትን ለመኖር የሚቸግራቸው ለምንድን ነው? ለዚህ ምክንያቱ:-

1. አንዳንዶቹ በሰይጣን ስለሚታለሉ ነው (ራእይ 12:9):: ሰይጣን እኛ በክርስቶስ ያለንን ማንነት እንድንገነዘብ አይፈልግም:: እንደዚሁም በኢየሱስ በምናምንበት ወቅት የተከናወነውን እውነት እንድናውቅ ወይም እንድንረዳ አይፈልግም::

2. አንዳንዶቹ ሰነፎች ስለሆኑ እግዚአብሔርን በትክክል ለማወቅ ከልባቸው መንፈሳዊ ጥረትን አያደርጉም (ዳን. 11:32):: እግዚአብሔርን በእውነት የሚያውቁ ሰዎች ክፋውን ወይም ሰይጣንን መቃወም ይችላሉ::

3. አንዳንዶቹ የእግዚአብሔርን ኃይል ይጠራጠራሉ። ስለዚህ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ይልቅ ኃያል እንደ ሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ይህ ሐሰት ነው። የእግዚአብሐር ኃይል ከሰይጣን ኃይል ይልቅ የበለጠ ነው (1ኛ ዮሐ. 4:4)።

## እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ወቅት ምን ሁኔታዎች እንደ ነበሩ እንመልከት:-

ዘፍጥረት 1:27፤2:7 እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው አዳምን በራሱ አምሳል ፈጠረው። እግዚአብሔር ሰውን "በራሱ አምሳል" ፈጠረ ስንል ምን ማለታችን ነው? እንደዚህ ስንል፣ እግዚአብሔር ለአዳም እርሱን የሚያውቅበትን አእምሮ ሰጠው ማለታችን ነው። እርሱን መውደድ እንዲችልም ለአዳም ስሜቶችን ሰጥቶታል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን መታዘዝን መምረጥ እንዲችልም ለአዳም ፈቃድን ሰጠው። ከሰው ጋር ኅብረት ማድረግንና እርሱን መታዘዝንም ምርጫው እንዲያደርግ እግዚአብሔር ፈለገ።

እግዚአብሔር ለአዳም ትልቅ ስፍራ ወይም ሥልጣን ሰጠው (ዘፍጥረት 1:26)። መላዋን ምድር እንዲያስተዳድር ሥልጣን ሰጠው። ሰይጣን በመጀመሪያ በምድር ላይ ባለ በማንኛውም ነገር ላይ ሥልጣን አልነበረውም ነበር። ይህ ሥልጣን የአዳም ነበረ። በእግዚአብሔር ፊት አዳም ትልቅ ስፍራ ነበረው። ነገር ግን አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ይህን ትልቅ ሥልጣን አጣ። ከዚህ የተነሣ ሰይጣን «የዚህ ዓለም አምላክ» ሊሆን ቻለ (2ኛ ቆሮንቶስ 4:4)። ምን ጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔርን እውነት እንዳናውቅ ሰይጣን ዓይኖቻችንን ማሳወር ያስደስተዋል።

## ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ ምን ተከሠተ?

1. ዘፍጥረት 2:17 ሞት ወደ ዓለም ገባ:- ሰው በሥጋው ይሞት ጀመር። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረትም ስለ ተቋረጠ በመንፈስ ምውት ሆነ። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ዳግም ከገነት አውጥቶ ስለ አባረራቸው እንደገና ወደዚያ መመለስ አልቻሉም። በኃጢአታቸውም ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለዩ። *ኢሳይያስ 59:2* እኛ ሁላችን በኃጢአታችን ምክንያት

ከእግዚአብሔር እንደ ተለየን ይናገራል:: *ሮሜ 5:12* ደግሞ ሁላችንም ኃጢአትን ስለ ሠራን ሞት በሁላችንም ላይ እንደ መጣ ያስረዳል::

2. **ኤፌሶን 4:18 ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነውን እውቀት ጨለማ ዋጠው:-** አዳምና ሔዋን በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ነበራቸው:: እግዚአብሔርን ያውቁት ነበር:: ነገር ግን ኃጢአትን በመሥራታቸው ምክንያት ከገነት ተባረሩ:: ስለ እግዚአብሔር እውቀት የነበራቸው ቢሆንም፣ ከእርሱ ጋር ያደርጉት የነበረው ኅብረት ተቋርጦ ነበር:: በትክክል አያውቁትም ነበር:: ስለዚህ ከዚያ በኋላ የሚጓዙት በጨለማ ውስጥ ሆነ:: እኛም በኢየሱስ ከማመናችን በፊት በጨለማ ውስጥ እንጓዝ ነበር:: ከዚያ በፊት የነበረን ጥበብ የዚህ ዓለም እንጂ ከእግዚአብሔር የሚመጣው እውነተኛው ጥበብ አልነበረም::

3. **ዘፍጥረት 3:10 ፍርሃት፣ ጭንቀትና ኃፍረት ተከሰቱ:-** አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን መፍራት ጀመሩ:: ለእርሱ ስላልታዘዙ ከእርሱ ፊት ለመደበቅ ሞከሩ:: በእግዚአብሔር ፊት የተኰነኑ መሆናቸውን እየተረዱ ሄዱ:: እራቁታቸውን ስለሆኑም በኀፍረት ተሞሉ:: ከኃጢአታችን የተነሣ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት በተመሳሳይ መንገድ በደለኞች ነን:: እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚጠላ ቅዱስ አምላክ ስለሆነ፣ እርሱን መፍራታችን የተገባ ነው::

ይህን ሁሉ ስንገነዘብ መልሳችን ምን ይሆን? ጳውሎስ **በሮሜ 7:24** «እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» በማለት የተናገረው ቃል ብቻ ይሆናል:: ጳውሎስ ይህን ብቻ ብሎ አላበቃም:: በቁጥር 25 ላይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ወደ ደኅንነትና በኃጢአት ላይ ድልን ወደ መቀዳጀት የሚያደርሰውን መንገድ ማወቅ ስለምንችል እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ያሳስበናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውና በእግዚአብሔር ዘንድም ተቀባይነት ያገኘ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ሰይጣንን፣ ኃጢአትንና ሞትን ድል አድርጓል:: ስለዚህ የሰይጣንን ሥራ ለማፍረስና በኃጢአት ቀንበር የታሠሩትን ነፃ ለማውጣት ኢየሱስ

ኃይል ነበረው (ዕብራውያን 2:14፣ 15፤ 1ኛ ዮሐንስ 3:8)። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት፣ በክርስቶስ ሰይጣንንና ፈተናዎቹን ወይም ሽንገላዎችን ለማሸነፍ የሚያስፈልገን ሁሉ ተሰጥቶናል (2ኛ ጴጥ. 1:3-4)።

አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ስለ ሠሩ ሁላችንም የተቀባይነት፣ የዋስትናና ትኩረት የማግኘት ፍላጐት አድሮብናል። ይሁንና እኛ በራሳችን ጥረት እነዚህን ፍላጎቶች ማሟላት አንችልም። ያጣነውን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ኅብረት ራሳችን መልሰን ማግኘት አንችልም። የተፈረደብን ሆነናልና። ሆኖም፣ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን በምንቀበልበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሰይጣን ግዛት ውስጥ ያወጣናል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እኛን ከጨለማው ግዛት ታድጎ በማውጣት፣ የብርሃንና የኃይል መንግሥት ወደ ሆነው ግዛቱ አስገብቶናል (ቆላስይስ 1:13)። እኛ አሁን «በክርስቶስ ኢየሱስ» ነን። ኢየሱስ በእኛ ውስጥ ነው፤ እኛም በኢየሱስ ውስጥ ነን (ዮሐንስ 14:20)። እንደ አዳም ኃጢአተኞች ሆነን በመወለዳችን ያጣናቸው የተቀባይነት፣ የዋስትናና ትኩረት የማግኘት ሁኔታዎች በእግዚአብሔር ምሕረት ይመለሱልናል። ይህም የሚሆነው ኢየሱስ በቀራንዮ ላይ ከፈጸመው የተሟላ ሥራ የተነሣ ነው።

| አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከመሥራታቸው በፊት | በኃጢአት በተወለድን ጊዜ | በኢየሱስ ክርስቶስ ከሆንን በኋላ |
|---|---|---|
| 1. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ነበረን። | በኃጢአታችን የተፈረደብንና በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያጣን ነበርን። | ከፍርድ ነፃ ወጣን። ሮሜ 8:1 በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አገኘን። |
| 2. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትና ዋስትና ነበረን። | ከእግዚአብሔር የተለየንና ዋስትና ያጣን ሆንን። | ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅን። 2ኛ ቆሮ. 5:18። ዋስትና አገኘን። ዮሐንስ 10:27-29 |
| 3. ትኩረትን የማግኘት | ምንም ዓይነት ትኩረት | ትኩረትና ተፈላጊነት |

| | | |
|---|---|---|
| አቋም ነበረን:: | የማግኘት ወይም ተፈላጊነት አልነበረንም:: | አገኘን:: ኢሳይያስ 43:1፣4 |

# ጥያቄዎች

1. «ነጻነት» የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ አብራራ::
2. ዮሐንስ 8:32፣ 36ን በቃል ማጥናት ጠቃሚ ነው:: _______ በምናውቅበት ጊዜ፣ በክርስቶስ ያገኘነውን ነጻነት እንገነዘባለን::
3. ሀ) ክርስቲያኖች የሚዋጉት ጦርነት ምንድን ነው? ኤፌ. 6:10-12

   ለ) ይህ ጦርነት የተጀመረው መቼ ነበር? ዘፍጥረት 3:1

   ሐ) በዛሬው ዘመን ሰይጣን ክርስቲያኖችን ማሳቱን አቁሟል? ሊያስተን የሚፈልገው ለምንድን ነው?
4. ብዙ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ማደግና ድል አድራጊ ሕይወት መኖር የሚያዳግታቸው ለምንድን ነው?
5. እግዚአብሔር ሰውን «በአምሳሉ/በመልኩ» ፈጠረ (ዘፍጥረት 1:27) ስንል ምን ማለታችን ነው?
6. እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ወቅት የሰጠው አስፈላጊ ሥራና ሥልጣን ምን ነበር? ዘፍጥረት 1:26
7. አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ፣ ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ ሆነ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን ሊሠራ እየተጣጣረ ያለው ምንድን ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 4:4 ፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5:8
8. ኃጢአት ወደ ዓለም በገባ ጊዜ በሰው ሕይወት ላይ የደረሰው ምን ነበር?

   ሀ) ዘፍጥረት 2:17፤ ኢሳይያስ 59:2፤ ሮሜ 5:12

   ለ) ኤፌሶን 4:18

   ሐ) ዘፍጥረት 3:10
9. አዳም ኃጢአት ከማድረጉ በፊትና ካደረገ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ ምን አቋም እንደ ነበረው ግለጽ::
10. ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝህ በማድረግ ከመቀበልህ አስቀድሞ እንዴት ነበርክ?

    ለ) ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝህ አድርገህ ከተቀበልክ ወዲህ ደግሞ ሁኔታህ እንዴት ነው?

# II. «በክርስቶስ»

«በክርስቶስ» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ መቶ ያህል ጊዜ ተጠቅሷል:: ይህ ቃል የአዲስ ኪዳን ቁልፍ አሳብ ነው:: ክርስቶስ በአማኞች ሁሉ ውስጥ ሲሆን፣ ሁሉም አማኞች ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ ናቸው (ዮሐንስ 14:20)::

በተወለድንበት ዕለት ሥጋ ለብሰን ተወለድን:: ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን ስንቀበል፣ ዳግም በመወለድ ዘላለማዊው የሆነውን መንፈሳዊ ሕይወት እንቀበላለን:: ስለዚህ ዘላለማዊ ሕይወት የምንቀበለው ከሞትን በኋላ ሳይሆን፣ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን በተቀበልንበት በዚያን ወቅት ወዲያውኑ የዘላለም ሕይወት የእኛ ሆኗል:: «በክርስቶስ» የሆነ ማንኛውም ሰው አዲስ ተፈጥሮንና አዲስ ልብን ተቀብሏል:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው አሁን ቅዱስ፣ ከእግዚአብሔር በመንፈስ የተወለደ፣ የብርሃን ልጅና የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17፤ 1ኛ ጴጥ. 2:9)::

በእምነታችን የምናድግበት መንገድ እርሱ ስለሆነ በክርስቶስ የተሰጠንን ማንነት መገንዘብ ይገባናል:: የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ከተገነዘብን፣ ልጆቹ መሆናችንን የሚያረጋግጥ ሕይወት የመኖር ፍላጐት ይኖረናል:: ይህም ሕይወት የድል ሕይወት ይሆናል::

*መዘንጋት የሌለባችሁ ቁም ነገር:- ሰይጣን ከፍ ብለው የተገለጹትን እነዚህን ነገሮች እንድንገነዘብ አይፈልግም::* እርሱ በድል ሕይወት እንዳንኖር ያለማቋረጥ ሊያስተን ይጥራል:: በሽንፈት ሕይወት ውስጥ እንድንኖር ይፈልጋል:: እውነት ከእርሱ ኃይል ነፃ ስለሚያወጣን እውነትን እንድንገነዘብ አይፈልግም::

ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ ክርስቲያኖችን «ቅዱሳን» (2ኛ ቆሮንቶስ 1:1፤ ኤፌ. 1:1) በማለት ይጠራቸዋል:: እግዚአብሔር ቅዱሳን ብሎ የሚጠራን ስለ መልካም ሥራችን ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለን እምነት ነው:: ስለዚህ «በክርስቶስ» ያሉ ሁሉ ኃጢአተኞች ተብለው አይጠሩም:: በዚህ ምክንያት ራሳችንን ኃጢአተኞች አድርገን ካሰብን አኗኗራችንም እንደ ኃጢአተኞች ይሆናል:: እርግጥ ነው ክርስቲያኖች ኃጢአት ይሠራሉ፣ ይሁን እንጂ

እግዚአብሔር የሚመለከታቸው እንደ ቅዱሳን አድርጐ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን ኃጢአት እንደሚሠሩ ቅዱሳን አድርገን ከቆጠርን፣ እንደ ቅዱሳን የመኖር ፍላጎት ያድርብናል:: ቅዱሳን ስለ ሆንን፣ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች እንሆናለን:: ኢየሱስ በእግዚአብሔር ልጅነቱ ያለው ሁሉ፣ በክርስቶስ ስለ ሆንን የእኛም ነው ማለት ነው::

## 1. በክርስቶስ አማካይነት ተቀባይነት አግኝቼአለሁ (ምሳሌ 8:35)

ሁላችንም በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳለን ማወቅ እንፈልጋለን:: ሰዎች እኛን በእኛነታችን እንዲወዱንና እንዲቀበሉን እንሻለን:: ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ስለ እኛ ምን እንደሚያስቡ ማወቁ ቀላል አይደለም:: አንዳንዶች በደንብ ሲቀበሉን፣ ሌሎች ግን ላይወዱን ይችላሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ ምናልባት ትንሽ ልጆች በነበራችሁበት ጊዜ ወላጆቻችሁ በሚገባ አልተንከባከቡአችሁ ይሆናል:: አባቶቻችሁ ሁልጊዜ ሲቆጡአችሁና ዋጋ ቢሶች እንደ ሆናችሁ ሲነግሯችሁ ቆይተው ይሆናል:: ምናልባትም ፍቅር በማይለገሥበት በዘመድ ቤት ስላደጋችሁ የወላጆችን ፍቅር በፍጹም አታውቁ ይሆናል:: ምናልባት ባላችሁ (ወይም ሚስታችሁ) የማይወዷችሁ ወይም የማይቀበላችሁ (የማትወዳችሁ/ የማትቀበላችሁ) ሰው ልትሆኑ ትችላላችሁ:: ይሁን እንጂ፣ በዚህ በደረሰባችሁ ሁሉ በመጽናናት ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም::

**ኤፌሶን 1:4-5** ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን በተቀበልን ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንደ ገዛ ልጆቹ አድርጎ ተቀብሎናል:: ኃጢአተኞች የነበርን መሆናችንን ቢያውቅም፣ እግዚአብሔር ልጆቹ አድርጎናል:: እኛ እግዚአብሔርን እንዲወድደን ማድረግ አንችልም:: እግዚአብሔር እንዲወድደን ለማድረግ ልንሠራው የሚገባን ምንም ነገር የለም:: እርሱ እኛን በእኛነታችን እንዳለን ተቀብሎ ይወደናል:: እኛ ተወዳጅ ልጆቹ ሆነናል:: በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳለን ያለ ጥርጥር ልንረዳ እንችላለን:: ይሁን እንጂ፣ ሰይጣን እግዚአብሔር እንደማይወደን ሊያሳምነን ይጥራል:: ይህን በበለጠ የሚያደርገው በተለይ ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ ነው:: ይህንን የሰይጣንን ውሸት ላለመስማት አሻፈረኝ ማለት ይገባናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአት ብንሠራም እንኳ፣ ምንጊዜም የሚወድደን

በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይጠላል፣ እኛን ግን በዘላለማዊ ፍቅሩ ይወደናል (ኤርምያስ 31:3)::

ዮሐንስ 1:12፣13 እኔ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን ማወቄና ማመኔ ይህ ራሱ አስደናቂ እውነት ነው:: እግዚአብሔር ልጁ ተብዬ እንድጠራ ሥልጣን ሰጥቶኛል:: ስለዚህ ማንም ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ሊያወጣኝ ሥልጣን የለውም::

## 2. በክርስቶስ ደኅንነቴ የተጠበቀ ነው (ዮሐንስ 10:27፣28)

ማንም ሰው ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማወቅ ይፈልጋል:: ብዙ ሰዎች በቂ ገንዘብና ብዙ ወገን ካላቸው ወይም በሥራ ቦታ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ ካሉ ደኅንነታቸው ይመስላቸዋል:: እነዚህ ነገሮች ከጎደሉአቸው ልባቸው በጭንቀት ይሞላል:: ከዚህም የተነሣ ማጉረምረም ለመጀመር ቀላል ይሆንላቸዋል::

ክርስቲያኖች ልብ ሊያደርጉ የሚገባቸው በዚህ ዓለም ያሉ መልካም ነገሮች ዘላቂነት እንደሌላቸው ነው:: የእግዚአብሔር ነገሮች ግን ዘላለማዊ ናቸው:: እውነተኛው ደኅንነታችንና ዋስትናችን ያለው በክርስቶስ ውስጥ ነው (ምሳሌ 3:21-26):: የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በምናውቅበት ጊዜ የምንፈራው ነገር አይኖረንም:: በእኛ ያለው (መንፈስ ቅዱስ) በዓለም ካለው (ሰይጣን) እንደሚበልጥ እናውቃለን (1ኛ ዮሐ. 4:4):: ከእግዚአብሔር ስለ ተወለድን ክፉው (ሰይጣን) ሊነካን እንደማይችልም (1ኛ ዮሐ. 5:18) እናውቃለን::

## 3. በክርስቶስ ጠቃሚ የሆንኩ ሰው ነኝ (1ኛ ጴጥሮስ 2:9)

ማንኛውም ሰው ጠቃሚና ተፈላጊ መሆኑን ማወቅ ይሻል:: በርካታ ሰዎች በመንግሥት ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉልህ ሥልጣን ለመያዝ ይጥራሉ:: አንዳንዶች የዩኒቨርስቲ ትምህርትን መከታተል ቢችሉ በጥበብ እንደሚሞሉና እውቅና እንደሚያገኙ ያስባሉ::

ሆኖም ግን፣ እውነተኛው ጠቃሚ ወይም ተፈላጊ ሰው መሆን የሚመጣው በክርስቶስ በምናገኘው ማንነት ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 3:9፤ 4:1-2):: እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነን::

የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ነገሮች በአደራ የተሰጡን አገልጋዮቹ ነን:: ራሳችን ማድረግ ስለምንችለው ነገር መታበይና ማውራት አይገባንም:: ልንመካበት የሚገባ ነገር ቢኖር እኛ እግዚአብሔርን ማወቃችን፣ እንዲሁም እርሱ እያንዳንዳችንን ከእርሱ ጋር አብረን እንድንሠራ መጥራቱ ነው:: እግዚአብሔር የእርሱን ሥራ እንድንሠራ መርጦናል:: ያለ እግዚአብሔር ልንሠራ የምንችለው ምንም ነገር የለም (ዮሐ. 15:5):: ነገር ግን ኃይልን በሚሰጠን በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እንችላለን (ፊልጵስዩስ 4:13)::

እያንዳንዳችን ለእግዚአብሔር ጠቃሚዎች ነን:: ሁላችንም በክርስቶስ ተፈላጊዎች ነን:: እግዚአብሔር እንደሚወደን ስናምንና ለእርሱ ጠቃሚዎች መሆናችንን ስንገነዘብ፣ ድንቅ የሆነ የማንነት ግምትና የተፈላጊነት ስሜት እናገኛለን:: ይህ ግንዛቤ ድል አድራጊ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድንመራ ሊያበረታታን ይገባል::

## ስለ ሚከተሉት ነገሮች እናስብ:-

ሌሎች ሰዎች ጠቃሚዎችና ተፈላጊዎች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ መርዳት የሚገባ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን:: ወላጆች ልጆቻችሁን፣ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን እንወዳችኋለን ያላችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? ደግሞስ ለእግዚአብሔርም ለእኔም ጠቃሚ ነህ/ነሽ ያላችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? ብዙ ልጆች መወደዳቸውን ሳይሰሙ ያድጋሉ:: ወላጆቻቸው እነርሱን ለማጫወትና ለማበረታታት ጊዜ አይሰጡአቸውም:: ልጆቻችንን እንደምንወዳቸው እና ጠቃሚ ሰዎች እንደ ሆኑ አድርገን እንደምንቆጥራቸው ካወቁ እኛን የሚታዘዝና የሚያከብር ልብ ይኖራቸዋል:: ለልጆቻችን (ለሌሎችም እንዲሁ) እንደምንወዳቸው መንገር በጣም ጠቃሚ ነው::

ከዚህ በታች የሚቀርበው ትምህርት በክርስቶስ ስላገኘነው ማንነት ይናገራል:: ነጥቦቹ ሁሉ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ትምህርቱ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን በተቀበልንበት ጊዜ ምን እንደ ሆነ የሚገልጽ ነው:: እነዚህን ነገሮች በገንዘባችን ወይም በሥራችን ልናገኛቸው አንችልም::

የኢትዮጵያ ዜጋ እንደ ሆንንበት ዓይነት ሁኔታ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ተወለድን በዜግነታችን ኢትዮጵያውያን ነን:: የኢትዮጵያ ፓስፖርት ወይም የይለፍ መታወቂያ የመያዝ መብት አለን:: የሚወክለንን መንግሥት ለመምረጥ በምርጫዎች የመሳተፍ መብትም አለን:: እነዚህ የዜግነት መብቶቻችን ናቸው:: በሚቀጥለው ዝርዝር ውስጥ የተገለጹት በእግዚአብሔር ቤተሰብ በመወለዳችንና የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች በመሆናችን ከተቀዳጀናቸው መብቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው::

## በክርስቶስ የእኔ ማንነት

1. በክርስቶስ ተቀባይነት አግኝቼአለሁ- ምሳሌ 8:35

| | |
|---|---|
| ዮሐንስ 1:12 | - የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ |
| ዮሐንስ 15:15 | - የክርስቶስ ወዳጅ ነኝ |
| ሮሜ 5:1 | - ጸድቄአለሁ (ተቀባይነት አግኝቼአለሁ) |
| 1ኛ ቆሮንቶስ 6:17 | - ከጌታ ጋር ተባብሬአለሁ፣ በመንፈስም ከእርሱ ጋር አንድ ነኝ:: |
| 1ኛ ቆሮንቶስ 6:20 | - በዋጋ ተገዝቼአለሁ፣ የእግዚአብሔር ነኝ:: |
| 1ኛ ቆሮንቶስ 12:27 | - የክርስቶስ አካል ብልት ነኝ:: |
| ኤፌሶን 1:1 | - ቅዱስ ነኝ:: |
| ኤፌሶን 1:5 | - የእግዚአብሔር ልጅነትን አግኝቼአለሁ:: |
| ኤፌሶን 2:18 | - በመንፈስ ቅዱስ በኩል በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት እችላለሁ:: |
| ቆላስይስ 1:14 | - ጌታ ተቤዥቶኛል፣ ኃጢአቴም ሁሉ ይቅር ተብሎልኛል:: |
| ቆላስይስ 2:10 | - በክርስቶስ ሙሉ ነኝ:: |

2. በክርስቶስ የደኅንነት ዋስትና አለኝ

| | |
|---|---|
| ሮሜ 8:1-2 | - ለዘላለም ከኩነኔ ነፃ ወጥቻለሁ:: |

ሮሜ 8:28 - ሁሉም ነገር ለእኔ ለበጎ እንደሚሠራ እርግጠኛ ነኝ::

ሮሜ 8:33-34 - ከኩነኔ ክስ ሁሉ ነፃ ወጥቼአለሁ::

ሮሜ 8:35 - ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየኝ የለም::

2ኛ ቆሮንቶስ 1:21 - በእግዚአብሔር የተተከልሁ፣ የተቀባሁና የታተምሁ ነኝ::

ቆላስይስ 3:3 - በእግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ የተሰወርሁ ነኝ::

ፊልጵስዩስ 1:6 - እግዚአብሔር በእኔ ውስጥ የጀመረውን መልካም ሥራ ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርስ እተማመናለሁ::

ፊልጵስዩስ 3:20- የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ነኝ::

2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7 - የተሰጠኝ የፍርሃት መንፈስ ሳይሆን፣ የኃይል፣ የፍቅርና የበጎ ሕሊና ነው::

ዕብራውያን 4:16 - በችግር ወቅት ጸጋና ምሕረት ማግኘት እችላለሁ::

1ኛ ዮሐንስ 5:18 - ከእግዚአብሔር ስለ ተወለድሁ ሰይጣን ሊነካኝ አይችልም::

3. በክርስቶስ ጠቃሚ ሰው ነኝ - 1ኛ ጴጥሮስ 2:9

ማቴዎስ 5:13፣14 - የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን ነኝ::

ዮሐንስ 15:1፣5 - የእውነተኛው ግንድ ቅርንጫፍ የክርስቶስ ሕይወት መተላለፊያ ነኝ::

ዮሐንስ 15:16 - የተመረጥሁና ፍሬ ላፈራም የተሾምሁ ነኝ::

የሐዋርያት ሥራ 1:8 - የክርስቶስ የግል ምስክር ነኝ::

1ኛ ቆሮንቶስ 3:16 - የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነኝ::

2ኛ ቆሮንቶስ 5:17-20 - የእርቅ አገልጋይ ነኝ::

2ኛ ቆሮንቶስ 6:1 - ከእግዚአብሔር ጋር አብሬ የምሠራ ነኝ::
ኤፌሶን 2:6 - በሰማያዊ ስፍራ ከክርስቶስ ጋር ተቀምጫለሁ::
ኤፌሶን 2:10 - የእግዚአብሔር እጅ ሥራ ነኝ::
ኤፌሶን 3:12 - በነጻነትና በመተማመን ወደ እግዚአብሔር እቀርባለሁ::
ፊልጵስዩስ 4:13 - ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ::

«በክርስቶስ» ስለሆንን ከላይ በተዘረዘሩት ጥቅሶች ውስጥ የተነገሩት እውነቶች ሁሉ የእኛ ናቸው:: እነዚህን ጥቅሶች ደጋግማችሁ ብታነቡአቸው ይጠቅሟችኋል:: ከልባችሁና ከአእምሮአችሁ ጋር ይዋሐዱ ዘንድ በቃል አጥኗቸው::

እነዚህን እውነቶች በሚገባ ስናውቃቸውና ስንገነዘባቸው ልባችን ለታላቁ አምላካችን በሚኖረን ፍቅር ውዳሴና ምሥጋና ይሞላል:: የአዳም ልጆች ሆነን በተወለድን ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት መኖር እንችል ዘንድ ራሳችንን ለመርዳት ልናደርግ የምንችለው አንዳችም ነገር አልነበረም:: አሁን «በክርስቶስ ኢየሱስ» ከሆንን በኋላ ግን፣ እግዚአብሔር የራሱ ቤተሰብ አካል እንድንሆን አድርጎናል:: በክርስቶስ ባመንበት ሰዓት እግዚአብሔር አዲስ ስም ሰጥቶናል:: ከእንግዲህ ወዲያ ወላጅ አልባዎች አይደለንም:: የእግዚአብሔር የራሱ ልጆች ነን:: ከጌታችን ጋር ተባብረናል፣ ከእርሱም ጋር በመንፈስ አንድ ሆነናል::

**1ኛ ዮሐንስ 3:1-3** የአማኞች ሁሉ ታላቅ ተስፋ ምንድን ነው? እኛ ልጁን ኢየሱስን እየመሰልን ያለን የእግዚአብሔር ልጆች ነን:: ይህ ተስፋ ያላቸው ሰዎች የሚኖሩት እንዴት ነው? ራሳቸውን እያነጹ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ይኖራሉ::

ኃጢአትን እምቢ ማለት ይቻላል:: ሰይጣንን ተቃውሞ በድል መኖርም ይቻላል:: ይሁንና ሁልጊዜ ይህ ቀላል ባይሆንም፣ «በክርስቶስ» ግን ይቻላል::

«በክርስቶስ የእኔ ማንነት» የሚለውን ዝርዝር በየዕለቱ እንድታነቡ እናደፋፍራችኋለን:: በእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ የተካተቱትን

ታላላቅ እውነቶች አሰላስሉአቸው:: እነዚህ እውነቶች የሰይጣንን ውሸት አውቃችሁ ለክርስቶስ የከበረ ሕይወት እንድትኖሩ ይረዱአችኋል::

## ጥያቄዎች

1. «በክርስቶስ» የሚለው ፍሬ አሳብ ታላቁ የአዲስ ኪዳን አሳብ የሆነው ለምንድን ነው?
2. የሚከተሉት ጥቅሶች "በክርስቶስ" ስለ ተሰጠን ማንነት ምን ይነግሩናል? ጥቅሱንና ለእናንተም የሚሰጠውን ትርጉም ለማብራራት ሞክሩ::
   - ሀ) 2ኛ ቆሮንቶስ 5:17
   - ለ) ኤፌሶን 2:10
   - ሐ) 1ኛ ጴጥሮስ 2:9፣10
   - መ) 1ኛ ዮሐንስ 3:1:2
3. በክርስቶስ የተሰጠንን ማንነት ማወቃችን እንዴት ይረዳናል? (የሚቀጥለውን ከማንበባችሁ በፊት ይህን ነገር አሰላስሉ::)

   *በእምነታችን ለመጠንከር ከፈለግን በክርስቶስ ማን መሆናችንን ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው:: እግዚአብሔርንና ራሳችንን፣ ደግሞም በክርስቶስ ማን መሆናችንን ማወቅ ይገባናል:: ከዚያ በኋላ በእምነታችን ማደግ እንችላለን:: መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ስለ ተሰጠን ማንነት የሚነግረንን ካላወቅን ሰይጣንንና ኃጢአትን ለማሸነፍ አንችልም:: ለምሳሌ ያህል:-*

   - በክርስቶስ ኢየሱስ ድል የእኛ መሆኑን ካላወቅን (ሮሜ 8:37፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 2:14) የሰይጣንን ሽንገላ (ኤፌሶን 6:11) መቋቋም አንችልም::
   - በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእምነት እንደ ጸደቅንና በእግዚአብሔር ዘንድ ሰላም እንዳለን (ሮሜ 5:1) ካላወቅን በተስፋ ልንደሰትና በመከራም ልንታገሥ (ሮሜ 12:12) አንችልም::

3. እስቲ ዛሬ ስለ ሕይወታችሁ አስቡ:: የሚያስቸግሩአችሁ ምን ነገሮች አሉ? እውነትን ማወቅ በእነዚህ ችግሮች ውስጥ እንዴት ሊረዳችሁ ይችላል?
4. 1ኛ ዮሐንስ 3:1-3 አንብቡ:: ያላችሁ ተስፋ ምንድን ነው?
   - ሀ) ለዛሬ
   - ለ) ለዘላለም

## III. አንዳንድ ልናምናቸው የሚገቡ ጠቃሚ ነገሮች

ድል አድራጊ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት መኖር ከፈለግን፣ ልናምናቸው የሚገቡ አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮች አሉ። ስለዚህ ከሰይጣንና ከኃጢአት ቀንበር ነፃ የሚያወጣን የእግዚአብሔር እውነት መሆኑን አስታውሱ። በመሆኑም የሚከተሉትን ማመን ይገባናል:-

**1. ድነናል**

ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ ተቀብሎ ወደ ሕይወቱ ውስጥ ያላስገባ ሰው ሰይጣንና ኃጢአትን ሊያሸንፍ አይችልም። ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሰው በኃጢአት ስለሚኖርና ሰይጣንን ስለሚያገለግል ነው።

የደኅንነትን መንገድ ማወቅ ጠቃሚ ነው። ይህም ማለት:-

ሀ) ኃጢአታችንን መናዘዝ ወይም ንስሐ መግባት:- ንስሐ መግባት ማለት ኃጢአተኛ እንደ ሆንሁ፣ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ተፈረደብኝና በኃጢአቴም ሞት እንደሚገባኝ መቀበል ማለት ነው። ንስሐ የአስተሳሰብና (የአእምሮ) የዓላማ ለውጥ ነው። ከኃጢአት ዘወር ማለትና ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው (2ኛ ዜና 6:36-39)።

ለ) ማመን:- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፣ ለኃጢአታችን እንደ ሞተና የደኅንነት መንገድ እርሱ ብቻ እንደ ሆነ ማመን ነው (ዮሐንስ 3:16፤ የሐዋርያት ሥራ 4:12፤ 16:31)።

ሐ) ኢየሱስ ይቅር እንዲለን መጠየቅ:- ኢየሱስ ኃጢአታችንን ይቅር በማለት አዳኝና ጌታ ሆኖ ወደ ሕይወታችን እንዲገባ ማድረግ ነው (1ኛ ዮሐንስ 1:7፤ የሐዋርያት ሥራ 3:19)።

ኢየሱስን ወደ ሕይወታችን እንዲገባ፣ እርሱ በእኛ ውስጥ እንደ ሆነና በእርግጥ ያለ ምንም ጥርጥር ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት እንዳገኘን ሙሉ ማረጋገጫ አለን ማለት ነው። 1ኛ ዮሐንስ 5:11፣ 12፣ 13 አንብቡ።

## 2. ደኅንነታችንን ማጣት አንችልም

ሰይጣን «እናንተ እኮ መልካም ሰዎች አይደላችሁም:: ኃጢአት ሠርታችኋል:: እንዴት የእግዚአብሔር ልጆች ትሆናላችሁ?» በማለት እኛን መሸንገል ያስደስተዋል:: ደኅንነታችን እንደ ተወሰደብንና እግዚአብሔርም ከእንግዲህ ወዲያ እንደማይወድደን ሊያሳምነን ይፈልጋል:: የሰይጣንን ሽንገላ ካመንን እንሸነፋለን፣ መልካም ፍሬ ማፍራትም ያዳግተናል:: ጥርጣሬ ወደ ሽንፈት ይመራል:: የእግዚአብሔር እውነት ግን ነፃ ያወጣናል (ዮሐ. 8:32፣ 36):: ሰይጣን ደኅንነታችንን ማጣት እንደምንችል እንድናምን ይፈልጋል:: ምክንያቱም መጠራጠር ከጀመርን በክርስትና ሕይወታችን ድል አድራጊዎች እንደማንሆን ስለሚያውቅ ነው::

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ ማጤን በጣም ጠቃሚ ነው:: «ክርስቲያን ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ ደኅንነቱን ያጣል? ክርስቲያን ኃጢአት ሠርቶ እያለ ኃጢአቱን ሳይናዘዝ ቢሞት ደኅንነቱ እንደ ተጠበቀ ይሆናል? ወይ መንግሥተ ሰማይስ ሊገባ ይችላል?»*

ምድራዊ ቤተሰባችንን እንደ ምሳሌ እንውሰድ:: በተወለድኩ ጊዜ የአባቴን ስም ተቀበልሁ:: የአባቴ ቤተሰብ አንዱ አካል ሆንሁ:: ለሁልጊዜውም ልጁ ሆኜ እኖራለሁ:: አባቴ ቢያባርረኝ እንኳ ልጅ መሆኔ አይቀርም:: በስሙ መጠራቴም አያቆምም:: ወይም ባለመታዘዜ ብንኮራረፍም ልጁ መሆኔ ግን አይቀርም:: በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስወለድም ነገሩ ተመሳሳይ ነው:: በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግም በምወለድበት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ እሆናለሁ:: እግዚአብሔር ሰማያዊ አባቴ፣ እኔም የእርሱ ልጅ ነኝ (1ኛ ጴጥሮስ 1:18-19):: በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ችያለሁ:: ስሜን ላጣው አልችልም:: ሆኖም ግን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳላደርግ ሊከለክለኝ የሚችል አንድ ነገር አለ:: ኃጢአት ስሠራና እግዚአብሔርን ሳልታዘዝ ስቀር ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ልጅነቴ ባይፋቅም ከእርሱ ጋር ያለኝ ኅብረት ግን ይቋረጣል::

በእውነት ያምንንና ኢየሱስን እንደ አዳኛችን የተቀበልን ከሆነ፣ ደኅንነታችንን ልናጣ እንደማንችል ማመን አለብን:: በእውነት አምነን

ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚፈልግ አዲስ ልብ ይኖረናል:: አንድ ሰው ክርስቲያን ነኝ እያለ በኃጢአት መኖርን የማያቆም ከሆነ፣ ከመጀመሪያው በእውነት ያመነ ላይሆን ይችላል (1ኛ ዮሐንስ 3:6)::

የደኅንነት ነፃ ስጦታ ከሰጠን በኋላ መልሶ የሚወስድብን ምን ዓይነት እግዚአብሔር ይሆን? ደኅንነት እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ስጦታ ነው:: የዳነ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይገባል:: ክርስቲያን የሚያገኘው ሽልማት ግን በሠራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው:: ክርስቲያኖች ሁሉ በሕይወታቸው ስላደረጉት ምላሽ ለመስጠት በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ (2ኛ ቆሮንቶስ 5:10፤ ሮሜ 14:12):: ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖች ታላቅ ሽልማት ይቀበላሉ:: ሌሎች ደግሞ አነስተኛ ሽልማት ይቀበላሉ (1ኛ ቆሮንቶስ 3:13-15፤ ቁጥር 15ን በሚገባ አጢኑት):: በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም እንዳናፍር ታማኝ አገልጋዮች ልንሆን ይገባል:: ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔርን በሚገባ እንዳገለገልን በማወቅ በፊቱ በታላቅ ደስታ እንድንቆም መትጋት ይገባናል (1ኛ ዮሐንስ 2:28):: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እየመዘገበ ቢይዝ ኖሮ ማን በፊቱ ይቆማል? ነገር ግን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ በእርሱ ዘንድ ሁልጊዜ ይቅርታ አለ (መዝሙር 130:3፣ 4):: ስለዚህ እኛ አንዳንድ ጊዜ ኃጢአት የምናደርግ ቅዱሳን ነን:: *ይሁንና አንዴ ከዳንን ደኅንነታችንን ማንም ሊወስድብን እንደማይችል ይህ የእግዚአብሔር እውነት ነው::*

3. አሮጌው ተፈጥሮአችን ሞቷል:: ኃጢአት በእኛ ላይ ኃይል የለውም:: በሮሜ 6 ላይ ስለ አሮጌው ተፈጥሮአችንና «በክርስቶስ» ስለአገኘነው አዲሱ ተፈጥሮአችን ብዙ እንማራለን:: አሮጌው ተፈጥሮ ከአዳም የወረስነው ዓመፀኛና ኃጢአት ማድረግን የሚያፈቅር ተፈጥሮ ነው:: ከኃጢአትና ከሰይጣን ባርነት ሥር የሚያሳስሩን ክፉ ምኞቶቻችን ናቸው::

ሮሜ 6:6፣ 7 ደኅንነትን በተቀበልንበት ጊዜ አሮጌው ተፈጥሮአችን ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ ሞቷል:: በመሆኑም ከኃጢአት ኃይል ነፃ ወጥተናል:: የኢየሱስም ሕይወት የእኛ ሕይወት ሆነ (ገላትያ

**2:20)**:: የኃጢአት ባሪያዎች መሆናችን አበቃ:: ከኃጢአት ፍርድም ነፃ ወጣን (**ሮሜ 8:1**)::

*ይህ ማለት ከእንግዲህ ወዲያ ኃጢአት አንሠራም ማለት ነውን?* አይደለም! ኃጢአትና ሰይጣን አሁንም ሥራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው፣ ነገር ግን በእኛ ላይ አሁን ምንም ሥልጣን የላቸውም (ሮሜ 6:7፣14):: ከእንግዲህ ወዲያ የኃጢአት ባሪያዎች አይደለንም:: ለሰይጣንም የመታዘዝ ግዴታ የለብንም:: አሁን በእግዚአብሔር መንግሥትና በእግዚአብሔር ኃይል ውስጥ ነን:: ሰይጣንንና ኃጢአትን እምቢ ለማለት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለን::

*በቆላስይስ 3:3* ላይ ጳውሎስ፣ «ሞታችኋልና፣ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና» ይላል:: ደኅንነትን በተቀበልንበት ጊዜ አሮጌው ተፈጥሮአችን ሞቷል:: አሮጌው ተፈጥሮአችንን እኛ አልገደልነውም:: ይህንን ተግባር ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ፈጽሞታል:: ኢየሱስን እንደ አዳኛችን በተቀበልን ጊዜ ከዚያ አሮጌ ተፈጥሮ ተፈታን:: ስለሆነም አሁን በዚህ በአዲሱ ተፈጥሮ መመላለስን ለመምረጥ ነፃ ነን::

**ቆላስይስ 1:13** ከጨለማው ግዛት ተነጥቀን ወደ ብርሃን ግዛት እንደ ፈለስን በግልጽ ይናገራል:: ከሰይጣን ኃይል ነፃ ወጥተናል:: እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ማድረግን እንድንመርጥ እግዚአብሔር በመንፈሱ ጥበብንና ኃይልን ይሰጠናል:: እርሱ አሮጌውን ተፈጥሮአችንን ወደ አዲስ ተፈጥሮ ቀይሮልናል:: ነገር ግን የአሮጌው ተፈጥሮአችን ባሕርይ የሆኑትን ክፉ ነገሮች ላለማድረግ እምቢ ማለት ይገባናል (ቆላስይስ 3:5):: አንዳንድ ጊዜ ኃጢአትን ስንሠራ በአሮጌው ተፈጥሮአችን ወይም በሰይጣን ላይ እናመካኛለን:: ነገር ግን አሮጌው ተፈጥሮአችን ስለ ሞተና ሰይጣንም በእኛ ላይ ሥልጣን ስለሌለው እነዚህን ነጥቦች እንደ ማመካኛ መጠቀም አንችልም:: ኃጢአት ከሠራን የሠራነው በምርጫችን ነው::

አሮጌው ተፈጥሮ እንደ ሞተና ኃጢአት በእኛ ላይ ኃይል እንደሌለው ስናምን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ ለመርካትና ፈቃዱንም ለመፈጸም ነፃ እንሆናለን::

## 4. በክርስቶስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን ነን::

ሮሜ 6:5:11 ከኢየሱስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው አንድ ሆነናል:: ስለዚህ ከኃጢአት ኃይል ነጻ እንደ ሆንንና ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ እኛም በእርሱ ውስጥ እንደምንኖር ማመን አለብን:: ከጌታ ጋር ተባብረናል፣ በመንፈስም ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል (1ኛ ቆሮንቶስ 6:17):: ይህንን እውነት በምናምንበት ጊዜ፣ ኃጢአት በእኛ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ እንዳያደርግ በድፍረት እምቢ ማለት እንችላለን:: የድል ሕይወት ለመኖር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ እንተማመናለን:: የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች ነን፣ በመሆኑም የመንግሥተ ሰማይ ሀብት በሙሉ በክርስቶስ ኢየሱስ የእኛ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰይጣንን መቃወምና ኃጢአትንም አሻፈረኝ ማለት እንችላለን::

ሮሜ 6:12፣13፣17-22 ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ፈለሰ ሕዝብ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መስጠት ይገባናል:: ይህም ኃጢአትን እምቢ እንላለን ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ጸጋ ኃጢአትን «እምቢ» ማለት መማር አለብን (ቲቶ 2:11፣ 12):: የጽድቅ ሕይወት ለመኖርና ክፉውን እምቢ ለማለት እንምረጥ:: ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ ሁሉ እኛም ኃጢአትን መጥላት አለብን::

የሚከተሉትን ማመን ይገባናል:-

- ሮሜ 8:1 - በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም::
- ገላትያ 3:13 - ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን::
- ቆላስይስ 2:13 - በበደላችን ሙታን በነበርን ጊዜ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን::
- ቆላስይስ 1:22 - በክርስቶስ ሞት አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል:: በፊት ቅዱሳን፣ ያለነቀፋና ከክስም ነፃ ተደርገናል::
- መዝሙር 103:12 - ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ እንዲሁ ኃጢአታችንን አራቀ::
- ኢሳይያስ 43:25 - እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ «መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፣ ኃጢአትህንም አላስብም::»

እያንዳንዱን ዕለት እንዲህ ባለ ውሳኔ ልንጀምር ይገባል:: «ዛሬ የድል ሕይወት እኖራለሁ:: ሽንፈትን እምቢ እላለሁ::» ፈተና በሚመጣብኝ ጊዜ እንዲህ እላለሁ፣ «ኢየሱስ ጌታዬና አዳኜ ነው:: እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ:: በእርሱ ኃይል ውስጥም እኖራለሁ:: ስለዚህ፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ይህ የአንተ ቀን ነው:: በማደርገው በማንኛውም ነገር አንተን ማክበር እፈልጋለሁ:: በኃጢአት ላይ የአንተን ድል እቀዳጅ ዘንድ በዓይኖቼ በማየው፣ በአፌ በምናገረው፣ በማስበውና በማደርገው ነገር ሁሉ ውስጥ አንተ ሥራ:: እኔም በዚህ ሥራህ ፈተና በሚመጣብኝ ጊዜ፣ ራሴን ለእግዚአብሔር እሰጣለሁ፤ ድልም እንዲያቀዳጀኝ የእርሱን እርዳታ እሻለሁ:: ኃጢአት በእኔ ላይ ሥልጣን የለውም::

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
2. አንድ ሰው በእውነት ከዳነ፣ ደኅንነቱን የሚወስድበት ነገር ይኖራል? ሮሜ 8:35፣ 37-39፤ ዮሐንስ 10:27-29
3. ደኅንነትን በተቀበልን ጊዜ አሮጌው ተፈጥሮአችን ምን ሆነ? ሮሜ 6:6፣7፤ ገላትያ 2:20፤ ቆላስይስ 3:3
4. ሮሜ 6: 11 ምን ይለናል?
5. የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበባችሁ በኋላ ምን ማመን እንደሚገባን አብራሩ::

   ሀ) ሮሜ 8:1 ለ) ገላትያ 3:13 ሐ) ቆላስይስ 2:13

   መ) መዝሙር 103:12 ሠ) ኢሳይያስ 43:25
6. ቆላስይስ 1:13ን አንብቡ:: ከመዳናችን በፊት ከ -------- ሥልጣን ሥርና በ-------- ግዛት ውስጥ ነበርን:: አሁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችን ስለ ተቀበልን እግዚአብሔር እኛን ታድጎን ወደ ----- መንግሥት አፈለሰን::

| <u>ከደኅንነት በፊት</u> | <u>ከደኅንነት በኋላ</u> |
|---|---|
| - በጨለማ ውስጥ | - በብርሃን ውስጥ |
| - በኃጢአት ባርነት ውስጥ | - ከኃጢአት ኃይል ነፃ |
| - በሰይጣን ግዛትና ኃይል ውስጥ | - በእግዚአብሔር መንግሥትና ኃይል ውስጥ |

7. ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኙ ከመቀበሉ በፊት ከሁሉም የባሰ ኃጢአተኛ እንደ ነበረ አወቀ (1ኛ ጢሞቴዎስ 1:12-16)። ኢየሱስን እንደ አዳኙና እንደ ጌታው ባመነ ጊዜ የተለየ ሰው መሆኑንም ተገንዝቧል።

ሀ) ከመዳናችሁ በፊት ሕይወታችሁ እንዴት እንደ ነበረ አብራሩ።

ለ) ከዳናችሁበት ጊዜ ወዲህ የሕይወታችሁ ለውጥ እንዴት ነው? ኢየሱስን እየመሰላችሁ በመሄድ ላይ ናችሁን?

ሐ) በይበልጥ ኢየሱስን ለመምሰል ካላችሁ ምኞት አኳያ፣ በሕይወታችሁ ሊለወጡ ይገባቸዋል የምትሏቸው ምን ነገሮች ይታዩአችኋል?

## IV. በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መመላለስ

የተቀደሰ ሕይወት መኖር፣ በሥጋ፣ በኃጢአትና በሰይጣን ኃይል ላይ ድል አድራጊም መሆን ከፈለግን፣ በመንፈስ እንዴት መመላለስ እንደሚገባን (በመንፈስ መኖርን) መማር ይገባናል። በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል በምንመላለስበት ወቅት፣ የሥጋ ምኞቶቻችንን ማሸነፍ እንችላለን። ገላትያ 5:16-18 አንብቡ።

### ሀ) ሦስት ዓይነት ሰዎች

በ1ኛ ቆሮንቶስ 2:14-3:3 ባለው ክፍል ጳውሎስ ስለ ሦስት ዓይነት ሰዎች ይናገራል።

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 2:14 መንፈሳዊ ያልሆነ ወይም ተፈጥሮአዊው ሰው፡- ይህ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙ አድርጎ ፈጽሞ ያልተቀበለ በመሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ የለም። በኃጢአቱ ምክንያት የሞተ ነው። የሚመላለሰው ኃጢአታዊ ምኞቶቹን በመፈጸም ነው። የሰይጣንን መንገድ የሚከተልና በገላትያ 5:19-21 የተጠቀሱትን ኃጢአታዊ የሥጋ መንገዶችን ምርጫው



መንፈስ ቅዱስ

ያደረገ ሰው ነው:: የዚህ ሰው ማንነት በኤፌሶን 2:1-3 ላይም ተጠቅሷል::




2. **1ኛ ቆሮንቶስ 2:15፤ 3:1 መንፈሳዊ ሰው** - ይህ ሰው ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ሰው ነው:: እግዚአብሔርን ያውቃል:: በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለው:: መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ይኖራል፣ የጽድቅ ሕይወት እንዲኖርም ኃይል ይሰጠዋል:: በኃጢአታዊ ምኞቶቹ እየተመራ መኖርን ለማቆም የወሰነ ሰው ነው:: ምርጫው በመንፈስ መመላለስ ነው:: የተቀደሰ ሕይወት መኖር ስለሚፈልግ ራሱን የጽድቅ ባርያ አድርጎ የሰጠ ሰው ነው (ሮሜ 6:19፣22):: በመንፈስ ቅዱስም የተሞላ ነው (ኤፌሶን 5:18):: በማንኛውም የሕይወት ገጽታው ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ያስገዛል:: ከእግዚአብሔር የሚደብቀው ምንም ነገር የለውም:: ሕይወቱ *በገላትያ 5:22፣23* የተገለጹትን የመንፈስ ፍሬዎች ያንጸባርቃል:: በእምነቱ የሚያድግና እውነተኛውን ነጻነት በክርስቶስ የሚለማመድ ሰው ነው:: የዚህ ሰው ማንነት *በኤፌሶን 2:13፣ 19-22* ላይም ተገልጿል::

3. *1ኛ ቆሮንቶስ 3:1፣3 ዓለማዊው ሰው ወይም ሥጋዊው ሰው* - ጳውሎስ «በክርስቶስ» ነው ስለሚለው (3:1) ይህ ሰው ክርስቲያን እንደ ሆነ እናውቃለን:: አዲስ ሕይወት አለው፣ ነገር ግን «በክርስቶስ ሕፃን» ተብሎ ተጠርቷል:: በመንፈስ አይመላለስም:: ሁሉም ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ አላቸው (ሮሜ 8:9):: ነገር ግን ይህ ዓለማዊ ወይም ሥጋዊ ሰው በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላም:: ራሱን ሙሉ በሙሉ



ለእግዚአብሔር የሰጠ አይደለም:: ከታሠረባቸው ኃጢአቶች ገና ያልተላቀቀ ነው:: በመንፈስ ለመመላለስና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ለማፍራት ነፃ ምርጫ ቢኖረውም፣ ሥጋዊ ፍላጎቶቹን በመከተል ይቀጥላል::

በክርስቶስ የተሰጠውን እውነተኛ ነጻነት አያውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደርጋል:: ነገር ግን ሥጋዊ ምኞቶቹን በሚከተልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረቱ ይቋረጥበታል:: ከዚህም የተነሣ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን በረከት አያውቅም:: ይህ ሰው ክርስቲያን ነው:: ነገር ግን የሚኖረው እንደ ተረታ ክርስቲያን ሲሆን፣ በሕይወቱ ያለው ደስታና ሰላምም የተሟላ አይደለም::

ሕይወታችንን የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት ቤት አድርገን ልናስብ እንችላለን:: አንድ እንግዳ ወደ ቤታችን ሲመጣ ተጠርጐና ተወልውሎ በተዘጋጀውና ለማንኛውም ሰው አምሮ በሚታየው ሳሎን ውስጥ እናስተናግደዋለን:: ነገር ግን የመኝታና የሌሎች ክፍሎች መዝጊያዎቻችን ለእንግዶች ዝግ ናቸው:: በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የግላችን የሆኑ ነገሮች ስላሉ ሌሎች ሰዎች እንዲገቡና እንዲያዩዋቸው አንፈልግም::

መንፈስ ቅዱስንም የምናስተናግደው ይህንኑ በመሰለ አቀባበል ነው:: ደኅንነትን ባገኘንበት ወቅት በሕይወታችን ሳሎን ውስጥ ተቀብለን እናስተናግደዋለን:: ይህ ስፍራ ጽዱና መልካም ስለሆነ፣ እርሱ በዚህ ስፍራ በመስተናገዱ ደስተኞች ነን:: ግን ኃጢአቶቻችንን የደበቅንባቸውን የሕይወታችን ሌሎች ክፍሎች መዝጊያዎች እንዘጋለን::

አካሄዳችንን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እናደርግ ዘንድ እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍል ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት ልናደርግለት ይገባል:: ኃጢአታችንን ያመለክተን ዘንድ በመላው ሕይወታችን ውስጥ መግባት አለበት:: በጸሎት የምንጠይቀው ከሆነ ያሠሩንን ነገሮች ጥለን መውጣት እንድንችል ይረዳናል::




*ይህ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን በሳሎኑ ውስጥ የሚያስተናግድ ሲሆን፣ የሌሎች ክፍሎቹ በሮች ግን የተዘጉ ናቸው::*




*ይህ ክርስቲያን የሕይወቱን አንጻሮች በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ የከፈተ ነው:: በመንፈስ ቅዱስም የተሞላ ነው::*

*ከሥጋ ሥራዎች ተጽዕኖ የሚያሳድሩባችሁ ወይም የሚያጠምዷችሁ የትኞቹ ናቸው?*

ከሥጋ ወይም ከዓለም ኃጢአቶች አሁንም የሚፈትኗችሁና ነጻነታችሁን የሚወስዱባችሁ የትኞቹ ናቸው?

ሰይጣን እኛን ለማሳትና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሕይወታችን ውስጥ ለማበላሸት ሲል ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ይጠቀማል::

ለምሳሌ ያህል፣ አንዳንድ ሰዎች *ቁጣ* ያስቸግራቸዋል:: እነርሱ የማይወዱትን ነገር አንድ ሰው ካደረገ፣ በቁጣ ገንፍለው መናገር የማይገባቸውን ይናገራሉ:: ሌሎች ደግሞ *ውሸት* ይናገራሉ:: ውሸት መናገርም ማቆም የሚችሉ አይመስሉም:: አንዳንዶች ደግሞ ብርቱ የሆነ የገንዘብ ምኞት ስላላቸው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የማይገቡ ነገሮችን ያደርጋሉ:: ለምሳሌ፣ መጠጥ አስካሪና በሰዎች ላይ ችግርን የሚያስከትል መሆኑን ቢያውቁም እንኳ፣ *ገንዘብ ለማግኘት* ሲሉ መጠጥን ይነግዳሉ:: ሌሎች ደግሞ የጓደኞቻቸውን ንብረት በሚያዩበት ጊዜ *ቅናትና ምቀኝነት* ውስጣቸውን ያብሰለስለዋል:: ሌሎች ደግሞ እንዴት አድርገው አሳቦቻቸውን ለክርስቶስ ማስገዛት እንዳለባቸው

ስላልገባቸው *በክፉ አሳቦቻቸው* ብዙ ጊዜ ይሠቃያሉ:: ሌሎች እንደዚሁ የበደሉአቸውን ይቅር ለማለት *ፈቃደኞች አይደሉም:: ትዕቢትና ዓመፅ* የሚያስቸግራቸውም አሉ:: አንዳንዶቹ *ከወሲባዊ ርኩሰት ጋር* የማያቋርጥ ትግል ያካሂዳሉ:: የአንዳንዶቹ ችግር ደግሞ *የማያምኑ ዘመዶቻቸው* ናቸው:: ሌሎች ደግሞ በፍርሃት ካሠሩአቸውና እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙ ከሚያደርጓቸው *ባሕሎች* የመላቀቅ ችግር አለባቸው:: በርካታዎች በቃልቻ ፍርሃት ተይዘዋል ወይም በሕይወታቸው ለሚገጥሙአቸው ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት *ቃልቻዎችን* ወይም ከእነርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መንገዶች ይጠቀማሉ:: አንዳንዶች የዘር ውቃቢን፣ *የሙታን መናፍስትን፣ እርግማንን ይፈራሉ:: የኀሊና ወቀሳ* ብዙዎቹን ምርኮኛ አድርጎአቸዋል::

ስለ እነዚህ ጉዳዮች በጥናታችን በስተ መጨረሻ «የሚገዙንን *ኃጢአቶች* ለይተን ማወቅና መቋቋም እንዴት እንደምንችል» በሚል ርእስ *ሥር በክፍል IX* በጥልቀት እንመለከታቸዋለን:: አሁን ስለሚያጠምዱአችሁና ድል አድራጊ ሕይወት እንዳትኖሩ ስለሚያግዱአችሁ ነገሮች *ማሰላሰል ጀምሩ::* በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በክርስቶስ ያለውን ነጻነት እንደ ተገነዘበ ክርስቲያን መኖር እንዳትችሉ በሕይወታችሁ ውስጥ የሚያስቸግሯችሁን ነገሮች እንዲያሳያችሁ *መንፈስ ቅዱስን* ተማጠኑ::

*በ1ኛ ቆሮንቶስ 10:13* ከምንችለው በላይ እንድንፈተን እንደማይፈቅድ እግዚአብሔር የሰጠን የተስፋ *ቃል* አለ:: እንደዚሁም በሚደርስብን ማንኛውም *ፈተና* ድል የምናደርግበትን *መንገድ* እግዚአብሔር እንደሚያዘጋጅልንም ተስፋ ገብቶልናል:: እነዚህን ነገሮች ሁሉ ትተን በመንፈስ ለመመላለስ መምረጥ እንችላለን::

*በርካታ ክርስቲያኖች እንደ «ዓለማዊ ሰው» ይኖራሉ:: ለምን?*

- በክርስቶስ ማን እንደ ሆኑ አልገባቸውም፣ አልተገነዘቡምም::
- ሰይጣን እኛን እንዴት ለማሳሳት እንደሚጥር እውነቱን አላወቁም::

### *ለ. በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት እንዳልሆነ::*

## *1. በመንፈስ መመላለስ ሕግጋትን መጠበቅ ወይም ሕግ አጥባቂነት አይደለም::*

መንፈስ ቅዱስን የምንቀበለው በእምነት ኢየሱስ ክርስቶስን በመቀበል እንደ ሆነ *በገላትያ 3:1-5* ጳውሎስ ይናገራል:: ታዲያ ሕግጋትን ለመጠበቅ በምናደርገው ጥረት በመንፈስ መመላለስ እንችላለን? የገላትያ ሰዎች ሕግጋትን በመጠበቃቸው በመንፈስ የሚመላለሱ መስሏቸው ነበር:: ነገር ግን ጳውሎስ «እናንተ ሞኞች» ነበር ያላቸው:: «ማን አዚም አደረገባችሁ» በማለት ይጠይቃቸዋል:: የገላትያ ሰዎች እውነቱን ያውቁ ነበር:: ነገር ግን እውነቱን በሰይጣን ሽንገላ ተኩት:: በመሆኑም በመልካም ሥራዎቻቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት እንደሚችሉ አድርገው ማሰብ ጀመሩ::

*ገላትያ 3:23-26* እምነታችንን በክርስቶስ ላይ ከማድረጋችን በፊት፣ በሕግ እሥራት ውስጥ ነበርን:: ኃጢአታችንን ለእኛ በማሳየት ሕግ ደኅንነት እንደሚያስፈልገን ያመለክት ነበር:: ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣበት ብቸኛው መንገድ ሕግን ለመታዘዝ በመሞከር ነበር:: አንዱን ሕግ የማንታዘዝ ከሆንን በሁሉም የሕግ ተላላፊዎች እንደምንሆን *ያዕቆብ 2:10* ይናገራል:: ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕግጋት ታዝዞ የሚዘልቅ ማን አለ? ማንም የለም:: የእግዚአብሔር ሕግጋት ልንከተለው የሚገባንን ትክክለኛ የአኗኗር ሥርዓት ያሳዩናል:: ነገር ግን ሕግጋቱ ሊያድኑን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን ሊያደርጉ፣ ወይም በሰይጣን ላይ ድል እንድንቀዳጅ ሊያደርጉ አይችሉም:: ደኅንነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ እንደዚሁም በሰይጣን ላይ ድል መቀዳጀትን ልናገኝ የምንችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ በሚኖረን እምነት ብቻ ነው::

*ገላትያ 5:1* - በቀራኒዮ በመስቀል ላይ ኢየሱስ ከሕግ ቀንበር ነፃ አውጥቶናል:: በፈሪሳውያን በርካታ ሕጎች አይሁድ ታሥረው ነበር:: ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ሕጎች ላይ የራሳቸውን ብዙ ዓይነት ሕጎችን ጨምረውባቸዋል:: ታዲያ እነዚህን ሁሉ ሕጎች ማንም መጠበቅና መታዘዝ ስላልቻለ ሕጎቹ ለአይሁድ ሕዝብ ከባድ ሸክም ሆነውባቸው ነበር:: ሕጎችን መጠበቅ ይገባናል በሚል አሳብ የታሠርን

ከሆንን፣ ሕጎቹን ብንተላለፍ ምን እንሆናለን በሚል ፍርሃት ሕይወታችን ይሸማቀቃል። አንዱን ሕግ እንኳ ብንተላለፍ ይፈረድብናል። ነገር ግን *ሮሜ 8:1* «በክርስቶስ ላሉት» ኩነኔ እንደሌለባቸው ይናገራል።

*ገላትያ 5:4* - ሕግን በመታዘዝ ለመጽደቅ የምንሞክር ከሆነ፣ ከክርስቶስ እንደ ተነጠልንና ከእግዚአብሔር ጸጋም ተለይተን እንደ ወደቅን ጳውሎስ ይነግረናል። በክርስቶስ የሆንነውን ሁሉ የሆንነው ከእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት የተነሣ ነው። *ጸጋ ማለት ለማይገባው ኃጢአተኛ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ችሮታ ወይም ትሩፋት ነው።* እኛ ኃጢአተኞች ስለ ሆንን ከእግዚአብሔር ምንም መልካም ነገር ማግኘት አይገባንም። የሚገባን ሞት ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ግን የዘላለም ሕይወት ሰጥቶናል። *ኃጢአተኞች ስለ ኃጢአታቸው ሊቀበሉት ከሚገባቸው ቅጣት የሚያመልጡበት የእግዚአብሔር መንገድ ምሕረት ብቻ ነው።* እኛ በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ ነን። ስለሆነም ለእግዚአብሔር ሕግጋት የምንታዘዘው ፍርዱን ስለ ፈራን ወይም ስለ ተገደድን ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ስለምንወድደውና እርሱንም ለማስደሰት ስለምንፈልግ ነው።

*ገላትያ 5:18* - በእግዚአብሔር መንፈስ የምንመራ ከሆንን ከሕግ በታች አይደለንም። ይህም ማለት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር ነፃ ነን ማለት ነው። ደኅንነትን ስንቀበል አዲስ ልብ ተቀብለናል። ይህ አዲስ ልብ ደግሞ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይፈልጋል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት ስለምንፈልግ እንታዘዘዋለን። ከሕግ ነፃ የወጣን ነን። ሆኖም፣ *እግዚአብሔርን ስለምንወድድ ለእርሱ መታዘዝን እንመርጣለን።*

አንድ ሰው ብዙ ሕጎችን ለመጠበቅ ሊጥር ይችላል። ምናልባት «አልዋሽም፣ አልሰርቅም፣ አላመነዝርም፣ አላስጠነቁልም። በየሳምንቱ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ፣ እጸልያለሁ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አነብባለሁ።» ሊል ይችላል። ይህ ማለት በመንፈስ ይመላለሳል ወይም ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ኅብረት አለው ማለት አይደለም።

ፈሪሳውያን ብዙ ሕጎችን ይጠብቁ ነበር:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አልነበራቸውም:: ኢየሱስም እንዲህ ብሎአቸው ነበር፣ «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን... በውጭ አምረው የሚታዩ፣ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት፣ ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ» *(ማቴዎስ 23:27-28)::* በመንፈስ መመላለስ የእምነት እርምጃ መራመድ ነው፤ የኢየሱስን ዱካ መከተል ማለት ነው:: የእግዚአብሔርንም ዕቃ ጦር መልበስ ነው:: ስለ እነዚህ ነገሮች ወደ ፊት እንነጋገራለን:: ክርስቲያን በፍጹም በሕግ የታሠረ እንደ ሆነ አይሰማውም:: ክርስቲያን ነፃ ስለሆነ ይህ ነጻነቱ ደስታንና ሰላምን ያመጣለታል::

- *መልካም የሆነውን ለመምረጥ* ነፃ ነን::
- *የእግዚአብሔርን ፈቃድ* ለማወቅ ነፃ ነን::
- *የእግዚአብሔርን ፈቃድ* ለማድረግ ነፃ ነን::
- *መታዘዝን* ለመምረጥ ነፃ ነን::

በሕግ የታሠሩ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ይመስላቸዋል:: ነገር ግን በክርስትና ሕይወታቸው ውስጥ ያላቸው ደስታ በጣም ዝቅ ያለ ነው:: ትልቅ ሸክም እንደ ተሸከሙ ሆኖ ይሰማቸዋል:: ሕግ አክራሪነት ደግሞ ደስታችንን ያስወግደዋል:: እውነተኛ ደስታ ከሌለን ደግሞ እግዚአብሔርን ማምለክና መታዘዝ አስቸጋሪ ይሆንብናል:: እነርሱንም ሕግ አጥባቂዎች እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው፣ ደስታ የሌለው ክርስቲያን የሌሎች ክርስቲያኖችን ደስታ ይገፍፋል:: አንዳንድ ሰዎች የክርስትና ሕይወት ብዙ ሕጎች ስላሉት ከባድ ነው ይላሉ:: የክርስትና ሕይወታችን የተወሰኑ ሕግጋትን በመጠበቅ የሚገለጽ ከሆነ በእርግጥም ሸክም ይሆናል:: ነገር ግን ከሕግ ነፃ በምንሆንበት ጊዜ የክርስትና ሕይወት በደስታና በሰላም የተሞላ ይሆናል:: ልባችን በምስጋናና በውዳሴ ስለሚሞላ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ እንፈልጋለን *(ኢሳይያስ 32:17)::* ፈጣሪያችንንና የሚወድደንን ሉዓላዊ ጌታ የምናገለግልበት ስለሆነ የክርስትና ሕይወት መልካም ሕይወት ነው::

አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔር እንዲወድደኝ እርሱን እታዘዘዋለሁ» ይላሉ:: ይህ ውሸት ነው:: እግዚአብሔር እኛ ስለ ሠራነው መልካም ሥራ ብሎ አይወደንም:: ኃጢአትን ብንሠራም እንኳ ይወድደናል:: የእግዚአብሔር እውነት እንዲህ የሚለው ነው:-

እግዚአብሔር ይወድደኛል፤ ስለዚህም፣ እኔም እወደዋለሁ::
እግዚአብሔር ይወድደኛል፤ ስለዚህም፣ ልታዘዘው እፈልጋለሁ::

*ገላትያ 1:6* የእግዚአብሔር ወንጌል የጸጋ ወንጌል እንጂ ሕግን የመታዘዝ ወንጌል አይደለም:: ስለ እውነተኛው ወንጌል ጳውሎስ ምን ያህል አጠንክሮ እንደሚናገር ልብ በሉ:: የእግዚአብሔር ጸጋ ከእሥራት ይፈታናል:: *ሕግ አጥባቂነት ግን ያሥረናል::*

2) በመንፈስ መመላለስ ኃጢአትን ለመሥራት ልቅ መሆን ማለት አይደለም::

*ሮሜ 6:1-2፣ 15* አንዳንድ ሰዎች ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአት ብንሠራ ምንም አይደለም ይላሉ:: ጳውሎስ ይህ እውነት እንዳይደለ ያረጋግጣል:: ከጸጋ በታች ነን ማለት ኃጢአት ብናደርግ ምንም አይደለም ማለት አይደለም::

ጳውሎስ *በገላትያ 5:13* ላይ እንዲህ ይላል:: «ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፣ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይስጥ::»

ጴጥሮስም *በ1ኛ ጴጥሮስ 2:16* የሚከተለውን ይላል:: «አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባርያዎች ሁኑ እንጂ ያን አርነት ለክፋት መሸፈኛ አታድርጉ::»

ከሕግ ነፃ ብንሆንም፣ እንደ ገዛ ፈቃዳችን አንመላለስም:: በመንፈስ የሚመላለስ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የመኖር ፍላጎት ይኖረዋል:: እኛ የእግዚአብሔርን ሥራ በእግዚአብሔር መንገድ ለመሥራት የምንፈልግ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነን:: በየዕለቱ የምናከናውናቸው ምርጫዎች ይኖሩናል:: ይህም ነፃ ሆነን ለእግዚአብሔር መሥራት ወይም ለሥጋ ፍላጐት እሥረኞች ሆነን ሰይጣንን ማገልገል ነው *(ሮሜ 6:17፣18)::*

ምሳሌዎች:-

1. ከሕግ ነፃ ከሆንኩኝ፣ ከባንክ ገንዘብ መስረቅን መምረጥ እችላለሁ:: ሆኖም፣ ይህ የሚያስከትልብኝን ፍዳ አውቃለሁ:: ከባንክ ገንዘብ ብሰርቅ እሥር ቤት እንደምገባ እረዳለሁ:: ስለዚህ ምን ማድረግ ይኖርብኛል? ከባንክ ገንዘብ መስረቅን አለመምረጥ ብቻ ነው::

2. ከሕግ ነፃ መሆኔን ካወቅሁ በኋላ ማመንዘር እችላለሁ:: ነገር ግን፣ ሰውነቴ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑን ከተረዳሁ ምን ማድረግ ይኖርብኛል? ሰውነቴን የእግዚአብሔርን ክብር በሚያጎድፍ መንገድ አለመጠቀም ብቻ ነው:: በዚህ ፈንታ ሰውነቴን እግዚአብሔርን በሚያከብር መንገድ መጠቀምን እመርጣለሁ::

እነዚህን ትክክለኛ ምርጫዎች የምናደርገው፣ ማድረግ ስላለብን ሳይሆን፣ ይልቁኑም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ ስለምንፈልግ ነው::

ስለዚህ በመንፈስ የተሞላ አካሄድ፣ የነጻነት አካሄድ እንጂ የሕግ አጥባቂነት አካሄድ አይደለም:: የነጻነት አካሄድ ነው፣ ሆኖም የምንፈቅደውን ሁሉ የምንፈጽምበት ሁኔታ አይደለም::

## ሐ. በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ

*2ኛ ቆሮንቶስ 3:4-6፣17* ሕግጋትን ሁሉ ለመጠበቅ ጥረት እያደረገ የሚኖር ሰው በእነዚያ ሕጎች የታሠረ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ግን ሕይወትንና ነጻነትን ይሰጠናል:: እኛ እንደ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነውን ነጻነት ልናውቅ ይገባል:: በመንፈስ ለመመላለስም ሆነ በኃጢአት ምኞቶች እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ለመኖር መምረጡ የእኛው ፈንታ ነው:: በመንፈስ እንድንመላለስ እግዚአብሔር ከቶ አያስገድደንም:: ምርጫው የግላችን ነው::

⇒ 1. *ባሉበት መቆም ሳይሆን መንቀሳቀስ ነው::*

የሚቀመጥ ወይም ባለበት የሚቆም ክርስቲያን በእምነቱ የሚያድግ ስላይደለ በሰይጣን ላይ ድልን አይቀዳጅም:: በእምነታችን ማደግ ማለት ራስን መግዛትና *ሥራን መሥራት* ነው:: *ሥራ የማንሠራ* ከሆነ ብዙ ጊዜ የዚህ ምክንያቱ ስንፍናችን ነው:: ስንፍና እኛ እንዳናድግ ሰይጣን

የሚጠቀምበት መሣሪያው ነው:: *ምሳሌ 10:4፤ 13:4 እና ሮሜ 12:11 አንብብ::* «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ ለጌታ ተገዙ» (ሮሜ 12:11)::

⇒ *2. መሮጥ ሳይሆን መራመድ ነው::*

ለእግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ሥራ መሥራት ለእኛ ቀላል ነው:: ሆኖም፣ ይደክመናል፣ እንዝላለን:: አንዳንድ ጊዜ ለሥራ ወዲያና ወዲህ እንራወጣለን:: ይህንንም በማድረጋችን ይበልጥ መንፈሳዊ የምንሆን ይመስለናል:: ከእግዚአብሔር ፈቃድ ቀድመን መሮጥ የለብንም፣ ይልቁንም ተረጋግተን እርሱ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግብን ልናውቅ ይገባል:: ከዚያ በኋላ ግን ሥራውን በትጋት መንፈስ ልንሠራ ያስፈልጋል:: ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በሚገባ ሳንረዳ በአንድ ነገር ላይ በጥድፊያ ወደ ምርጫ ውስጥ እንገባለን:: ይህ ደግሞ ችግር ውስጥ ይከተናል:: በእግዚአብሔር ፈቃድና በእግዚአብሔር መንገድ በእርጋታና በጽናት መራመድ ግን ወደ ድል ይመራናል:: *ኤፌሶን 5:15-17 አንብቡ::*

⇒ 3. *ከኢየሱስ ጋር በአንድ ቀንበር ሥር ሆኖ መንቀሳቀስ ማለት ነው::*

*ማቴዎስ 11:28-30* በመንፈስ እንመላለሳለን ስንል ምን ማለታችን እንደ ሆነ በግሩም ሁኔታ የሚያሳየን ቃል ነው:: እያንዳንዱ ክርስቲያን ወደ እርሱ እንዲመጣና በእርሱ ቀንበር ውስጥ ተጠምዶ አብሮት እንዲሄድ ኢየሱስ ጥሪውን ያቀርባል:: የእርሱ ቀንበር ቀላል ቀንበር እንደ ሆነ ተናግሯል:: ብዙዎች ቀንበሮች አስቸጋሪዎች ናቸው:: ከመዳናችን በፊት፣ ከባድ በሆነው በኃጢአትና በክፉው የሰይጣን ቀንበር ሥር ነበርን *(ገላትያ 5:1)::* በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዶች ሕግጋትን በመፈጸም የጠበቀ ቀንበር ሥር ታሥረው ነበር:: እነርሱ ሕጉን ሊጠብቁ አልቻሉም:: ሕጉም እነርሱን ሊያድናቸው አልቻለም:: ነገር ግን *በማቴዎስ 11:30* ላይ ኢየሱስ «ቀንበሬ ልዝብ፣ ሸክሜም ቀሊል ነው» ይላል::

በአንድ ቀንበር ሥር ተጠምደው ስለሚራመዱ በሬዎች አስቡ::

- በቀንበሩ የተጠመዱት በሬዎች ስንት ናቸው? ሁለት ብቻ ናቸው::

- አንድ ብቻ ቢሆን ኖሮ በሚገባ ይሠራ ነበር? አይሠራም:: ሁለት ሲሆኑ ግን በመልካም ሁኔታ አብረው ይራመዳሉ::
- አንደኛው በሬ ቢሮጥና ሌላኛው በዝግታ ቢሄድ በደንብ አብረው ሊራመዱ ይችላሉ? አይችሉም፣ ምክንያቱም አንዱ ሌላውን ይጐትተዋል:: በተሳካ ሁኔታ በአንድነት ሊሠሩ የሚችሉት ተጠባብቀው አብረው የሚራመዱ ከሆነ ነው::
- በተቃራኒ አቅጣጫ ቢጓዙ ምን ይከሠታል? ምንም እርምጃ ሊያደርጉ አይችሉም:: ምክንያቱም አንዱ ሌላውን ይጐትተዋል:: ሁለቱ በተመሳሳይ እርምጃና በተመሳሳይ አቅጣጫ ሲጓዙ ብቻ በአንድነት በሚገባ መራመድ ይችላሉ::
- በሬውንና አህያውን በአንድ ቀንበር ሥር ልንጠምዳቸው እንችላለን? አንችልም! ምክንያቱም መጠናቸውም ሆነ ባሕርያቸው የተለያየ ነው:: በሬ ትልቅና የሥራ ፍላጐት ያለው እንስሳ ነው:: አህያ ግን አነስተኛና ልግመኛ እንስሳ ነው:: ስለዚህ ሁለቱ አንድ ቀንበር ሥር መጠመድ አይችሉም::

ከኢየሱስ ጋር በቀንበር ተጠምዶ የሚጓዝ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው::

- ኢየሱስ መሪ ስለሆነ ትክክለኛውን የአረማመድ ፍጥነትና ትክክለኛ ውን የጉዞ አቅጣጫ ያውቃል:: እኛ የሚጠበቅብን ዝም ብለን ከእርሱ ጋር መራመድ ብቻ ነው:: ነገር ግን እርሱ እየተራመደ እያለ ቀድመነው ለመሮጥ ወይም ቆጭ ብለን ለማረፍ መሞከር የለብንም::
- ከኢየሱስ ጋር የምንራመድ ከሆን የምንሠራው ሥራ ቀላል ይሆንልናል:: ነገር ግን ቀድመነው ከሮጥን ወይም ቆጭ ካልን ጉዞው አስቸጋሪና የማይመች ይሆንብናል::
- የኢየሱስ ቀንበር የባርነት ቀንበር አይደለም:: ከኢየሱስ ጋር አብረን ለመራመድ የምንመርጠው ቀንበር የነጻነት ቀንበር ነው (ገላ. 5፡1):: ከኢየሱስ ጋር አንድ የሆነ አስተሳሰብ እንዲኖረን እንመርጣለን:: ዓይኖቻችንን በኢየሱስ ላይ እናደርጋለን፣ እርሱም እንዴት መራመድ እንዳለብን ያሳየናል:: እርሱ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ፣ እንዴት መመላለስ እንዳለብን አስተምሮናል::

- የእግዚአብሔርን *ሥራ* እንዴት *መሥራት* እንዳለብን ከእኛ የሚጠበቀው ከኢየሱስ *ጋር መራመድን* ማወቅ ነው። በሰይጣንና በኃጢአት ላይ ድልን የሚያጎናጽፈን ይህ *መንገድ* ነው። ክርስቲያንና ኢየሱስ በአንድ ቀንበር *ሥር* ተጠምደው የሚጓዙበት እርምጃ የድል እርምጃ ነው።

*አንድ ልታስታውሱት የሚገባ ፍሬ ነገር፡-* ኢየሱስ ከእርሱ *ጋር* እንድንራመድ ፈጽሞ የማያስገድደን መሆኑን ነው። እያንዳንዳችን ከእርሱ *ጋር መራመድን* ምርጫችን እንድናደርግ ይጠበቅብናል።

*ማቴዎስ 11:29* ታላቅ ተስፋ ይሰጠናል። ከቀንበሩ *ሥር* ተጠምደን ከኢየሱስ *ጋር* አብረን በምንራመድበት ጊዜ እርሱ ለነፍሳችን ዕረፍት ይሰጠናል። ያኔ በጽድቅና በነጻነት እንደምንራመድ እንገነዘባለን። እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንሰማለን ደግሞም እናደርገዋለን።

⇒ 4. *የኢየሱስን ፈለግ ወይም ምሳሌ ተከትሎ መራመድ* ነው።

1ኛ ጴጥሮስ 2:21 ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ እኛን የገጠሙን ልምምዶች ሁሉ ገጥመውታል። ሆኖም፣ በፍጹም ኃጢአትን አላደረገም። እርሱ ምሳሌያችን ነው። እንዴት መራመድ እንደሚገባን ማወቅ ከፈለግን የኢየሱስን ፈለግ መከተል አለብን። የእርሱ ፈለግ ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ ይመራናል። ኢየሱስ *በዮሐንስ 10:27* ላይ፣ «በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፣ እኔም አውቃቸዋለሁ እነርሱም ይከተሉኛል» ይላል። የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመከተል የመምረጥ ነጻነት አለን። የኢየሱስንም ፈለግ ለመከተል ነጻነት አለን። ኢየሱስ በችግር ውስጥ የነበሩትን ሁሉ ረድቷቸዋል። ሁልጊዜም የተናገረው እውነትን ነው። እኛም የእርሱን ፈለግ መከተልና እርሱ የኖረውን ሕይወት መኖር አለብን።

*ሮሜ 8:14፣ ዮሐንስ 16:13* በመንፈስ መመላለስ ማለት በመንፈስ ቅዱስ መመራት ማለት ነው። አንድ እረኛ በጎቹን ወደ ትክክለኛ ስፍራ እንደሚመራ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም በእውነት መንገድ ይመራናል።

*በመንፈስ እየተመራን እንዳለን እንዴት እናውቃለን?*

ይህ ቀላል ነው:: ለዚህ ባሕርያችንን መመልከት በቂ ነው *(ማቴ. 7:16-20)::* በመንፈስ የምንራመድ ወይም የምንመላለስ ከሆንን፣ የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወታችን ውስጥ ይታያሉ *(ገላትያ 5:22-23)::* የኃጢአት ተፈጥሮአዊ ድርጊቶች የሚታዩብን ከሆነ፣ በመንፈስ እየተመላለስን አይደለንም *(ገላትያ 5:19-21)::*

*በተሳሳተ መንገድ ላይ እንደ ሆንን ከተገነዘብን፣ ምንድን ነው ማድረግ የሚገባን?*

በመጀመሪያ ደረጃ በተሳሳተ መንገድ ላይ እየተጓዝን እንደ ሆነ መቀበል አለብን:: ከዚያ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ችግሩን ለማረም መወሰን አለብን *(1ኛ ዮሐ. 1:9)::* ከዚያ እግዚአብሔርንና የበደልነውን ማንኛውንም ሰው ይቅርታ መጠየቅ አለብን *(ያዕቆብ 5:16)::*

> «በመንፈስ መመላለስ የነጻነት ጉዳይ ነው:: *ሥጋዊውን ወይም መንፈሳዊውን መንገድ ለመከተል ነፃ ምርጫ አላችሁ::* ነገር ግን ሰይጣን እናንተ ነፃ ስትሆኑ ደስ አይለውምና ተጠንቀቁ:: በክርስቶስ የተሰጣችሁን ነጻነት አውቃችሁ እንዳትደሰቱበት ለማደናቀፍ በሚችለው በማንኛውም ዓይነት የሽንገላ ጥበብ ለመጠቀም ይጥራል:: የእግዚአብሔርን ማንነትና መንገዶቹን ማወቅ አሳሳች የሆኑ መናፍስትን ለመለየት ይጠቅማችኋል:: በውስጣችሁ የሚሰማችሁ ትንሽ ድምፅ ስሜታዊ እርምጃ እንድትወስዱና በፈተና እንድትጠመዱ የሚገፋፋችሁ፣ ወይም ያለ ርኅራኄ የሚከሳችሁ ከሆነ፣ ይህ የእግዚአብሔር ድምፅ አይደለም:: ከኢየሱስ ጋር ይበልጥ አብራችሁ በተራመዳችሁና ይበልጥ እርሱን ባወቃችሁ መጠን፣ የሰይጣንን ሽንገላ ለመረዳትና ስልቱን ለማፈራረስ በሚገባ የተዘጋጃችሁ ትሆናላችሁ::»

⇒ 5. *የእምነት ሰካሄድ* ነው::

*2ኛ ቆሮንቶስ 5:7* «በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና::» ዕብራውያን 11:6 «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም::» በእምነት መራመድን መማር ይገባናል:: እግዚአብሔርን ማወቅና ስለ እርሱ ያወቅነውንና እርሱ

የሚያደርገውን ማመን ይገባናል:: ድልን የምንጎናጸፈው በእምነት ብቻ ነው::

*ቆላስይስ 2:6-7* ብርቱዎች እንድንሆን፣ በየዕለቱ በእምነት መራመድ አለብን:: ኢየሱስን የተቀበልነው በእምነት ነው:: ከኢየሱስም ጋር በየዕለቱ መራመድ ያለብን በእምነት ነው::

*1ኛ ዮሐ. 5:4፣5* ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን እንደ ሆነ ይናገራል:: ከእግዚአብሔር የተወለዱ ዓለምን ማሸነፍ ይችላሉ:: በክርስቶስ ያገኘነውን ማንነት በማመን ሰይጣንና ኃጢአትን ማሸነፍ እንችላለን::

*i) እምነት ምንድን ነው?*

*ዕብራውያን 11:1* «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው::» እምነት ማለት እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት ነው ብሎ መቀበል ነው:: እግዚአብሔር አንድን ነገር አደርጋለሁ ካለ ያደርገዋል ብለን እናምናለን:: ቀላል የሆነው የእምነት መግለጫ ይህ ነው:- *እግዚአብሔር ይናገራል፣ እኔም አምናለሁ::*

በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት በእምነት እንደ ዳንንና የእግዚአብሔር ልጆችም እንደ ሆንን ማመን ይገባናል:: ይህንን ካደረግን በአኗኗራችን እግዚአብሔርን እናከብራለን፣ ደስም እናሰኘዋለን:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ከኢየሱስ ጋር በምንራመድበት ጊዜ ይህ አኗኗራችን፤ ለሌሎች እምነታችንን ለመግለጽ ይረዳናል::

*ዮሐንስ 20:24-29* ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ፣ ቶማስ በኢየሱስ እጆችና እግሮች ላይ ያለውን የችንካር ምልክት ካላየሁ፣ በጦር የተወጋውንም የጐኑን ቁስል በእጄ ካልዳሰስኩ አላምንም ብሎ ነበር:: ኢየሱስ ቶማስን በተመለከተው ጊዜ ግን የነበረውን ጥርጥር ሁሉ አውቆ፣ «ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን» አለው *(ቁ. 27)::* ከዚያም ቀጠለና፤ «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» አለ:: *ሥጋዊ ዓይኖቻችን* ኢየሱስን አላዩትም:: ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ልናየውና ልናውቀው እንችላለን::

በየዕለቱ በእምነት እንራመዳለን:: ለምሳሌ፣ በወንበር ላይ በምንቀመጥበት ጊዜ ሁሉ ወንበሩ እንደሚሸከመን በማመን እንቀመጥበታለን:: በተመሳሳይ መንገድ እምነታችንን በእርሱ ላይ በመጣል እግዚአብሔርን እናምነዋለን::

የዚህ ዓለም ነገሮች ይለወጣሉ:: ለምሳሌ፣ ይሸከመኛል ብዬ ያመንኩት ወንበር ሊሰበር፣ እኔም ልወድቅ እችላለሁ:: ነገር ግን የእግዚአብሔር እውነቶች ከቶ አይለወጡም:: ስለዚህ በኢየሱስ ያለን እምነት ሊጠነክር ይችላል::

- ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው (ዕብራውያን 13:8):: እግዚአብሔር አይለወጥም (ሚልክያስ 3:6)::
- እግዚአብሔር ሊዋሽ ስለማይችል የሚናገረውን ማመን እንችላለን (ዘኍልቁ 23:19)::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ካወቅን፣ ራሱን እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን::

- እግዚአብሔር ሙሴንና የእስራኤልን ሕዝብ እንደ መራ ሁሉ፣ እኛንም ይመራናል::
- እግዚአብሔር ጳውሎስን በመከራው ሁሉ አበረታትቶታል:: በተመሳሳይ መንገድ፣ እግዚአብሔር እኛንም በመከራችንና በችግራችን ጊዜ ያበረታታናል::
- ከቤርሳቤህ ጋር ስለፈጸመው የዝሙት ኃጢአት ተጸጽቶ ንስሐ በገባ ጊዜ እግዚአብሔር ዳዊትን ይቅር ብሎታል:: እኛም እንደዚሁ ኃጢአቶቻችንን ከተናዘዝን፣ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል::
- እግዚአብሔርን ካላወቅን በእምነት መራመድ አንችልም:: ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ትንሽ ከሆነ፣ እምነታችንም ትንሽ ይሆናል:: ነገር ግን እግዚአብሔርን በሚገባ ካወቅን እምነታችን ያድጋል፣ ይጠነክራልም:: በእምነት ለማደግ እጅግ መልካም የሆነው መንገድ፣ እግዚአብሔርን በማወቅና በመረዳት ማደግ ነው *(ሮሜ 10:17፤ ዳንኤል 11:32)::* መጽሐፍ ቅዱስን ባነበብንና ቃሉን በቃላችን ባጠናን መጠን ስለ እግዚአብሔር የበለጠ እናውቃለን::

*በእምነት መራመዳችንን እንዴት ማወቅ እንችላለን?*

ያዕቆብ እምነታችንን የምናሳየው በሥራችን ነው ይለናል *(ያዕቆብ 2:17፣18፣26)*:: መልካም ሥራ የሌለበት እምነት ፈጽሞ እምነት አይደለም:: እምነትና መልካም ድርጊቶች አብረው ይሄዳሉ:: እምነት አለን ልንል እንችላለን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን ካልፈጸምን እምነት የለንም::

የሚከተሉትን ማመን አለብን:-

1. በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእምነት መራመድ እንችላለን::
2. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የኃጢአትንና የሰይጣንን ፈተናዎች እንቋቋማለን::
3. በክርስትና ሕይወታችን ማደግ እንችላለን::

አንዳንድ ጊዜ በእምነት አካሄዳችን ረገድ ውድቀት ያጋጥመናል:: በእግዚአብሔር መተማመንን እንዘነጋለን:: አንዳንድ ጊዜም ሰይጣን ያስተናል:: በተለይ በችግር ውስጥ በምንሆንባቸው አንዳንድ ጊዜያት እግዚአብሔር የረሳን ይመስለናል:: ከእንግዲህ፣ እግዚአብሔር እኛን አይወደንም ብለን ካሰብን ምን ሊሆን ይችላል? የዚያን ጊዜ ደኅንነታችንን እንጠራጠራለን፣ እምነታችንም መዳከም ይጀምራል:: ራሳችንን እንደ ዕድለ ቢሶች እናደርግና መቆዘም እንጀምራለን:: ይህ በእምነት መራመድ አይደለም:: ይህ መሸነፍ ነው:: በዚህ ጊዜ ለሰይጣን ደስታ ይሆናል:: እርሱ የእግዚአብሔርን በጎነት እንድንጠራጠር ማድረግ ይወዳል:: *ጥርጣሬ ታላቁ የእምነት ጠላት ነው::*

*ነገር ግን አንድ ነገር አስታውሱ:-* ምንም እንኳ በሕይወታችን ውስጥ ሁሉም ነገር የተበላሸና በችግር ውስጥ የገባ ቢመስልም፣ እግዚአብሔር እኛን ከመውደድ ፈጽሞ ወደ ኋላ አይልም:: የእግዚአብሔር ፍቅርም ፈጽሞ አይለወጥም:: በትክክል ስንራመድ ይወደናል:: በትክክል ሳንራመድም እንኳን እግዚአብሔር ይወደናል:: በእምነታችን አንድ ቀን ብንበረታ፣ በሌላ ቀን ደግሞ ብንደክም፣ እግዚአብሔር እኛን መውደዱን አያቆምም:: እግዚአብሔር በትክክል እንድንራመድ ይፈልጋል *(1ኛ ዮሐንስ 2:1)*:: ይሁን እንጂ፣ አንዳንዴ እንደምንዝልና እንደምንወድቅ ስለሚያውቅ ለእኛ ያለው ፍቅር ያው

ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድንጠራጠር ይፈልጋል። ነገር ግን በእኛ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሰይጣን ኃይል ይበልጣል *(1ኛ ዮሐንስ 4:4)።* ኢየሱስ ላለፈው፣ ለአሁኑና ለወደፊቱም ኃጢአታችን ሁሉ የሚቤዥን መሥዋዕት ሆኗል *(1ኛ ዮሐንስ 2:2)።* በእምነት በጽናት እንድንራመድ ይፈልጋል፣ ብንደናቀፍ ግን በፍቅር ወደ ራሱ ለመመለስ ሁልጊዜም ከአጠገባችን አይለይም።

አሳባችንን ለክርስቶስ ታዛዥ እንዲሆን ማድረግን መማር አለብን *(2ኛ ቆሮንቶስ 10:5)።* ፈተናዎችና ችግሮች በሚመጡበት ጊዜ እንዲህ በሉ (ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ብትሉት ይበልጥ ይረዳችኋል:-

*«እግዚአብሔር ይወደኛል። ይህንንም በእውነት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ሊለየኝ እንደማይችል ይነግረኛል። ከእግዚአብሔር እጅ ሊያወጣኝ የሚችል ምንም የለም። የማደርገው ወይም ማድረግ ያልቻልኩት ማንኛውም ነገር ቢሆን ከፍቅሩ ሊለየኝ አይችልም። እነዚህን እውነቶች በሙሉ ማመንን ምርጫዬ አድርጌአለሁ። እነዚህን እውነቶች ለማመን መርጫለሁ። ስለዚህ እግዚአብሔር እንደማይወደኝ አድርጐ ሰይጣን ሊያሳምነኝ የሚያቀርበውን ሁሉ ላለመቀበል አሻፈረኝ ብያለሁ።»*

በእምነት የሚከተሉትን እንቀበላለን:-

- የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን።
- እግዚአብሔር እንደሚወድደንና ከእርሱ ፍቅር ምንም ሊለየን እንደማይችል።
- እንደ ጸደቅን (ተቀባይነት እንዳገኘን)።
- ከጥፋት የተቤዠን መሆናችንና ለኃጢአታችንም ይቅርታ እንደ ተቀበልን።
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማንኛውንም ነገር መሥራት እንደምንችል።
- በእኛ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሰይጣን ኃይል ይልቅ ብርቱ ስለሆነ ሰይጣንን እንደምናሸንፍ።

*«በክርስቶስ የእኔ ማንነት»* የሚለውን እንደገና አንብቡ።

**ሁልጊዜ የእግዚአብሔር እውነት የሰይጣንን ውሸት ያሸንፋል።**

*ii. ትክክል ያልሆነ አስተሳሰብ የእምነት ጠላት ነው::*

*ማንኛውንም አሳብ ለክርስቶስ ለማስገዛትና ታዛዥም እንዲሆን ማድረግ የምትችሉበትን መንገድ ተማሩ:: ፍርሃት፣ ጥርጣሬና አለማመን እምነታችንን የሚያፈርሱ ናቸው::* ጦርነቱ ያለው በአስተሳሰባችን ውስጥ ነው:- መጥፎ አሳቦችን ማሰብ ስንጀምር፣ የእግዚአብሔርን እውነት መጠራጠር እንደምንጀምር ሰይጣን ያውቃል:: መጥፎ አሳቦች ወደ ኃጢአት ይመሩናል:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመላለስ ሰው መጥፎ አሳቦችን ይቃወማል:: የእግዚአብሔር ቃል እውነትን በመጠቀም ያሸንፋቸዋል:: አሳቦቻችንን ለክርስቶስ ትእዛዝ ማስገዛትን መማር አለብን:: *2ኛ ቆሮንቶስ 10:5* በጣም ጠቃሚ ጥቅስ ስለሆነ *በቃላችሁ አጥኑት::*

በክፉ አሳቦች ሲሠቃይ በነበረበትና በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን ለመተው በተፈተነ ጊዜ ዳዊት ምን እንዳደረገ እስቲ እንመልከት:-

*ሀ) መዝሙር 13*

- *ቁጥር 1-2* ዳዊት እንዲህ ብሎ እግዚአብሔርን ይጠይቃል፣ «አቤቱ፣ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ? እስከ መቼ ድረስ ነው ከአሳቤ ጋር የምሟገተው?»:: ዳዊት እግዚአብሔር የተወው መስሎት ነበር:: ከመጥፎ አሳቦች ጋር ትግል ገጥሞ ነበር:: ልቡም በኀዘን ተሞልቶ ነበር:: ነገር ግን በአሳቡ ውስጥ የሚመላለሰውን ለእግዚአብሔር ነገረ:: ምን እንደሚሰማን ለእግዚአብሔር መንገር መልካም ነው:: ምንም እንኳ እርሱ የሚያውቃቸው ቢሆንም፣ ስሜቶቻችንንና አሳቦቻችንን መንገሩ ይረዳል::
- *ቁጥር 5-6 ዳዊት፣ «እኔ ግን* በቸርነትህ *ታመንሁ፣* ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል::» ይላል:: በውስጡ ያሉትን መጥፎ አሳቦች *ይገነዘባል፣* ሆኖም እነዚያን አሳቦች አልቀበልም ይላል:: ከዚያ ይልቅ ስለ እግዚአብሔር ቸርነት ማሰብን *ይመርጣል::* ከዚህ በኋላ ምን ይሆናል? ትካዜው ወደ ደስታና ወደ ዝማሬ ይለወጣል::

*ለ) መዝሙር 55*

- ❖ *ቁጥር 1-8* እዚህም ዳዊት የሚሰማውን እንደገና ለእግዚአብሔር ይናገራል:: የገዛ አሳቦቹ እያስጨነቁት እንደ ሆነ ይናገራል:: የሥጋትና የመረበሽ ስሜት ተሰምቶታል:: «ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፣... ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ» ይላል:: ለመሸሽና ከችግሮቹ ሁሉ ለመሰወር ይፈልጋል:: የሚሻው ሰላምንና ዕረፍትን ነው::
- ❖ *ቁጥር 16-18* «ነገር ግን» የሚለውን ቃል እንደገና ልብ በሉ:: ዳዊት አሳቦቹን ለእግዚአብሔር ይናገራል:: ከዚያም እነዚህን አሳቦች ላለማስተናገድ ወስኖ አሳቡን ወደ እግዚአብሔር ቸርነት ይመልሳል::» «እጮሀማለሁ፣ ቃሌንም ይሰማኛል» ይላል:: ዳዊት የጸሎትን አስፈላጊነት አውቋል:: ምን ይሰማው እንደ ነበር ለእግዚአብሔር ይነግራል:: እግዚአብሔር እንደሚሰማውና በችግሮቹም ውስጥ እንደሚጠብቀው ይተማመናል:: በልቡ ውስጥ የሚሰማው ነውጥ በእግዚአብሔር የእንክብካቤ ዋስትና ወደ ተሞላ ሰላምና መረጋጋት ይለወጣል::
- ❖ ቁጥር 22 አስደናቂ ጥቅስ ነው:- «ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፣ እርሱም ይደግፍሃል፤ ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይሰጠውም»::

*አሳቦቻችን ለክርስቶስ እንዲገዙና ትእዛዛቱንም የሚፈጽሙ እንዲሆኑ ማድረግ እንዴት እንችላለን?*

1. መጥፎ አሳቦቻችንን *መገንዘብ::* የተሰማንንም ስሜት ለእግዚአብሔር መንገር::
2. ለእነዚህ መጥፎ አሳቦች *ስፍራ አለመስጠት*
3. ስለ እግዚአብሔር ቸርነት ማሰብን *መምረጥ::*

አምላካችን የፍቅር፣ የጸጋና የምሕረት አምላክ ነው:: ስለ እኛ ሁሉን ነገር ያውቃል:: እግዚአብሔር ምንም ስሕተት የማይሠራ ቅዱስ አምላክ ነው:: እርሱ አይለወጥም፤ ሊዋሽም አይችልም:: የሚናገረውን

ሁልጊዜም ያደርጋል:: የእግዚአብሔር ኃይል ከኃጢአትና ከሰይጣን ኃይል ይበልጣል:: ሰይጣንና ኃጢአት በእኛ ውስጥ እንዲሠሩ ካልፈቀድን በስተቀር በእኛ ላይ *ሥልጣን* የላቸውም *(1ኛ ዮሐንስ 5:18)::* በእርሱ የሚተማመኑትን እንደማይተዋቸው እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣቸዋል::

*ፊልጵስዩስ 4:8* «እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፤ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ...» አስቡ::

*ዕብራውያን 3:1* «ኢየሱስን አስቡ»፣ እንዲሁም *ዕብራውያን 4:14-16ን* አንብቡ::

መጽሐፍ ቅዱስ *ስለ እግዚአብሔር ቸርነት* በሚናገሩ ጥቅሶች የተሞላ ነው:: የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው:- *መዝሙር 31:19፤ 34:7-10፤ 84:11፣ 12፤ 103:1-5፤ 107:8፣ 9፤ ሮሜ 8:28-37::*

ስለ አምላካችን ቸርነት ማሰብን ተማሩ:: ይህም ሰይጣን በአሳቦቻችሁ ላይ የሚሠራውን ተንኮል ለማፈራረስ ይረዳችኋል::

ብዙ ጊዜ መጥፎ አሳቦች የሚመጡብን ስለምንፈራ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ *ፍርሃትም* ቢሆን የሚናገረው ብዙ ነገር አለው:: ይህን በተመለከተ የሚከተሉት ጥቂት ጥቅሶች ሊረዷችሁ ይችላሉ:-

*ዘዳግም 31:6፤ 2ኛ ዜና 20:15፤ ኢሳይያስ 35:4፤ 41:10፣ 13፤ 43:1-3፤ መዝሙር 23:4፤ 27:1-3፤ 34:7፤ 91:1-16::*

የሚከተሉት ዝርዝር ነጥቦች አሳቦቻችሁን ለክርስቶስ ማስገዛት እንድትማሩ የሚረዱአችሁ ናቸው:: *2ኛ ቆሮንቶስ 10:5...* «... *ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን::»*

| *እኔ:-* | *የማስታውሰው:-* |
|---|---|
| 1. አልችልም ብዬ በማስብበት ጊዜ | መጽሐፍ ቅዱስ ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ (ፊልጵ. 4:13) የሚለውን ነው:: |

| | |
|---|---|
| 2. አንድ ነገር እንደሚጎድለኝ ሳስብ | አምላኬ እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልገኝን ሁሉ እንደሚሞላብኝ የሚናገረውን ቃል ነው (ፊልጵ. 4:19):: |
| 3. በምፈራበት ጊዜ | እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ እንዳልሰጠኝ የሚናገረውን ቃል ነው (2ኛ ጢሞ. 1:7):: |
| 4. እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለማድረግ በቂ እምነት የለኝም ብዬ ሳስብ | እግዚአብሔር የተወሰነ የእምነት መጠን እንዳካፈለኝ የገለጸበትን ክፍል ነው (ሮሜ 12:3):: |
| 5. ደካማ ነኝ ብዬ ሳስብ | እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛ ዋ ነው የሚለውንና አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፣ ያደርጋሉም የሚለውን ቃል ነው (መዝ. 27:1፤ ዳን. 11:32):: |
| 6. ሰይጣን ሕይወቴን እንዲቆጣጠር እስከምፈቅድ ቢፈትነኝ | በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና (1ኛ ዮሐንስ 4:4) የሚለውን ቃል ነው:: |
| 7. ተሸንፌአለሁ ብዬ ሳስብ | በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ እንደሚያዞረኝ (2ኛ ቆሮ. 2:14) የሚናገረውን ቃል ነው:: |
| 8. ጥበብ ሲጎድለኝ | ክርስቶስ ለእኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ እንደ ሆነልኝና ሳይነቅፍ በልግሥና እግዚአብሔር እንደሚሰጠኝ የሚያረጋግጥልኝን ቃል ነው (1ኛ ቆሮ. 1:30፤ ያዕቆብ 1:5):: |

| | |
|---|---|
| 9. መንፈሴን ሲጫጫነኝና ሲከባብደኝ | «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና:: ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ታማኝነትህ ብዙ ነው::» (ሰቆቃወ ኤር. 3:21-23) የሚለውን ቃል ነው:: |
| 10. ጭንቀትና ውጥረት ሲመጣብኝ | ስለ እኔ በሚያስበው በእርሱ ላይ የሚያስጨንቀኝን ሁሉ እንድጥል የሚነግረኝን ቃል ነው (1ኛ ጴጥ. 5:7):: |
| 11. የታሠርሁ መስሎ ሲሰማኝ | የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ የሚለውን ቃል ነው፤ (2ኛ ቆሮ. 3:17፤ ገላትያ 5:1):: |
| 12. እንደ ተኰነንሁ ሲሰማኝ | በክርስቶስ ስለ ሆንኩ ኩነኔ እንደሌለብኝ የሚነግረኝን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው (ሮሜ 8:1):: |
| 13. ብቸኝነት ሲሰማኝ | ኢየሱስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ. 28:20) ያለውንና «አልለቅህም ከቶም አልተውህም» (ዕብ. 13:15) የሚለውን ቃል ነው:: |
| 14. የተረገምኩና መጥፎ ዕድል የተጸናወተኝ ሲመስለኝ | «ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላትያ 3:13-14):: ተብሎ የተጻፈውን ቃል ነው:: |
| 15. አለመርካት ሲሰማኝ | እኔም እንደ ጳውሎስ፣ «የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን |

| | |
|---|---|
| | ተምሬአለሁና» (ፊልጵ. 4:11) የሚለውን ቃል ነው:: |
| 16. ዋጋ ቢስ እንደ ሆንኩ ሲሰማኝ | «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮ. 5:21) ተብሎ የተጻፈውን ቃል ነው:: |
| 17. እየተሰደድኩ መሆኔ ሲሰማኝ | «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» (ሮሜ 8:31) የሚለውን ቃል ነው:: |
| 18. ግራ ሲገባኝ | እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንደ ሆነና (1ኛ ቆሮ. 14:33) በውስጤ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ እውቀትን እንደሚሰጠኝ (1ኛ ቆሮ. 2:12) የሚገልጽልኝን ቃል ነው:: |
| 19. ሽንፈት ሲሰማኝ | በክርስቶስ በሁሉም ነገር አሸናፊ እንደ ሆንሁ (ሮሜ 8:37) የሚገልጽልኝን ቃል ነው:: |
| 20. የኑሮ ውጣ ውረድ ሲያውከኝ | በዓለም ሳላችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ (ዮሐ. 16:33) የሚለውን ቃል ነው:: |

*III) ጥርጣሬ የእምነት ታላቅ ጠላት ነው::*

*ሀ) ጥርጣሬ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ጥያቄ ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል::*

ክርስቲያኖች ከሰይጣን ጋር በጦርነት ውስጥ ይገኛሉ:: በራሳችን ጉልበት ከተዋጋን እንሸነፋለን:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል ተማምነን ብንወጣ ሰይጣንንና ኃጢአትን እናሸንፋለን::

*አስተውሉ፡-*

*በዮሐንስ 15፡5* ኢየሱስ፣ «*ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም*» ብሏል፡፡

*ፊልጵስዩስ 4፡13* «*ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡*» የእግዚአብሔርን ኃይል የምናገኘው በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡

*ኃጢአትን የምንሠራበት አንዱ ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን ኃይል ስለምንጠራጠር ነው፡፡* በአፋችን የእግዚአብሔር ኃይል ከሰይጣን ይበልጣል ብለን እንነጋገራለን፡፡ በአኗኗራችን ግን የሰይጣን ኃይል እንደሚበልጥ አድርገን እንመላለሳለን፡፡

ስለ *እግዚአብሔር ኃይል* የሚናገሩ ከ100 በላይ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ *ታነብቡአቸው ዘንድ ጥቂቶች ከዚህ ቀጥሎ* ቀርበዋል፡- ዘጸአት 15፡6፤ 1ኛ ዜና 29፡11፣12፤ *መዝሙር* 62፡11፤ 147፡5፤ ኤር. 32፡17፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 10፡3፣4፤ ኤፌ. 1፡18-21፤ 3፡20፣21፤ 6፡10፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡7፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡5፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡4፤ 5፡18፡፡

ከመዳናችን አስቀድሞ በሰይጣን ግዛት ውስጥ ነበርን፡፡ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ስንሆን፣ በእግዚአብሔር *መንግሥት* ውስጥ ነን፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል አሁን ለእኛ አለን *(ቆላ. 1፡13)፡፡* ስለዚህ የእርሱን ኃይል እንያዝ፡፡

የእግዚአብሔርን ኃይል በምንጠራጠርበት ጊዜ፣ ሰይጣን በእኛ ውስጥ *እንዲሠራ ዕድል* እንሰጠዋለን፡፡ ከዚያ በኋላ በቀላሉ በአጉል ባሕል፣ በጥንቆላና በፍርሃት እንጠመዳለን፡፡ ከዚህ በኋላ በመጥፎ አሳቦች ስለምንጠመድ እንሸነፋለን፡፡

*እውነቱን ለማመን መቁረጥ ይገባናል፡፡ «ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮ ሁሉ...» እንደሚማረክ ማድረግ አለብን (2ኛ ቆሮ. 10፡5)፡፡*

ሰይጣን ኃይል ቢኖረውም «በክርስቶስ» ስላለን ልንፈራው አይገባም፡፡ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ደኅንነታችን የተጠበቀ ነው፡፡

በእግዚአብሔር ከታመንንና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከተመላለስን ሰይጣን ምንም ሊያደርገን አይችልም:: *ኤፌሶን 1:8-21 አንብቡ::*




አንዳንድ ሰዎች ስለ ጦርነቱ ያላቸው አስተሳሰብ:-
እግዚአብሔርና ሰይጣን ሁለት እኩል የሆኑ ኃያላን ናቸው::
ይህ ሐሰት ነው::




*የእግዚአብሔር ቃል እውነት:-*

*የእግዚአብሔር ኃይል (ሥልጣን) ከሰይጣን ኃይል ይበልጣል::*

*ለ) የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት መጠራጠር ወደ ጥፋተኝነት ወይም በደል ይመራል::*

የበደለኛነት ስሜት በኃጢአት ምክንያት የሚሰማ ኀፍረት ነው:: የበደለኛነት ስሜት ስለ ተሠራ በደል ወይም ጥፋት ኃላፊነትን

መውሰድን ያመለክታል:: አንድ ሰው የተከለከለን ነገር በሚያደርግበት ወይም ማድረግ የሚገባውን በማያደርግበት ጊዜ የሚኖር ሁኔታ ነው::

የበደለኛነት ስሜት በእውነት በተፈጸመ ተግባር ምክንያት ወይም በስሜት የሚከሰት ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው በቀጥታ ሕግን ቢጥስ፣ ሕጉን ስለ ጣሰ በቀጥታ ወንጀለኛ ወይም በደለኛ ይሆናል:: እንዲህ በመሰለው ሁኔታ አንድ ሰው የበደለኛነት ስሜት ቢሰማውም ባይሰማውም የተፈጸመ በደል አለ:: ይህን የበደለኛነት ስሜት በተመለከተ ክሱ ወይም ወቀሳው ከሰውየው ከራሱ፣ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከእግዚአብሔር ሊመጣ ይችላል:: ሕጉን የጣሰው ሰው ሕጉን በመተላለፍ በደለኛ ይሆናል::

እንደ ስሜት በሚከሠትበት ጊዜ የበደለኛነት ስሜት የሰውየውን ስሜታዊ ሁኔታ ያመለክታል:: አንድ ሰው በራሱ የመወገዝ ወይም ኃጢአተኛ የመሆን ስሜት ይሰማዋል:: ይህ ስሜት ተፈጸመ ከተባለው ድርጊት ጋር ጥቂት ወይም ምንም ግልጽ የሆነ ግንኙነት ላይኖረው ይችላል:: በሌላ አነጋገር አንድ ሰው በደለኛነቱን የሚጠቁም ምክንያት ወይም ማረጋገጫ ባይኖርም ጥፋተኝነት ሊሰማው ይችላል ማለት ነው::

ስሜት ብዙውን ጊዜ ትክክለኛ የጥፋተኝነት መግለጫ ነው:: መራራ ለቅሶን የሚያመለክተው *መዝሙር 51* የኃጢአትን ስሜት፣ የጸጸትንና የንስሐን ቃል የያዘ ነው:: *መዝሙር 38* ደግሞ የኃጢአትና የበደል ሸክም የተጫነው ሰው ምን ያህል እንደሚሠቃይ ያመለክታል:: በደል ሸክም ነው *(መዝሙር 38:4)*፣ ጭንቀትንም ያመጣል *(መዝሙር 38:18)*::

መፍትሔ ያልተገኘለት በደል ሰውን አቅመ-ቢስ ሊያደርግ ይችላል:: በደል በእምነታችን እንዳናድግ ሊያደርገን ይችላል:: ሊያሳስረንና በክርስቶስ ያለውን ነጻነት እንዳናውቅ ሊያደርግ ይችላል:: እኛ የበደለኛ ነት ስሜት እንዲሰማን በማድረጉ ሰይጣን ደስ ይለዋል::

የበደለኛነት ስሜት በሚሰማን ጊዜ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል:: ምክንያቱም እርሱ ይቅር ሊለን ቃል ገብቷል (1ኛ ዮሐንስ 1:9):: እርሱ ፈጽሞ ይቅርታ ያደርግልናል:: ኃጢአታችንንም ተመልሶ

አያስታውሰውም *(ኢሳይያስ 43:25)::* ለኃጢአቶቻችን ይቅርታ ስናገኝ በደላችንም ይወገዳል *(ኢሳይያስ 6:7)::* እኛም ከበደላችን ነፃ ስለምንሆን እግዚአብሔር አይፈርድብንም *(ሮሜ 8:1)::* ከዚያም በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን የለበስን ቅዱሳን አድርጎ እግዚአብሔር ይመለከተናል::

እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቀን ገና ከጥፋተኛነት ስሜት ጋር እየታገልን ከሆነ ጋየል ሮፐር ከዚህ በታች ያቀረባቸውን የመፍትሔ አሳቦች እንመልከት:-

1. አሁን ሰላም እየነሳችሁ ያለውንም ይሁን ሌላውንም ኃጢአታችሁን ክርስቶስ ይቅር ያላችሁ መሆኑን ለእግዚአብሔር አሳውቁ::

2. ባለማቋረጥ የሚሰማችሁ የበደለኛነት ስሜት የሚመጣው ከእርሱ ሳይሆን ከገዛ ራሳችሁ መሆኑን ለእግዚአብሔር አረጋግጡ::

3. በደላችሁን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ:: በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽ መሆን ያስፈልጋችኋል:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው መጥፎ ስድብ ሰድቤው እንደ ሆነ፣ ይህንን ሰው በመስደቤ ስላደረስኩት በደል እናዘዛለሁ ማለት ነው::

4. ቁም ነገረኛ (ሐቀኛ) ሰዎች ከሆናችሁ፣ የሚያስጨንቃችሁን በደል በወረቀት ላይ ጻፉና እንደ በደል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አቃጥሉት:: በሕሊናዊ ሥዕል የምታምኑ ከሆናችሁ ደግሞ፣ የበደል ሸክማችሁን አንሥታችሁ በኢየሱስ ክንድ ላይ አስቀምጣችሁ ስትሄዱ በዓይነ ሕሊናችሁ ተመልከቱ:: ፍሬ አሳቡ፣ በደላችሁን በትክክል ጠንካራ በሆነው በኢየሱስ ክንዶች ላይ ማስቀመጣችሁን እንድትገነዘቡት ነው::

5. የበደለኛነት ስሜት ተመልሶ በሚመጣባችሁ ጊዜ፣ እነዚህን የይቅርታ ቃላት አስታውሱ:- «አባት ሆይ፣ ይቅርታ አግኝቼአለሁ:: ስለዚህ ክርስቶስ አስቀድሞ ይቅርታ ያደረገልኝን

በደል ዳግም እንዳላስበው እርዳኝ::» አሁን የበደል ሸክማችሁን መልሳችሁ በክርስቶስ ክንዶች ላይ አኑሩት::

6. እውነቱን ማወቅ ብቻ የበደለኛነት ስሜቶቻችንን ወዲያው እንዲወገዱልን ሊያደርግ እንደማይችል ተረዱ:: ይህ የተደጋገመ ልምምድን ይጠይቃል:: «...መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው» (ዕብራውያን 5:14)::

*ጥያቄዎች - በመንፈስ ስለ መመላለሳችን:-*

1. ሀ) 1ኛ ቆሮ. 2:14ን እና ኤፌ. 2:1-3ን አንብቡ:: እነዚህ ጥቅሶች ማንን ይገልጻሉ?

   ለ) በ1ኛ ቆሮ. 2:15፤ 3:1 እና ኤፌ. 2:13፣ 19-22 የተገለጸው ማን ነው?

   ሐ) በ1ኛ ቆሮ. 3:1፣ 3 ላይ የተገለጸው ሦስተኛው ዓይነት ሰው ማን ነው? ይህ ሰው ክርስቲያን ነው ምክንያቱም ቁጥር 1 «በክርስቶስ ሕፃን» ብሎ ስለሚጠራው ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ሰው ምርጫው የሥጋ ነገሮችን መከተል ስለሆነ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሰው አይደለም::

   መ) ከእነዚህ ከሦስቱ ሰዎች መካከል እናንተ የትኞቹ ናችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችሁ ተቀብላችሁታልን?

   በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታችኋል?

   ወይስ አሁንም በሥጋ ነገሮች እንደ ታሠራችሁ ናችሁ?

2. ሀ) ከሥጋ ነገሮች ሊያስሩን የሚችሉት የትኞቹ ናቸው?

   ለ) አንተስ የታሠርህባቸው በየትኞቹ ነው?

3. በመንፈስ መመላለስ ሕግ አጥባቂነት (አክባሪነት) አለመሆኑን በምን እናውቃለን?

4. በመንፈስ መመላለስ ማለት የፈለግነውን የማድረግ ፈቃድ ማግኘት አይደለም:: ለምን?

5. በመንፈስ መመላለስ ምንድን ነው? 5 የተለያዩ አሳቦችን ግለጽ::

6. በመንፈስ መመላለስ በእርሱ ቀንበር ሥር ከኢየሱስ ጋር አብራችሁ እየተራመዳችሁ እንደ ሆናችሁ እንድታስቡ እንዴት ይረዳችኋል? የኢየሱስ ቀንበር እንዴት እንደ ሆነ ግለጹ::
7. በመንፈስ እየተመራን መሆናችንን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ማቴ. 7:17፣ 20፤ ገላ. 5:19-23
8. በመንፈስ አለመመላለሳችንን ከተረዳን ምን ማድረግ ይገባናል? 1ኛ ዮሐንስ 1:9፤ ያዕቆብ 5:16
9. ሀ) በመንፈስ መመላለስ በእምነት መመላለስ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 5:7፤ ዕብራውያን 11:1፣ 6
   ለ) ዓለምን ----------------- ስለሆነ እምነት ጠቃሚ ነው (1ኛ ዮሐንስ 5:4-5)::
10. ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው ነው (ዕብራውያን 13:8):: እግዚአብሔር ከቶ አይለወጥም (ሚልክያስ 3:6):: እግዚአብሔር ሊዋሽ አይችልም (ዘኁልቁ 23:19):: እነዚህን ጠቃሚ እውነቶች ማወቅና መገንዘብ ለምን አስፈለገ?
11. በእምነታችን ለማደግ ከፈለግን ምን ማድረግ ይገባናል? ሮሜ 10:17፤ ዳንኤል 11:32
12. ይህን ዓረፍተ ነገር አንብቡ:- እግዚአብሔር እምነታችን ጠንካራ ሲሆን ይወደናል፤ ነገር ግን እምነታችን ሲዳከምና ኃጢአት ስንሠራ እኛን መውደዱን ይተዋል:- ይህ እውነት ነው ወይስ ሐሰት? ሮሜ 8:35-39፤ ኤርምያስ 31:3፤ 1ኛ ዮሐንስ 2:1፣ 2

    *በጽድቅ እየተመላለስንም ይሁን ኃጢአት ብንሠራም፣ እግዚአብሔር እንደሚወድደን ማስተዋሉ በጣም ጠቃሚ ነው:: ኃጢአት ሠርተን ከሆነ፣ እግዚአብሔር የሠራነውን ኃጢአት አይወድድም፤ ነገር ግን ኃጢአተኛውን ሁልጊዜ ይወድዳል::*

13. አሳባችሁን ለክርስቶስ ታዛዥ እንዲሆን የምታደርጉት እንዴት ነው?
14. ጥርጣሬ የእምነት ጠላት የሆነው በምን ምክንያት ነው?
15. ከበደለኛነት ስሜት ጋር በምንተናነቅበት ጊዜ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

## V. በሥጋ ላይ ድል ለመቀዳጀት የሚታለፉ ደረጃዎች

በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ፈተናን፣ ኃጢአትንና ሰይጣንን ስለ ማሸነፍ ተነጋግረናል:: ሰይጣን እንዴት ውሸታምና አታላይ እንደ ሆነ ተመልክተናል:: የእግዚአብሔርን እውነት እንዳናውቅ ይጥራል:: ሰይጣን የእግዚአብሔርን መልካምነትና ኃይል እንድንጠራጠር የሚገፋፉ መጥፎ አሳቦችን በአእምሮአችን ውስጥ ያደርጋል:: ፍርሃትን እንደ መሣሪያ በመጠቀም እኛን ከእምነታችን ያርቀናል:: በምናያቸው ነገሮች አማካይነት ይፈትነናል:: በሌሎች ሰዎችም ተጠቅሞ ሊፈትነን ይችላል::

*ፈተናን እንዴት መቋቋም እንችላለን?*

ማስታወስ ያለባችሁ በፈተና ላይ ድልን ማግኘት የሚቻል መሆኑን ነው *(1ኛ ቆሮ. 10:13)::* ሰይጣንን በራሳችን ጉልበት ልናሸንፈው አንችልም:: ነገር ግን በእኛ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ኃይል ማሸነፍ እንችላለን *(1ኛ ዮሐንስ 4:4)::*

እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል» *(ያዕቆብ 4:7)::*

*ሀ) ለእግዚአብሔር ተገዙ*

i. በመንፈስ ቅዱስ በመመላለስ (ኤፌሶን 5:16):: (ክፍል IV ተመልከቱ::)

ii. በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት (ኤፌሶን 5:18):: (ክፍል VI ተመልከቱ::)

*ለ) ሰይጣንን ተቃወሙት*

i) የእግዚአብሔርን *ዕቃ* ጦር ልበሱ *(ኤፌ. 6:10-17)::* (ይህንን በክፍል VII ውስጥ በዝርዝር እንመለከተዋለን::)

ii) ክፉ አሳቦችን ፈቅዳችሁ አለመቀበልንና በእርሱ ፈንታ አሳቦቻችሁን ለክርስቶስ ማስገዛትን ተማሩ *(2ኛ ቆሮንቶስ 10:5)::* ስለዚህ ጉዳይ አስቀድመን በክፍል IV ሐ) ii. ላይ ተነጋግረናል::

iii) ጸልዩ *(ኤፌሶን 6:18)::* ስለ ጸሎት ኃይል ብዙ ብንናገርም ማጋነን አይሆንም (ክፍል Vii ተመልከቱ::)

ኃጢአትና ሰይጣን እኛን የሚቆጣጠሩበት ምክንያት ሊኖር አይገባም:: *ሰይጣንንና ኃጢአትን እምቢ የማለት መብት አለን:: የጽድቅ መሣሪያዎች አድርገን ራሳችንን ለእግዚአብሔር የመስጠት ምርጫ ማድረግ እንችላለን (ሮሜ 6:11-14)::* ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር የብርሃንና የእውነት *መንግሥት* ውስጥ እንጂ፣ በሰይጣን ጨለማ ግዛት ውስጥ አይደሉም *(ቆላ. 1:13)::* ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር *ሥ*ልጣን *ሥ*ር እንጂ፣ በሰይጣን *ሥ*ልጣን *ሥ*ር አይደሉም *(1ኛ ዮሐ. 5:18)::*

*የሚከተሉትን ደረጃዎች መከተል ድልን እንድትቀዳጁ ይረዳችኋል::*

1. በሕይወታችሁ ውስጥ *ሥጋዊ ኃ*ጢአት ይኖር እንደ ሆነ በመፈተሽና ካለም *መ*ኖሩን በመቀበል ለራሳችሁ *ታ*ማኝ ሆናችሁ *ቅረቡ (ማርቆስ 7:21-23፤ ገላ. 5:19-21)::*
2. *ለኃ*ጢአት ሞ*ታ*ችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ሕያው እንደ ሆናችሁ *አስቡ፤* ደግሞም እመኑ *(ሮሜ 6:6፣7፣11)::* በመንፈሳዊ ጦርነት ላይ ድል የሚገኘው በተጨባጭ እውነት እንጂ በስሜት አይደለም:: ነፃ የሚያወጣን *እውነትን* ማወቅ ነው::

   «በ*ሥጋ* ላይ የሚካሄድ ጦርነት መካሄድ ያለበት እውነትን መሠረት በማድረግና እውነትን በመጨበጥ እንጂ አስተማማኝ ያልሆነ ስሜትን በመጠቀም አይደለም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራኒዮ መስቀል ላይ ሞተ፣ የእርሱም ሞት የምትክነት ባሕርይ ስለነበረው የእርሱ ሞት የእኛ ሞት ነው:: የአማኝ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ከክርስቶስ *ጋ*ር ተሰቅሏል:: ይህም የሆነው የአማኙን የኃጢአት *ዕዳ* ለመክፈል ብቻ ሳይሆን የኃጢአትን ተፈጥሮ ኃይል- አልባ በማድረግ አማኙን ከኃጢአት ቁጥጥር ነፃ ለማድረግም ነው:: በ*ሥጋ* ላይ ድልን የመቀዳጀት «ከክርስቶስ *ጋ*ር ተሰቅያለሁ» (ገላትያ 2:20) የሚለውን ፍጹም እውነት በንቃትና በኃይል፣ ቀን በቀንና በየጊዜው የግል ልምምድ የማድረግ ተግባር ነው::» *(ገላትያ 2:20)::*

3. በመንፈስ መመላለስን እንምረጥ (ገላ. 5:16):: የክርስቶስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ መሆኑን እንመን:: ማንኛ ውም አማኝ መንፈስ ቅዱስ አለው (ሮሜ 8:9-10):: በመንፈስ

ቅዱስ መሞላት የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው (ኤፌ. 5:18)። በመንፈስ በምትሞሉበት ጊዜ አካላችሁ፣ ነፍሳችሁና መንፈሳችሁ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥርና ምሪት ሥር ይሆናሉ።

## VI. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

**ኤፌሶን 5:18**

ብርካታ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን እንደ ሆነ አልገባቸውም። ጳውሎስ የኤፌሶን ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንዳለባቸው አስተምሯቸዋል። አንድ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው እንዴት ነው?

1. ኃጢአቶቻችሁን ማስተዋል እንድትችሉ *ራሳችሁን መርምሩ (2ኛ ቆሮ. 13:5)። ታማኞች መሆንና የትኛውን የሕይወታችሁን* ክፍል ሰይጣን እየተቆጣጠረ እንዳለ ለይቶ መረዳት ጠቃሚ ነው *(ኤፌሶን 4:27-31)።*
2. *የምታውቁትን ማንኛውንም ኃጢአት ተናዘዙ (1ኛ ዮሐንስ 1:9)።*
3. *ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ (ሮሜ 6:13፤ 12:1)።* ፈቃዳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስጡ። የግል ሕይወታችሁን፣ የሥራ ሕይወታችሁን፣ ማኅበራዊ ሕይወታችሁን፣ የቤተሰብ ሕይወታችሁንና የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ሕይወታችሁን በእግዚአብሔር ሥልጣንና ቁጥጥር ሥር እንዲሆን አድርጉ።
4. እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላችሁ *በጸሎት ጠይቁ (ሉቃስ 11:13)።*
5. በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላችሁ *በማመን ጥርጣሬንም አስወግዱ።* መጽሐፍ ቅዱስ መሞላት ትችላላችሁ ብሎናል። ስለሆነም መሞላት እንደምንችል እናውቃለን። ዋነኛው ነገር እምነት ነው *(ዮሐንስ 7:38፣ 39፤ ሮሜ 14:23)።*
6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው *ለእግዚአብሔር ፈቃድ ታዘዙ (ዮሐንስ 14:15፤ የሐዋርያት ሥራ 5:32)።* መንፈስ ቅዱስ

የእግዚአብሔርን ቃል በማትታዘዙበት መንገድ ከቶ እንደማይመራችሁ አስታውሱ:: በመንፈስ ቅዱስ በምንሞላበት ጊዜ የተቀደሰ ሕይወት ለመኖርና ፍሬያማ አገልግሎት ለመስጠት ኃይል ይኖረናል::

አካሄዳችንን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንድናደርግ በእርሱም እንድንሞላ የሚረዳን ዓይነተኛ ጸሎት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል:: በዚህ ጸሎት ውስጥ ያሉ ቃላት በራሳቸው ምንም ኃይል የላቸውም:: ይህ ጸሎት የሚገልጸው የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል የሰው ልብ የሚያሳየውን ፍላጎት ነው:: ጸሎት ከአንደበታችን ቃላትን የማውጣት ተግባር ብቻ ሊሆን አይገባም::

*«የተባረክህ የሰማዩ አባታችን ሆይ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዛሬ በመንፈስ መመላለስን እሻለሁ:: ከሥጋ ሥራዎቼ መገላገል የምችለው መንፈስ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ሲኖር ብቻ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ:: መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ሥራና ትንሣኤውን ዛሬ ወደ ሕይወቴ እንዲያመጣልኝ እማጠነዋለሁ:: እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ የራሱን ፍሬ በእኔ ውስጥ እንዲያፈራና ለአንተና ዛሬ ለማያቸው ሁሉ ታላቅ ፍቅር እንዲኖረኝ ልቤን እንዲሞላ እጸልያለሁ:: ውድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አንተን ስላሳዘንሁባቸውና እንዳትሠራብኝ ስለ ከለከልሁባቸው ጊዜያት ሁሉ ይቅር በለኝ:: ድምፅህን ሰምቼ ምላሽ እንድሰጥ እርዳኝ:: ለከበረው ቃልህ ለመታዘዝ ፍላጎትን በውስጤ ቀስቅስ:: በሐሰተኞች መናፍስት ከመታለል ጠብቀኝ:: መንፈስ ቅዱስ በሙላ ሕይወቴ ውስጥ እንዲኖርና እንዲቆጣጠረኝ ፍላጎቴ ነው:: ዛሬ ድልን ለመቀዳጀት በመንፈስ ቅዱስ ላይ በፍጹም እተማመናለሁ:: በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሁሉም የሕይወቴ አንጻሮች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም ሙላት እቀበላለሁ:: አሜን::»*

በሥጋ ላይ ድልን ለማግኘት በመንፈስ መመላለስ አስፈላጊ ነው:: ይህ አካሄድ ድል አድራጊ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድንኖር ይረዳናል:: በመንፈስ የመሞላት ምልክት «የመንፈስ ፍሬዎች» ናቸው *(ማቴ.*

*7:17፣ 20፤ ገላ. 5:22፣23)*:: በመንፈስ ቅዱስ የመሞላታችሁ ግልጽ ማረጋገጫ የዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ በመንፈስ ፍሬዎች የተሞላ መሆኑ ነው::

በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ልምምድ የአንድ ጊዜ እውነታ ሳይሆን፣ ይልቁን የዕለት ተዕለት ፍላጎት ነው:: በመንፈስ መሞላታችንን እናውቅ ዘንድ የግድ በልሳን መናገር ወይም መሬት ላይ መውደቅን የመሳሰሉ መግለጫዎች አያስፈልጉንም:: አስቀድመን የተመኘነውና ደግሞም የጸለይንበት ስለሆነ በመንፈስ እንደምንሞላ እናውቃለን:: በመንፈስ በምንሞላበት ጊዜ ሕይወታችን የተለየ ይሆናል::

ዌስሊ ኤል. ዲዩዌል፣ «Ablaze For God» *(አብሌዝ ፎር ጋድ)* በሚል መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ጠቃሚ ማብራሪያ ይሰጣል:-

> «መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ሁኔታ እንዲነካን በየጊዜው ፍላጐት አለን:: እርሱም በሚሞላን ጊዜ ማለትም በሕይወታችን ውስጥ የጌትነቱን ስፍራ ሲይዝ የክርስትና ሕይወታችን ድል አድራጊ ይሆን ዘንድ ያነጻናል፤ ኃይልንም ይሰጠናል::
>
> ብዙ ጊዜ ይህን መሰዩ ተትረፍርፎ የመፍሰስ ሁኔታ፣ ደግሞም አዲስ ቅባት በዓይን በሚታይ ሁኔታ ወይም በጠንካራ ስሜት በታጀበ ሁኔታ አይከሠትም:: መንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ እኔነት ያለው እንጂ፣ ቅዱስ ስሜት አይደለም:: አዲስ ኃይልና ችሎታ የሚሰጥ የእግዚአብሔር እጅ በእኛ ላይ መሆኑን መገንዘብ ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ ደስታ፤ በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ የተመሠረተ ሁለንተናዊ የእረፍት ስሜት፣ እንዲሁም በቃላት የማይገለጥ ዘላቂ ሰላም ይሰጠናል::»

አዎን፣ የሥላሴ ሦስተኛው አካል የሆነው ቅዱስ አካል፣ በሙላት በእኛ ውስጥ ሲያድር መላ ሕይወታችንን ይገዛዋል:: እርሱ አዝማቾችን ደጋግሞ በመዘመር ወይም እጆችን በመዘርጋት ወይም ውዳሴን በማስተጋባት በሰው ሠራሽ ስሜት ሕልውናውን ማምጣት የምንችለው አይደለም:: የተቀደሱ እጆች ለእግዚአብሔር በእምነትና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሊነሡ፣ እንደዚሁም የተቀደሱ ውዳሴዎች በቃላት ሊገለጹና ሊዘመሩ ይችላሉ:: ይህ ሊሆን የሚችለው በሰብአዊ ስሜት

ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ሕልውና መልካምነትና ጸጋ ውስጥ ሆኖ ከሚያመሰግን፣ ስለ ቸርነቱና ስለ ጸጋው ከሚያወድስ ልብ ወጥቶ ሲፈስ ነው።

ምእመናን ተቀምጠው በማዳመጥ ላይ ሳሉ፣ እግዚአብሔር በኃይሉ በጆናታን ኤድዋርድስ ላይ በወረደ ጊዜ ምእመናኑ ወደ ሲኦል እንዳይወርዱ ፈርተውና ደንግጠው ገሚሱ መቀመጫዎቻቸውን ሲይዙ የተቀሩት ደግሞ የቤተ ክርስቲያኑን አምዶች ይይዙ ነበር። ይሁን እንጂ፣ በዚህን ጊዜ ጆናታን እየጮኸና እየተቆጣ ወደፊትና ወደ ኋላ ይንጐራደድ ነበር? በፍጹም ይህን አላደረገም። መልእክቱን ያነበበት የነበረውን ወረቀት እንኳን እንዲታየው ወደ ዓይኑ አቅርቦ ከያዘበት ስፍራ አላንቀሳቀሰውም። መልእክቱንም ለአድማጮቹ ያቀርብበት ከነበረው የድምፅ መጠን በላይ አልጨመረም። ረጋ ብሎ በንግግራዊ አቀራረብ ይሰብክ ነበር። በስሜት ተቀስቅሶ ወይም ድምፅን ከፍ አድርጐ መናገር ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጋር አይስተካከልም።

የስሜት ግፊት ሳይኖርበት በዝግታና በመረጋጋት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታግዞ የሚቀርብ መልእክት ከርቱአዊ (ቀልጣፋ) አንደበትና እንቅስቃሴ የበለጠ መንፈሳዊ ውጤት ይኖረዋል። በሳይኮሎጂ ወይም በሥነ ልቦና ዘዴ በመጠቀም የሰዎችን ስሜት ለመቀስቀስ ይቻላል። *የእግዚአብሔርን መንፈስ ግን በዚህ ዓይነት እንዲሠራ ማድረግ አይቻልም።*

አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላና በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በቃሉ ብርሃን የሚሄድ ከሆነ ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይጥራል። በውስጡ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ላይም ዕለት በዕለት ይደገፋል። በውስጡ ያደረውም መንፈስ ቅዱስ የሚደርስበትን ፈተና ሁሉ ድል እንዲያደርግ ያግዘዋል።

# VII. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ

ክርስቲያኖች ከሰይጣን ጋር በጦርነት ላይ ናቸው:: በዚህ ጦርነት ሰይጣንና ኃጢአትን ለማሸነፍ ምን ማድረግ እንዳለብን ተምረናል:: በዚህ መንፈስ መራመድና በመንፈሱም መሞላት አለብን:: በሥጋ ፍላጎቶቻችን መታሠር አንችልም::

ለዚህ መንፈሳዊ ውጊያ እግዚአብሔር ጠቃሚ መሣሪያዎችን ሰጥቶናል:: እነዚህም *በኤፌሶን 6:10-18* ላይ ይገኛሉ:: በክርስቶስ ኢየሱስ ሰይጣንንና ኃጢአትን ለማሸነፍ የሚያስፈልጉን ሁሉ እንዳሉን አስታውሱ *(2ኛ ጴጥሮስ 1:3)::*

ይሁንና አንዳንድ ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ::

- ቁጥር 10 በጌታ የበረታችሁ ሁኑ::
- ቁጥር 11፣ 13 የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ::
- ቁጥር 14 በመዘጋጀት / ጠንክራችሁ ቁሙ::

ሰይጣንን በሥጋ ክንዳችን ለማሸነፍ ብንሞክር እንወድቃለን:: ነገር ግን ጠንክረን የመቆም፣ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የመልበስና የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ የመሻት ኃላፊነት አለብን:: ለጦርነት የተዘጋጀን ወታደሮች መሆን ይገባናል::

የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር በምንለብስበት ጊዜ፣ ኢየሱስን ራሱን እንለብሰዋለን *(ሮሜ 13:12-14)::* የጨለማን ሥራ ሁሉ እየተቃወምን የእግዚአብሔርን የእውነት ብርሃን ዕቃ ጦር መልበስ አለብን:: ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን በተቀበልን ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከሰይጣን ግዛት አውጥቶን በራሱ መንግሥት ውስጥ አስቀምጦናል:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሰይጣን ሥልጣን የለውም *(ዮሐንስ 14:30፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:18)::* ሰይጣን ሥልጣን የሚያገኘው ያን ሥልጣን ስንሰጠው ብቻ ነው::

*ኤፌሶን 6:11* «የእግዚአብሔርን *ዕቃ ጦር* ሁሉ ልበሱ::» ይላል እንጂ ከእግዚአብሔር ዕቃ ጦር «አንዳንዶቹን» ልበሱ አይልም:: *ሁሉንም* ዕቃ ጦር ማወቅና *ሁሉንም* መልበስ አለብን::

*2ኛ ቆሮንቶስ 10:3፣4* ሰይጣንንና ኃጢአትን ለመዋጋት የምንጠቀምባቸው *የጦር ዕቃዎች* የዓለም ጦር *መሣሪያዎች* አይደሉም:: ከእግዚአብሔር *ኃይል ጋር* አብረው *የሚመጡ መሣሪያዎች* ናቸው:: በመሆኑም የሰይጣንን ምሽግ ለማፈራረስ ይችላሉ::

*ኤፌሶን 6:14፣15* እያንዳንዱ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የጦር *ዕቃዎች* ውስጥ *የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ* ክፍሎች አሉት:: እነዚህም የእውነት *መታጠቂያ*፣ የጽድቅ ጥሩርና የሰላም ወንጌል የዝግጁነት ትጥቆች ናቸው:: «ወገባችሁን *ታጥቃችሁ*»፣ «የጽድቅን ጥሩር ለብሳችሁ» እና «እግሮቻችሁ ተጫምተው» በሚሉት ውስጥ *ያለው* የግሥ ጊዜ *የሚያመለክተው* እነዚህ *ሦስቱ* የጦር *ዕቃዎች* የተለበሱ ወይም የተደረጉ *መሆናቸውን ያመለክታል*:: ደኅንነትን ባገኘን ጊዜ እነዚህን ትጥቆች ተቀብለናል::

## *1. የእውነት መታጠቂያ (ኤፌሶን 6:14)*

«ወገባችሁን በእውነት *ታጥቃችሁ* ቁሙ::» አንድ *ወታደር* በወገቡ ላይ ጠንካራ ቀበቶ *ይታጠቃል*:: *የሚያደርገው* ቀበቶ *የመጀመሪያው ዕቃ* ጦር ነው:: ሌሎቹ *በመታጠቂያው* ላይ የሚነገቡ (የሚንጠለጠሉ) ናቸው:: ውጊያችንን ሁሌም *መጀመር ያለብን በእውነት ነው::*

በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የማንኛውም ነገር *መሠረት* እውነት ነው:: ኢየሱስ «እኔ እውነት ነኝ» ብሏል *(ዮሐንስ 14:6)::* ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ስላለ እውነትም በእኛ ውስጥ ነው *(ኤፌሶን 4:21)::* የእግዚአብሔርን እውነት ሁልጊዜ ማሰብ አለብን፤ ምክንያቱም ሰይጣን ሁልጊዜ ይህን እውነት ሊያጣምም ይፈልጋል:: ሔዋን በዔድን ገነት ውስጥ በነበረች ጊዜ እንደ ዋሻት ሁሉ፣ እኛንም በውሸቱ ሊሸነግለን ይፈልጋል::

*ፈተና በሚመጣብን ጊዜ ፈተናውን መመርመር ያለብን ከእግዚአብሔር ቃል እውነት አንጻር ሊሆን ይገባል::* «በብርሃን የሚመላለስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኔ ይህን ማድረግ እችላለሁ?» ብላችሁ *ራሳችሁን* ጠይቁ:: *ፈተናውን* ከእግዚአብሔር *ቃል* እውነት *ጋር* አነጻጽሩት:: ከእግዚአብሔር እውነት *ጋር* የማይስማማ ከሆነ

አናደርገውም። *የእግዚአብሔር እውነት የሰይጣንን ውሸት ሁልጊዜ ያሸንፋል።*

*ዮሐንስ 8:32* የሚለውን አስታውሱ፤ «እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።» እውነትን በምናውቅበት ጊዜ እውነቱ ከሰይጣን ኃይል ነፃ ያወጣናል፣ ሰይጣንም ይሸነፋል። ቢያሸንፍና እኛ በእርሱ ብናምን በእኛ ላይ ኃይል እንደሚኖረው ስለሚያውቅ ሰይጣን ይዋሻል። እውነትን ማወቅና አጠቃቀሙንም መማር ይገባናል። የዚያን ጊዜ ሰይጣንን ማሸነፍ እንችላለን።

ሰይጣንን ማሸነፍ ከፈለግን የሚከተሉትን ወሳኝ እውነቶች ማመን ይገባናል።

- የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ በእርሱም ዘንድ ተቀባይነት አግኝተናል።
- እግዚአብሔር እኛን የሚያየን እንደ ቅዱሳን ነው። አሮጌው ተፈጥሮ/ ሰው ሞቶአል። የኢየሱስ ሕይወት በእኛ ውስጥ ነው።
- የድል ሕይወትን *መምረጥ እንችላለን።*
- ለኃጢአት ሞተን ለእግዚአብሔር ሕያው ነን *(ሮሜ 6:6፣ 11)።* ኃጢአት በእኛ ላይ ገዥነቱ አክትሟል።
- *ይሁንና ኃጢአት አሁንም እየሠራ ነው። «የሰውነትን ሥራ»* *ገድለን (ሮሜ 8:13)* በመንፈስ *መመላለስ* ይገባናል *(ገላትያ 5:16)።*

*2ኛ ቆሮንቶስ 10:5ን* በቃል አጥኑ። *መጥፎ* አሳቦችን *መቃወም*ና የእግዚአብሔርን *ቃል* እውነት *መምረጥ* ይገባናል።

## *2. የጽድቅ ጥሩር (ኤፌሶን 6:14)*

ወታደር ጥሩር የሚለብሰው የሚምዘገዘጉት ፍላፃዎች ልብና ሳንባዎቹን ወግተው እንዳይገድሉት ነው። በተመሳሳይ መንገድ ክርስቲያን የጽድቅን ጥሩር የሚለብሰው የሰይጣን ፍላፃዎች ወግተው እንዳይገድሉት ነው። በምንድንበት ወይም በምንጸድቅበት ጊዜ ክርስቶስን እንለብሰዋለን። *ይህም* ማለት እግዚአብሔር እኛን በሚያይበት ጊዜ፣ የእኛን ኃጢአት በመመልከት *ፈንታ* የኢየሱስን

*ጽድቅ ያያል ማለት ነው (2ኛ ቆሮ. 5:21፤ 1ኛ ቆሮ. 1:30፤ ፊልጵ. 3:8፣ 9)።*

ኃጢአትን በምንሠራበት ጊዜ ሰይጣን «እውነተኛ ክርስቲያን ብትሆን ይህን ባላደርግህ ነበር» በማለት ይከሰናል። ነገር ግን ጳውሎስ *በሮሜ 8:33* የሰጠውን ያንኑ ምላሽ እኛም መስጠት እንችላለን፣ «እግዚአብሔርም የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?» በሌላ አባባል እግዚአብሔር ልጆቹ እንድንሆን ከመረጠን፣ ማንም ሊከሰን አይችልም። ከእግዚአብሔር እጅ ሊያወጣን የሚችል ምንም ነገር የለም። በክርስቶስ ያለን ጽድቅ ከሰይጣን ክሶች ሁሉ ይጋርደናል።

*በኢየሱስ የጽድቅ ብርሃን ውስጥ ሰይጣን ሊሠራ አይችልም።* ሰይጣንን ለማሸነፍ ልባችንን በጽድቅ ላይ ማድረግ ይገባናል። ምንም እንኳ እኛ በየጊዜው ኃጢአትን የምንሠራ ሰዎች ብንሆንም፣ በክርስቶስ ጽድቅ ውስጥ በምንቆምበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ቅዱሳን አድርጎ ይመለከተናል።

በኢየሱስ ጽድቅ ውስጥ መቆም ከፈለግን፣ ኃጢአትን ባደረግን ጊዜ ሁሉ ኃጢአታችንን *መናዘዝና ንስሐ* መግባት ያስፈልገናል *(1ኛ ዮሐንስ 1:9)*። ስንናዘዝና ንስሐ ስንገባ፣ ኃጢአት መሥራታችንን እንቀበላለን፣ ያንንም ኃጢአት ላለመድገም እንወስናለን። ኃጢአት ስንሠራ የምናጣው ደኅንነታችንን ሳይሆን፣ ሰይጣንን የማሸነፍ አቅማችንን ነው።

*በኤፌሶን 4:27* ላይ ጳውሎስ በሕይወታችሁ «ለሰይጣን ዕድል ፈንታ አትስጡት» ይለናል። ዕድል ከሰጠነው ሰይጣን በእኛ ውስጥ እንዲሠራ ፈቀድንለት ማለት ነው። ኃጢአትን ከሠራን በኋላ የማንናዘዝና ንስሐ የማንገባ ከሆንን፣ ለሰይጣን ዕድል እንሰጣለን። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ያላንዳች ጥርጣሬ ወደ ባሰ ኃጢአት ይመራናል። ስለዚህ ወደ ድል ጎዳና ለመግባት መናዘዝና ከኃጢአታችን ፍጹም መመለስ ይኖርብናል። በሐዋ. ሥራ 24:16 ጳውሎስ፣ «ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለበት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ።» ብሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ እኛም ኃጢአታችንን ለመናዘዝ፣ ለኃጢአትም ጀርባችንን ለመስጠትና ንጹሕ ሕሊናን ለመያዝ እንትጋ።

### *3. በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ (ኤፌሶን 6:15)*

ወታደሮች ጠንካራ ጫማ ሊኖራቸው ይገባል:: ጥንካሬ የሌላቸው ጫማዎች በጦርነት ጊዜ ይቀደዳሉ:: ይህ ሲሆን ደግሞ ወታደሩ ቶሎ ቶሎ የመራመድ ችግር ይገጥመዋል ወይም እግሮቹ ይጎዱበታል:: የክርስቲያን መጫሚያ «የሰላም ወንጌል» ነው:: ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን የተቀበልን ከሆንን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን *(ሮሜ 5:1)::* ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለየን ነበርን:: አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በደሙ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ቀርበናል:: ክርስቶስ ሰላማችን ነው *(ኤፌሶን 2:13-17)::*

አንድ ወታደር ቀበቶውን አጥብቆ ሲታጠቅና ጥሩሩን ሲለብስ እንዲሁም ጠንካራ መጫሚያዎቹን ሲያደርግ ያለፍርሃት ለውጊያ የተዘጋጀ ይሆናል:: *ፊልጵስዩስ 4:6፣7* የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንንና አእምሮአችን ይጠብቃል ይላል:: ይህ ሰላም ሰይጣንን ለማሸነፍ ስለሚረዳን፣ በምንሠራው ሁሉ እርሱ ሊያደርገው በሚችለው ምንም ፍርሃትና *ሥጋት* ሊኖረን አይችልም:: በእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር ውስጥ የምንኖር ከሆንን፣ ያ ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል *(1ኛ ዮሐንስ 4:16፣ 18)::* «የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችን *ሥር* ፈጥኖ ስለሚቀጠቅጥ» ያለ ፍርሃት ወደ ጦርነቱ እንገባለን *(ሮሜ 16:20)::*

በክርስቶስ የተሰጠንን ማንነት አስታውሱ:: ኢየሱስ በእኛ ውስጥ እኛም በኢየሱስ ውስጥ ነን:: ስለዚህም እኛ የኃያሉ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን በእርሱ ኃይል ያለ ፍርሃት መቆም እንችላለን:: በሕይወታችን ውስጥ ስፍራ ካልሰጠነው በቀር ሰይጣን በእኛ ላይ *ሥ*ልጣን አይኖረውም:: ጠንካራ ጫማዎችን በእግሮቹ በማድረግ ወታደር ለጦርነት ይሰናዳል:: እኛም የእግዚአብሔርን የሰላም ጫማዎች በማድረግ ለመንፈሳዊ ጦርነት ልንዘጋጅ ይገባናል::

*ኤፌሶን 6:16-17፣* በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ደግሞ ሦስት ተጨማሪ የጦር ዕቃዎችን እናገኛለን:: የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ

ማለትም (የእውነት መታጠቂያ፣ የጽድቅ ጥሩርና የሰላም መሰናጃ ጫማዎች) በክርስቶስ በመሆናችን የእኛ ናቸው:: እውነቱን እናውቃለን፣ የክርስቶስም ጽድቅ የእኛ ነው፣ ስለዚህ በሰላም የተጠበቅን ነን:: ነገር ግን የሚቀጥሉት ሦስቱ ማለትም የእምነት ጋሻ፣ የደኅንነት ራስ ቁርና የመንፈስ ሰይፍ የእኛ የሚሆኑት ከምናደርገው ነገር የተነሣ ነው:: ስለዚህ ልንጠቀምባቸው ይገባል::

### *4. የእምነት ጋሻ (ኤፌሶን 6:16)*

ጋሻ አንድ ወታደር የጠላትን ፍላጻ ለመመከት የሚጠቀምበት ከጠንካራ ብረት የተሠራ የጦር ዕቃ ዓይነት ነው:: የሚወረወሩበት ፍላጻዎች እንዳይወጉት ወታደሩ ከጋሻው በስተኋላ ራሱን ይከልላል:: ሰይጣን ሁልጊዜ በፍላጻዎቹ ያጠቃናል:: ብርቱ ከሆኑት ከእነዚህ ፍላጻዎች ሦስቱ:- ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ክፉ አሳብ ናቸው:: የእምነት ሰው ያመነውን ያውቃል፣ የሰይጣንንም ጥቃት ለማሸነፍ እንዴት *ይህንኑ እምነቱን* እንደሚጠቀምበት ያስተውላል::

ፍርሃት በሚጀምረን ጊዜ እግዚአብሔር የፍርሃትን መንፈስ ስላልሰጠን ይህን ፍርሃት በዚህ እንቃወመዋለን *(2ኛ ጢሞ. 1:7)::* የእግዚአብሔር ኃይል ከሰይጣን ኃይል እንደሚበልጥ ስለምናውቅ ለፍርሃት ስፍራ አንሰጠም *(1ኛ ዮሐንስ 4:4)::* ራሳችንን ለእግዚአብሔር ብንሰጥና ሰይጣንን ብንቃወም፣ ሰይጣን ከእኛ ይሸሻል *(ያዕቆብ 4:7)::*

መጥፎ አሳቦችን ማሰብ ብንጀምር፣ ወይም እግዚአብሔርን ብንጠራጠር የሰይጣንን ፍላጻዎች መከላከል አንችልም:: ስለ እግዚአብሔር የተነገሩ እውነቶችንና በክርስቶስ ያለንን ማንነት የራሳችን አድርገን መቀበል አለብን:: ይህን ስናደርግ ጠላታችንን እናሸንፋለን *(1ኛ ዮሐንስ 5:4፣ 5)::*

እምነታችን እየተጠናከረ እንዲሄድ ስለ እግዚአብሔር ብዙ እውቀት እየጨመርን መሄድ ይኖርብናል:: የእግዚአብሔርን እውነት ተጠቅመን የሰይጣንን ውሸቶች ስናሸንፍ እምነታችን እያደገ መሆኑን እንገነዘባለን:: እምነታችን የእግዚአብሔርን ቃል በምንሰማበት ጊዜም ያድጋል *(ሮሜ 10:17)::* ነገር ግን እውነትን ማወቅና ማመን የእኛ ፈንታ ነው::

## *5. የደኅንነት ራስ ቁር (ኤፌሶን 6:17)*

የራስ ቁር የወታደርን ራስ ይከላከላል:: ፍለጻ የወታደሩን ጭንቅላት ካፈረሰው ወታደሩ የተሰለፈበትን ውጊያ የማሸነፍ ዕድል አይኖረውም:: ክርስቲያን ኢየሱስን የማየት ታላቅ ተስፋ አለው *(1ኛ ዮሐንስ 3:2፣ 3)::* ይህ ተስፋ የሚመነጨው ከደኅንነታችን ነው:: ይህ ደኅንነት ደግሞ ዘላለማዊ ደኅንነት ስለሆነ፣ ሰይጣን ከእኛ ሊወስድብን አይችልም:: አስተሳሰባችንን ስለሚጋርድና በሰላምም ስለሚጠብቀን፣ የደኅንነት ተስፋችን በራስ ቁር ይመሰላል:: እኛ በእግዚአብሔር ደኅንነትን ያገኘን ስለሆንን በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ያለ ሥጋት እንኖራለን:: ደኅንነታችንን ስንጠራጠር ሰይጣን ደስ ይለዋል፣ የራስ ቁር እንደሌላቸው ወታደሮች አድርጎም ይመለከተናል:: በፊቱ አቅመ-ቢሶች ስለምንሆን ከዚህ በኋላ ኮብላዮች እንድንሆን ሊያደርገን ይችላል:: ነገር ግን ደኅንነትን እንዳገኘንና የዳንን በመሆናችን ደኅንነታችንንም ማንም ሊወስድብን እንደማይችል ካወቅን፣ እምነታችን ዳግም ይጠነክራል:: ከዚህ በኋላ ጥርጣሬን አስወግደን ለክርስቶስ ታዛዥ እንዲሆን አሳባችንን እናስገዛዋለን *(2ኛ ቆሮ. 10:5)::*

## *6. የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የመንፈስ ሰይፍ (ኤፌሶን 6:17)*

ወታደር ሰይፍን የሚጠቀመው ራሱን ለመከላከልና ጠላቶቹን ለመግደል ነው:: የክርስቲያን ሰይፍ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚነገር፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ሰይጣን ወደ እኛ የሚያመጣቸውን የተሳሳቱ አሳቦች የእግዚአብሔር ቃል ሊያፈራርሳቸውና ድል ሊያደርጋቸው ይችላል:: ከሰይጣን የሚመነጩትንም ፍርሃቶቻችንን ድል ሊያደርግ ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጠቀም ይኖርብናል::

መጽሐፍ ቅዱስን የማታነቡና በቃላችሁ የማትይዙ ሆናችሁ፣ ሰይጣንን ማሸነፍ የምትችሉ ይመስላችኋል? ሊሆን አይችልም! ነገር ግን ቃሉን ካወቃችሁና በቃላችሁም ካጠናችሁት ጥቅሶቹ እናንተን በመጠበቅና ኃጢአትንም በማራቅ ይረዷችኋል *(መዝሙር 119:11)::* የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን *ሙክ ብላችሁ* በቃል ተናገሯቸው:: ሰይጣን

ጥቅሶቹን በሚሰማቸው ጊዜ ይሸሻል። ኢየሱስ በምድረበዳ ሲፈተን፣ ሦስቱንም ጊዜ ሰይጣንን ለማሸነፍ የተጠቀመው የእግዚአብሔርን ቃል ነበር። በሦስተኛው ጊዜ ሰይጣን ጥሎት ሸሸ።

*ኤርምያስ 23:29፤ ዕብራውያን 4:12* የእግዚአብሔር ቃል ኃይል አለው። ሰይጣንን ለማሸነፍ ይህን ኃይል መጠቀም እንችላለን።

*2ኛ ጢሞቴዎስ 2:15* ፈተናን ለማሸነፍ ልባችንንና አእምሮአችንን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ማድረግ አለብን።

እስካሁን ስለ እግዚአብሔር ዕቃ ጦር የቀረበውን ትምህርት ተመልክተናል። ትምህርቱ የጀመረው እውነትን በማወቅ ነው። ከዚያም የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ለብሰን በእግዚአብሔር ሰላም እንመላለሳለን። የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምንጠቀምበት ጊዜ በእምነታችንና በደኅንነታችን ተስፋ ጸንተን እንቆማለን። ሰይጣንንና ኃጢአትን የማሸነፊያ መንገዱ ይኸው ነው። ነገር ግን ከዚህ የበለጠ አንድ ሌላ ጠቃሚ ነገር አለ።

*7. ጸሎት (ኤፌሶን 6:18)*

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ ብሏል። ነገር ግን በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ መጸለይ ይገባናል። ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው። አንዱ ያለ ሌላው በሚገባ ሊሠራ አይችልም።

በምንጸልይበት ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገራለን። እርሱ አባታችን ነው። ጸሎታችንንም ያደምጣል። የምናስበውንና የሚሰማንን ለእርሱ ለመንገር ነጻነት አለን። ሆኖም ግን ስንጸልይ ደካሞች መሆናችንን በመገንዘብ በተሰበረ ልብ መጸለይ ይገባናል።

ጠንክረን መቆም ከፈለግን የእግዚአብሔርን እርዳታ መፈለግ ይገባናል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጸለይን መማር አለብን *(ሮሜ 8:26፣27)።* ከጸለይን እግዚአብሔር እንደሚረዳን ቃል ገብቶልናል *(1ኛ ቆሮ. 10:13)።* ከምንችለው በላይ እንድንፈተን እንደማይፈቅድ ተናግሯል። ደግሞም በፈተና ጊዜ ድል አድራጊዎች እንድንሆን ሁልጊዜ መውጫውን እንደሚያዘጋጅም ተናግሯል። እግዚአብሔር

እንዲረዳን ከጸለይን ይረዳናል:: ነገር ግን የማንጸልይ ከሆንን የእርሱን እርዳታ መጠበቅ የለብንም *(ዮሐ. 16:23፣24፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:14፣15)::* በጸሎት ወደ ድል የሚያደርሰንን መንገድ እናገኛለን *(ማቴዎስ 26:41)::*

በእምነታችን ጸንተን መቆምን መማር አለብን:: በክርስቶስ ባለን ማንነት ላይ ጸንተን እንቁም:: ሰይጣን በእግዚአብሔር ቸርነት ላይ የጥርጣሬ ማዕበል እንዳይለቅብን፣ እነዚህ ነገሮች አስተሳሰባችንን የሚመሩ ሥርዓቶች ሊሆኑ ይገባል:: በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የተማርነው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር እውነት ነው:: እነዚህን እውነቶች አጥብቀን ስንይዝና የሕይወታችን አካል ስናደርጋቸው ሰይጣንን ሁልጊዜ እናሸንፈዋለን::

*በ2ኛ ቆሮንቶስ 1:8-10፣* ጳውሎስ የደረሰበትን በርካታ ሥቃይና መከራ ይጠቅሳል:: ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ከሥቃይ እንደሚያድነው ያውቅ ነበር:: «እርሱም (እግዚአብሔር) ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፣ ያድነንማል» ብሏል:: በእግዚአብሔር የምንተማመን ከሆንን በእርግጥ እኛንም ወደፊትም ያድነናል::

## ጥያቄዎች

*ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ጋር በጦርነት ውስጥ ነን::*

*የሰይጣን ኃይሉ የሚመነጨው ከውሸቶቹ ነው::*

*እንደ ክርስቲያንነታችን ኃይላችን ከእግዚአብሔር የሚመጣው እውነትን ስናውቅ ነው:: ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለ እግዚአብሔር ኃይል ያለው እውነት ከሰይጣን ኃይል ነፃ ያወጣናል::*

1. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ በምንለብስበት ጊዜ ምን ማድረግ እንችላለን? ሮሜ 13:12-14
2. የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ እውነት ምን ይነግሩናል?

   ሀ) ዮሐንስ 8:32፣ 36 — ሐ) ዮሐንስ 16:13

   ለ) ዮሐንስ 14:6 — መ) ዮሐንስ 17:15፣17
3. ከሰይጣን ጋር በምናደርገው ጦርነት እውነትን ማወቅ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ዮሐንስ 8:32፣ 44

4. የጽድቅ ጥሩር ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 1:30፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5:21

5. ሀ) በእግዚአብሔር ዘንድ ሰላም እንዳለን ማወቅ የሚጠቅመን እንዴት ነው? ሮሜ 5:1፤ ቆላስይስ 3:15

   ለ) በሮሜ 16:20 የሚገኘ ተስፋ ምንድን ነው?

6. የእምነት ጋሻ የሚከልለን እንዴት ነው? 1ኛ ዮሐንስ 5:4፣ 5፤ ያዕቆብ 4:7::

7. ሀ) የደኅንነት የራስ ቁር ሊከላከልልን የሚችለው እንዴት ነው? ዮሐንስ 10:27-29፤ ሮሜ 8:35፣38፣39

   ለ) መጥፎ አሳቦች ወደ እኛ ሲመጡ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 10:5

8. ሀ) የመንፈስ ሰይፍ ምንድን ነው? ኤፌሶን 6:17

   ለ) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ምን ማድረግ ይችላል? መዝሙር 119:11፤ ኤርምያስ 23:29፤ ዕብራውያን 4:12

9. ሀ) ኤፌሶን 6:18 መጸለይ አስፈላጊ እንደ ሆነ ይናገራል:: ጸሎት ሰይጣንን ለማሸነፍ የሚጠቅመን እንዴት ነው?

   ለ) የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ጸሎት ምን ይናገራሉ?

      i) ማቴዎስ 26:41 ii) ሮሜ 8:26-27

## VIII. እውነተኛውን ነጻነት ስለ ማወቅ

በ *ማቴዎስ 16:24* ላይ ኢየሱስ፣ በእርሱ የሚገኘውን እውነተኛ ነጻነት እንዴት ማወቅ እንደምንችል ይገልጻል:: ነጻነት የሚመጣው በመንፈስ ስንመላለስ፣ በእምነት ስንራመድ እና ከሰይጣንና ከዚህ ዓለም ነገሮች እሥራት ነፃ ስንወጣ ነው::

*1. ራስን መካድ*

**ራስን መካድ:-* በውድድር ለማሸነፍ የሚፈልግ ሰው አካሉን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን አያደርግም:: ለምሳሌ፣ ሲጋራ አያጨስም፣ አስካሪ መጠጦችን አይጠጣም:: የዩኒቨርስቲ ትምህርት ለመማር የፈለገ ማንኛውም ሰው ጠንክሮ ያጠናል እንጂ በጨዋታና በፌዝ ጊዜውን አያጠፋም:: ይህ እንግዲህ *ራስን መካድ* ነው፣ ማለትም ወደ አንድ ግብ ለመድረስ የተወሰኑ ነገሮችን መተው ማለት ነው:: ወደ አሰብነው ግብ በምንደርስበት ጊዜ፣ ክብርና ሞገስን እንቀበላለን:: ራስን መካድ ጥሩ ነው:: ኃጢአትን ለማሸነፍ ሊረዳን ይችላል:: *1ኛ ቆሮንቶስ 9:24-27 አንብቡ::*

*ሆኖም *ራስን መካድ* የተለየ ነው:: *ራሳችንን በምንክድበት* ጊዜ መንፈስ ቅዱስን የሕይወታችን ጌታ እናደርገዋለን:: ራሳችንን ከበላይነት ዙፋን ላይ አውርደን መንፈስ ቅዱስን እናስቀምጥበታለን:: መንፈስ ቅዱስ በትክክለኛው አቅጣጫ እንዲመራንና እንዲቆጣጠረን እንፈቅድለታለን *(ዮሐንስ 16:13)::* (በክፍል IV-1 የተገለጹትን ሦስት ሥዕላዊ ማስረጃዎችን መለስ ብላችሁ ተመልከቱ::)

በእኛ መሥራት እንዲችል ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር እንሰጣለን *(ፊልጵ. 1:6)::* ወደ የትኛውም የሕይወታችን ክፍልና ምሥጢራዊ ስፍራ ሁሉ የሚያስገባውን በራችንን በመክፈት መንፈስ ቅዱስ ሥልጣኑን እንዲወስድ እንፈቅዳለን:: ይህንንም ስናደርግ ሕይወታችንን የእግዚአብሔር ቅዱስ ቤት አድርገን በመቁጠር፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል እየገባ እንዲያፀዳውና እንዲያሳምረው መፍቀድ እንደ ማለት ነው:: እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ሊሠራ ስለሚፈልግ በእኛ ውስጥ እንዲሠራ ልንፈቅድለት ይገባል:: ራሳችንን የካድን ሰዎች ከሆንን፣ ለራሳችን ምንም ዓይነት ክብር አንፈልግም:: ይልቁንም፣ ፍላጎታችን እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ተገልጾ ክብርን እንዲያገኝ ማድረግ ይሆናል:: እንዲህ ያለው ሕይወት ራስን ሳይሆን *እግዚአብሔርን ማዕከል* ያደረገ ሕይወት ነው::

እግዚአብሔር የፈጠረን የግል ምኞታችንን እንድንከተል አይደለም:: እርሱ እኛን የፈጠረን እርሱን መከተልን እንድንመርጥና እርሱ እንድንፈጽም የሚፈልገውን እንድናደርግ ነው:: እርሱ የፈጠረን

እርሱን እንድናከብር ነው *(ፊልጵስዩስ 1:11)*:: ስለዚህ እግዚአብሔርን የማገልገል ወይም የራሳችንን ፈቃድ ተከትለን ሰይጣንን የማገልገል ምርጫ አለን ማለት ነው:: ራሳችንን በምንክድበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን እንዲያመጣ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ላይ እንዲሠለጥን ፈቃድ እንሰጠዋለን::

በክርስቶስ ነፃ የሆንን ሰዎች ከመሆናችን በፊት ራሳችንን መካድ አለብን::

## 2. መስቀላችሁን ተሸከሙ

የኢየሱስን መስቀል ተሸከሙ:: «መስቀሉን ተሸከሙ» ማለት ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንስጥ ማለት ነው:: ክርስቶስ እንደ ተሠቃየ ለመሠቃየት ፈቃደኞች ነን ማለት ነው:: ይህን ካደረግን ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍል ክርስቶስን እንከተላለን:: «መስቀላችንን መሸከም» ማለት «ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሞት ፈቃደኛ ነኝ» ማለታችን ነው *(ፊልጵስዩስ 1:21፤ ገላትያ 6:17)*::

*2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12* ክርስቲያን መከራ ሊገጥመው እንደሚችል መጠበቅ አለበት:: የተለያዩ ዓይነት መከራዎች ወይም ሥቃዮች አሉ:- በሽታ፣ ድህነት፣ ረሃብ፣ የዘመድ መሞት የመሳሰሉ ናቸው:: አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው የሚያሾፉባቸው ጎረቤቶች ሲኖሯቸው፣ ሌሎች ደግሞ የታመመ ልጃቸውን ወደ ጠንቋይ ቤት እንዲወስዱ ግፊት የሚያደርጉባቸው ዘመዶች ይኖሯቸዋል:: ዛሬ በአንዳንድ አገሮች፣ ክርስቲያኖች ክርስቲያን ስለሆኑ ብቻ ወኅኒ ቤት ይገባሉ፤ ይደበደባሉ፣ እስከ መገደልም ይደርሳሉ:: እስቲ ራሳችሁን እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ፣ «ክፉ ሰዎች መጸለይና እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳቆም ቢነግሩኝ ምን አደርጋለሁ? በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ካላቆምክ እንገድልሃለን ቢሉኝ ምን አደርጋለሁ?»

ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ ተሠቃይቷል:: *ዕብራውያን 5:8* «. . . ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ» ይላል:: ኢየሱስ ምሳሌያችን ነው:: እኛ የእርሱን ፈለግ እንከተላለን *(1ኛ ጴጥሮስ 2:21-23)*::

ኢየሱስ መታዘዝን በመከራ ከተማረ፣ እኛም በመከራ መማር አለብን::
*2ኛ ጢሞቴዎስ 2:11፣ 12 አንብቡ::*

ዮሐንስ 16:33 ልናስታውሰው የሚገባን መልካም ጥቅስ ነው:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ»::

### *3. ኢየሱስን ተከተሉ*

ኢየሱስን ከተከተልን የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ ይታያል *(2ኛ ቆሮንቶስ 4:11)::* ኢየሱስን በመከተላችን፣ የእግዚአብሔር ነገሮች ከዚህ ዓለም ነገሮች ይልቅ ይበልጥ ዋጋ እንዳላቸው እናሳያለን *(ማቴዎስ 10:37-38)::* ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢየሱስን ይበልጥ የመምሰልና የዚህን ዓለም አካሄድ ያለመከተል ፍላጎት ሊያድርብን ያስፈልጋል *(ሮሜ 12:1፣2)::* ብዙ ጊዜ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት እንመለከትና ከእነርሱ የተሻለ አኗኗር ስላለን እኛ ጥሩ ክርስቲያኖች ነን ብለን እናስባለን:: ነገር ግን ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር አይገባንም:: ራሳችንን ማነጻጸር ያለብን ከኢየሱስ ጋር ነው:: ያኔ ገና ብዙ መማር እንዳለብን እናያለን::

*1ኛ ጢሞቴዎስ 4:8* - እጅግ አስፈላጊው ነገር ምንድን ነበር?
*ሉቃስ 10:38-42* - ለማርታ እጅግ አስፈላጊው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 40)?
ለማርያምስ እጅግ አስፈላጊው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 39)?
ኢየሱስ ምን አለ? (ቁጥር 41፣42)
*ዕብራውያን 11:24-26* - ለሙሴ እጅግ አስፈላጊው ነገር ምን ነበር?

እናንተስ፣ ለእኛ እጅግ አስፈላጊ የምትሉት ምንድን ነው?

ጳውሎስ፣ ለእኛ በዓለም ትልቁ ነገር የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ማወቅ ነው ይላል *(ፊልጵስዩስ 3:7-10)::* ኢየሱስን ስንከተል በመከራና በችግር ውስጥ ማለፍ ሊኖርብን ይችላል:: ሆኖም፣ አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማይ ከእርሱ ጋር እንሆናለን::

አስታውሱ፣ ኢየሱስ ድካማችንን ያውቃል። በችግሮቻችን ወቅት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በልበ ሙሉነት ቀርበን የሚያስፈልገንን እርዳታ መቀበል እንችላለን *(ዕብራውያን 4:14-16)።*

ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ስፍራ ለመውሰድ ይፈልጋል። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ማሰብ ትተን ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ የራሳችንን መንገድ ስንከተል፣ ያን ጊዜ ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ ስፍራ ያገኛል። ከዚያ ብዙም ሳንቆይ እንደገና በኃጢአት እንጠመዳለን።

አሁን የምትኖሩበት ሕይወት እንዴት ያለ ነው? በሕይወታችሁ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲቆጣጠረው ያልፈቀዳችሁለት ስፍራ ካለ እርሱ ራሱ እንዲያሳያችሁ ለምኑት። ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ ያልሰጣችሁት ነገር ካለ አሁኑኑ ተናዘዙ። ለእግዚአብሔር ሊሆን ሲገባ ለሰይጣን የሰጣችሁት ስፍራ በሕይወታችሁ ካለ፣ እግዚአብሔር ይህን ይቅር ይላችሁ ዘንድ ተማጠኑት። ራሳችሁን ለኢየሱስ አሳልፋችሁ ስጡ። ከዚያም እርሱ የሕይወታችሁ ንጉሥና ጌታ እንዲሆን ፍቀዱለት።

# *IX. የሚገዙንን ኃጢአቶች ለይተን ማወቅና መቋቋም እንዴት እንደምንችል*

በየቀኑ ምን ማድረግ እንዳለብን ብዙ ምርጫዎች አሉን። «በክርስቶስ» ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን ነጻነት አለን። ለዚህም ሊረዳን የሚችል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለን። የእኛ ኃላፊነት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን ማድረግ ነው። ይህን የምናደርገው ደኅንነታችንን እናጣለን በሚል ሥጋት ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ለማክበርና የድል ሕይወትን ለመኖር ስለምንፈልግ ነው። ለዚህ የሚበቃ ከራሳችን የሆነ ብርታት የለንም *(ዮሐንስ 15:5)*፣ ነገር ግን «በክርስቶስ» ሁሉን ማድረግ እንችላለን *(ፊልጵስዩስ 4:13)።*

ልብ አድርጉ፣ ከአሁን ወዲያ ከሰይጣን ሥልጣን ሥር ወይም በእርሱ *መንግሥትም* ውስጥ አይደለንም። ያለነው በእግዚአብሔር *ሥልጣን ሥርና* በእግዚአብሔር *መንግሥት* ውስጥ ነው *(ቆላስይስ*

*1:13፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:18)::* መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ኃይል ይሰጠናል:: ይህም ኃይል ከሰይጣንና ከኃጢአት ኃይል በላይ ነው *(1ኛ ዮሐንስ 4:4)::*

ሰይጣን ውሸታምና አታላይ ነው፣ የሚሠራውም በጨለማና ጽድቅ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ነው:: እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፣ የሚሠራውም በብርሃንና በጽድቅ ውስጥ ነው:: የሰይጣን ኃይሉ ውሸት ነው:: የእግዚአብሔር ኃይል ግን በእውነት ውስጥ ነው:: ሰይጣን የሚሠራውን በቀላሉ ማየት ስለሚቻል አንዳንድ ሰዎች ታላቅ ኃይል ያለው ይመስላቸዋል:: እግዚአብሔር ግን ፍጹም ኃያልና ሁሉን አዋቂ ነው:: እንደዚሁም እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ድል አድራጊ ነው:: የእርሱ ኃይል ለሕይወትና እግዚአብሔርን እየመሰልን ለመኖር የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል *(2ኛ ጴጥሮስ 1:3)::* ትግላችን ተስፋ ቢስ ስላልሆነ በክርስቶስ ድልን መቀዳጀት እንችላለን::

ጦርነቱ የሚካሄደው በአእምሮአችን ውስጥ ነው:: መጥፎ አሳቦች እንዲሁም ፍርሃትና ጥርጣሬ ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ ስፍራ እንዲያገኝ ያደርጋሉ:: አሳቦቻችን ለክርስቶስ እንዲታዘዙ ማድረግ አለብን *(2ኛ ቆሮ. 10:5)::* ሰይጣን ግን የታሠርንና ነፃ መውጣት የማንችል እንደ ሆንን ሊያሳምነን ይፈልጋል:: እውነቱ ግን «በክርስቶስ» ነፃ መሆናችን ነው:: ስለዚህ ምርጫችሁ እውነትን ማመን ይሁን:: በዚህን ጊዜ የሰይጣንን ውሸት ማሸነፍ እንችላለን *(1ኛ ዮሐንስ 5:4-5)::* በሥልጣን መጸለይ እንችላለን - ማለትም በእውነትና በእግዚአብሔር ኃይል እንደቆምን እናውጃለን ማለት ነው:: *ከዚያም ጠላትን ለማሸነፍ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት እንጸልያለን::*

ቀጥሎ ሰይጣን አሳቡን እንድንፈጽም ሊያደርግ የሚችልባቸው ስምንት መንገዶች ቀርበዋል:: እነዚህ መንገዶች የሰይጣንን ውሸቶች እያጋለጡ ልንቆምበት የሚገባንን የእግዚአብሔርን እውነት ያሳዩናል:: ነጻነት የሚመጣው እውነትን ለማመን ስንመርጥ፣ ኃጢአታችንን ስንናዘዝና ስንተወው ነው::

ሰይጣንን በምንጋፈጥበት ጊዜ ድምፃችንን አውጥተን ምላሽ መስጠት አለብን:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ሰይጣን በአሳቦቻችን ውስጥ፣

እንደዚሁም በምናየውና በሚሰማን ነገር ውስጥ ሊሠራ ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ አሳቦቻችንን ሊያውቅ አይችልም:: ሁሉንም ነገር የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

## *1. ባሕሎች (ወጐች)*

ባሕሎች ወይም ወጐች የሚባሉት ከቀደምት አንጋፋ ቤተሰቦች ወይም አያት ቅድመ-አያት ስለ ሕይወት የተላለፉልን ትምህርቶች ናቸው:: ባሕሎች ወይም ወጐች የምንከተላቸው መመሪያዎች (ሕጎች) ናቸው:: እያንዳንዱ ባሕል የራሱ ዝርዝር ደንቦች (ወጐች) አሉት::

*አንዳንድ ባሕሎች ጠቃሚዎች ናቸው::* ለምሳሌ፣ የዛምቢያ ሰዎች ለእንግዶች መልካም መስተንግዶ ማድረግ ያውቃሉ:: የዛምቢያ የጋብቻ ባሕሎች በጣም ጥሩዎች ነበሩ:: ከተወሰኑ ዘመናት በፊት አንድ ወንድ ድንግል ያልሆነችን ልጅ አያገባም ነበር:: ጋብቻ ታላቅ ክብር ይሰጠው ነበር:: በአሁን ጊዜ ይህ ጥሩ የጋብቻ ባሕል የቀረ ይመስላል::

ሰዎችን በፍርሃት ውስጥ እንዲኖሩ ስለሚያደርጉ፣ *ሌሎች ባሕሎች ደግሞ መጥፎዎች ናቸው::* ሰዎች አንድ ሥርዓትን ካልጠበቁ መጥፎ ነገር ይደርስብናል ብለው ይፈራሉ:: ባሕሉ ጠቃሚ አለመሆኑን ቢያውቁትም ከፍርሃት የተነሣ ያደርጉታል::

*ምሳሌዎች*

1. አንዳንድ ሰዎች መድኃኒት የተቋጠረበት ማተብ በልጆቻቸው አንገት ያስራሉ:: ሌሎች ደግሞ በቆዳ የተሰፋ መድኃኒት በልጆቻቸው ክንዶች ያጠልቃሉ ወይም በወገባቸው ላይ ዶቃ ያስራሉ:: እንዲህ በማድረጋቸው እነዚህ ነገሮች ልጆቻቸውን ከበሽታ የሚከላከሉላቸው ይመስላቸዋል:: ክርስቲያኖች እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉት የእግዚአብሔርን ኃይል ስለሚጠራጠሩ ነው:: የልጆቻችን ሕይወት በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ነው:: እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል:: በእርሱ ኃይል እንድናምን ሰይጣን እነዚህን ሰንሰለቶች፣ ቆዳዎችንና ጨሌዎችን ይጠቀምባቸዋል:: ብዙ ሰዎች በእነዚህ ነገሮች መጠቀምን ማቋረጥ ይፈራሉ:: ይህ

ፍርሃት ከእግዚአብሔር የሚመጣ ፍርሃት አይደለም:: ፍርሃት ሁልጊዜ የሚመጣው ከሰይጣን ነው::

2. ከጋብቻ ጋር የተያያዙ በርካታ ባሕሎች አሉ:: ከአንድ ጐሣ የሆኑ የሁለት ሰዎች ጋብቻ እንደ መጥፎ ነገር ተደርጎ ይቆጠር ነበር:: ከአንድ ጐሣ የሆኑ ከተጋቡ ልጆችን ሊወልዱ እንደማይችሉ ወይም የወለዷቸው ልጆች እንደሚሞቱባቸው ይታሰባል::
3. መጥፎ ነገር እንደሚደርስባቸው በማሰብ፣ አንዳንዶች እንደ ዶሮና እንቁላል ያሉ ምግቦችን አይበሉም::

እነዚህን የመሳሰሉ ባሕሎች *ሰዎችን ፈሪዎች እንዲሆኑ* ያደርጋሉ:: እንድንፈራ የሚያደርጉን ባሕሎች በሙሉ ሊወገዱ ይገባል:: ምክንያቱም ይህን መሳይ ፍርሃት በእግዚአብሔር እንዳንተማመን ደርጋል:: ፍርሃት የሚያስፈንና ሰይጣን በእኛ ውስጥ እንዲሠራ በር የሚከፍት ነው:: በክርስቶስ ነፃ የወጣን ስለሆንን፣ ክርስቲያኖች እንዲህ ያሉ ነገሮችን በፍጹም መፍራት የለብንም:: ከሰይጣን የሆኑ ነገሮች በእኛ ላይ ሥልጣን የላቸውም:: በእግዚአብሔር እውነት ማመንን መማር አለብን፣ ምክንያቱም ነፃ የሚያወጣን ይህ እውነት ነው:: እግዚአብሔር በፍጹም የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንም:: ይልቁኑ እርሱ የሚሰጠን የኃይል፣ የፍቅርና ራስን የመግዛት መንፈስ ነው:: የምንጠበቀው በእግዚአብሔር ፍቅር ነው:: ይህ ፍቅሩ ደግሞ ፍርሃትን ከውስጣችን ያስወግድልናል *(2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7፤ 1ኛ ዮሐንስ 4:16፣ 18)::*

ሌሎች ባሕሎች *በቀጥታ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የሚያምጹ ናቸው::* ኢየሱስ ይህን *በማርቆስ 7:8-13* ባለው ክፍል፣ «ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል:- ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፣ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ::» በማለት በግልጽ ተናግሯል::

ኢየሱስ በ«ቁርባን» ሕግ ምሳሌ ተጠቅሞአል:: ይህ ሕግ እንደሚገልጸው ለእግዚአብሔር ብቻ የተሰጠን ስጦታ በሌላ መንገድ መጠቀም አይቻልም:: ነገር ግን በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ሰዎች

ቤተሰቦቻቸውን ላለመንከባበከብ በመፈለጋቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው መስጠት የነበረባቸውን ገንዘብ ወይም ዕቃ የቁርባን ነው በማለት ይከላከሉ ነበር:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስጦታን የማቅረብ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሆኖ የተጀመረው ሂደት ቤተሰብን ላለመንከባከብ ማመካኛ ሆኖ ቀረ:: እግዚአብሔር ቤተሰቦቻችንን እንድንከባከብ ተናግሯል:: ፈሪሳውያን ግን ይበልጥ የሚያስደስታቸው የቁርባን ሕግ ነበር:: የቁርባንን ሕግ በመጠበቅ የእግዚአብሔርን ሕግ ያፈርሱ ነበር::

*ምሳሌዎች:-* ሰዎች በሚሞቱበት ወቅት ብዙ ዓይነት የባሕል ሁኔታዎች አሉ:: በተለይም ሴት ባሏ በሚሞትበት ጊዜ የሚፈጸሙ ብዙ ባሕሎች ነበሩ:: ይህም የሴትዮዋ ባል በሚሞትበት ወቅት አብዛኛ ውን ጊዜ የባል ዘመዶች ይመጡና በቤት ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር በመውሰድ ሚስቱንና ልጆቹን በድህነት ውስጥ ጥለዋቸው ይሄዳሉ:: አንዳንድ ክርስቲያኖችም እንኳ ይህንን ክፉ ነገር ያደርጋሉ ሆኖም፣ ይህ ድርጊት *ንጥቂያ* ነው:: በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ባልና ሚስት አንድ ናቸው፣ የባል ንብረት የሚስቲቱም ነው::

አንዳንድ ጊዜ የባል ዘመዶች በሚስቲቱ ላይ ሌሎች ችግሮችን ያስከትላሉ፣ እንዲያውም ባሏ እንዲሞት ያደረገችው እርሷ ነች በማለት ይወነጅሏታል:: ሆኖም፣ ይህ ድርጊት የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሳየት አይደለም:: እግዚአብሔር የሚለው ዘመዶቻችሁን ውደዱ ነው:: እኛ ግን በሚሞቱበት ጊዜ የምንጠላቸው እንመስላለን:: እንዲያውም አንዳንድ ክርስቲያኖች ባል የሞተባትን ሴት የ«ባሕላዊ መንጻት» ሥርዓትን እንድትከተል ይገፋፋሉ:: ይህ ባሕል ባል የሞተባት ሴት «አታመንዝር» የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንድትተላለፍ ያደርጋታል:: የ«ባሕላዊው መንጻት» ሥርዓት መሠረቱ የሞተው ሰው (የባልየው) መንፈስ በሚስቲቱ ውስጥ በመቅረት ችግር ይፈጥራል የሚል ፍርሃት ነው:: ክርስቲያኖች መፍራት የለባቸውም:: ከሰይጣን ኃይል ይልቅ ኃያል በሆነው በእግዚአብሔር ኃይል ውስጥ ደኅንነታቸው የተጠበቀ ነው::

*ገላትያ 1:13-14፣* ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ አስቀድሞ የአባቶቹን ባሕል ወይም ወግ አጥብቆ ይከተልና ይጠብቅ ነበር:: በደማስቆ

መንገድ ላይ ኢየሱስ ከተገለጠለት በኋላ ግን እነዚህን ወጎች በሙሉ ትቶ የእግዚአብሔርን መንገድ ተከተለ:: *በገላትያ 4:9* ላይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጠይቃል:- «አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደገና ወደ ደካማ ወደሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? እንደገና *ባሪያዎች* ሆናችሁ ዳግመኛ ለዚያ ልትገዙ ትወዳላችሁን?»

*ቆላስይስ 2:8፣20-22* ላይ፣ ከእግዚአብሔር ጥበብ ይልቅ በሰው ጥበብና በዓለም መርሆች ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ፣ አንዳንድ ባሕሎች ከዓለም ነገሮች ላይ እንደሚያጠላልፉን ተጽፏል:: ምክንያቱም በምናደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልግ በክርስቶስ አዲስ ልብ ስላለን እነዚህን ባሕሎች መተው እንችላለን፣ መተውም ይኖርብናል::

*1ኛ ጴጥሮስ 1:18-19* ላይ፣ እንደተጻፈው ክቡር የኢየሱስ ደም ከአባቶቻችን ከወረስነው ከከንቱ ኑሮአችን ዋጅቶናል (ነፃ አውጥቶናል)::

አንድ ባሕል ጥሩ ወይም መጥፎ መሆኑን ማወቅ ስትፈልጉ ልትጠይቁ የሚገባችሁ *ሁለት ጠቃሚ ጥያቄዎች* ቀጥለው ቀርበዋል::

1. *እንድፈራ ያደርገኛል?* ባሕሉን ሳላደርግ በመቅረቴ ፍርሃት ከተሰማኝ፣ መጥፎ ባህል መሆኑን አውቄአለሁና ያን መጥፎ ባሕል መተው አለብኝ::

2. *የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንድተላለፍ ያደርገኛል ወይ?* የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳልታዘዝ የሚያደርግ ነገር ከፈጸምሁ፣ ያ ነገር መጥፎ ስለሆነ መተው ይገባኛል::

ከእግዚአብሔር ሕግጋት ይልቅ የሰዎችን ወግ የምትከተሉባቸው ሁኔታዎች በሕይወታችሁ ውስጥ ይገኛሉን? ከፍርሃት የተነሣ የታሰራችሁባቸው ነገሮች አሉን? እነዚህን ነገሮች በግልጽ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ:: እነዚህን ነገሮች ለመተው መንፈሱ ብርታትን እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ::

*ጸሎት:-* የሰማይ አባት ሆይ፣ እንድፈራና የአንተን የጽድቅ ትእዛዛት እንዳልታዘዝ ከሚያደርጉኝ የቀደምት አባቶቼ ባሕሎች፣

በክቡር የኢየሱስ ደም ነፃ እንዳወጣኸኝ አውቃለሁ:: በ --------- የታሠርሁ መሆኔን እናዘዛለሁ:: ከእነዚህ ነገሮች ለመላቀቅ እፈልጋለሁ:: እነዚህን ነገሮች ለመተው ብርታት እንዳገኝ እባክህ የመንፈስህን ኃይል ስጠኝ::

## 2. ጥንቆላ

የጥንቆላ ኃይል ከሰይጣን የሚመጣና የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይል የሚክድ ነው:: ዛሬም ሆነ ከዚህ በፊት ከእነዚህ ሰይጣናዊ ድርጊቶች ጋር ግንኙነት ከነበራችሁ ሰይጣን ሕይወታችሁን እንዲያበላሽ ትልቅ ዕድል ሰጥታችሁታል ማለት ነው:: ስለዚህ ይህን ግንኙነታችሁን በማውገዝ አሁኑኑ ማቋረጥ ተገቢ ነው::

ከዚህ የጥንቆላ ባለሙያ ጋር ግንኙነት ያለው ወይም ከጠንቋይ ጋር ንክኪ ያለው የሕይወታችሁ ክፍል ካለ እግዚአብሔር ይህን እንዲያሳያችሁ በጸሎት ጠይቁት::

ከዚህ በታች ያለውን ዝርዝር እስቲ ተመልከቱ:: ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ ከየትኞቹ ጋር ግንኙነት ነበራችሁ? ይህን የጥንቆላ ሥራ በስፍራው ተገኝታችሁ ከተመለከታችሁ ወይም ጠንቋዩ ባለበት ስፍራ ተገኝታችሁ ከሆነ፣ ሰይጣን በሕይወታችሁ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግባችሁ ይችላል::

*ዘዳግም 18:9-12* ላይ - ልጅን በእሳት ስለ መሠዋት፣ ሙዋርተኝነት፣ ሞራ ገላጭነት፣ አስማተኝነት ስለ ድግምተኝነት፣ ስለ መናፍስት ጠሪነት ወይም ሙታንን አነጋጋሪነት ተጽፎአል::

*ቁጥር 12* እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው «በጌታ ፊት የተጠላ ነው» ይላል::

*ኢሳይያስ 47:12-15* አስማቶችን - መተቶችን የሚያደርጉ - የሰማይን ከዋክብት የሚቆጥሩ - ከዋክብትንም የሚመለከቱ:- እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ በእሳት እንደሚበሉ ገለባዎች እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ያስጠነቅቃል:: በስሕተታቸው የሚቀጥሉ በመሆናቸው ራሳቸውንም ሆነ ማንንም ሊያድኑ አይችሉም:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሰይጣን ውሸቶች ናቸው::

*ኢሳይያስ 57:3-13* ላይ ስለ አስማት ይናገራል *(ቁጥር 3)* - ይህ አስማት አስማተኛው የሚያደርገውን ተግባርና የሚጠቀምባቸውን መድኃኒቶች ያካትታል::

- ለጣዖታት የሚቀርቡ የመጠጥና የእህል ቁርባን *(ቁጥር 6)*

- ከመዝጊያውና ከመቃኑ በኋላ የሚደረግ ክታብና የሚንጠለጠሉ ነገሮች ወይም ምልክት *(ቁጥር 8)*

*በቁጥር 4* ላይ እነዚህን ሰዎች «የዓመፅ ልጆችና የሐሰት ዘር» ይላቸዋል::

*በቁጥር 12* እግዚአብሔር «ጽድቃችን» የሚሉትን (ሆኖም በትክክለኛው የዓመፅ ሥራ የሆነውን) ሥራቸውን እንደሚያጋልጥና እነርሱም እነዚህ ነገሮች የማይጠቅሙአቸው እንደሆኑ እንደሚገነዘቡ ይናገራል::

*በቁጥር 13* ላይ ለእርዳታ በሚጮኹበት ጊዜ የሰበሰቡአቸው ጣዖታት እንደማይታደጉአቸውና ነፋስም እንደሚወስዳቸው እግዚአብሔር ይናገራል::

*ሕዝቅኤል 13:18-23* ስለ ምዋርቶች ይናገራል::

*ቁጥር 18፣* ሰዎች እነዚህን ነገሮች ሌሎችን ለማጥመድ እንደሚጠቀሙባቸው ያስረዳል::

*ቁጥር 19፣* እነዚህን ሟርቶች የሚጠቀሙ ሰዎች ይዋሻሉ፣ ይገድላሉም::

*ቁጥር 20-* እግዚአብሔር እነዚህን ሟርቶች ይቃወማል፣ ከክንዳቸውም ላይ ያራግፋቸዋል:: በእነዚህ ነገሮች የተጠመዱትን እግዚአብሔር ነፃ ለማውጣት ይፈልጋል::

*ቁጥር 22-* እነዚህ ሰዎች ጻድቁን በውሸታቸው ተስፋ እንዲቆርጥ ያደርጋሉ፣ ክፉዎችን ደግሞ በክፉት መንገዶቻቸው እንዲቀጥሉ ያበረታቱአቸዋል::

*ሚልክያስ 3:5* እግዚአብሔር በመተተኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል::

*የሐዋርያት ሥራ 8:9-13፣* መተተኛው ስምዖን፣ ባሳየው «ትልቅ ኃይል» ተከታዮችን አፍርቶ ነበር:: ይሁንና የእግዚአብሔር ኃይል

ከእርሱ ኃይል እንደሚበልጥ ተገነዘበ:: ስለሆነም ስለዚህ ኃይል የበለጠ ለማወቅ ፊልጶስን ተከተለው:: የሚያሳዝነው ግን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በገንዘቡ ለመግዛት ማሰቡ ነበር:: ጴጥሮስ *በሐዋርያት ሥራ 8:18-23* ለስምዖን የተናገረውን አንብቡ::

የሐዋርያት *ሥራ* 13:6-12 ኤልማስ (በርያሱስ) የተባለ ጠንቋይ ሰዎችን ከክርስቶስ እምነት ወደ ኋላ ለመመለስ ይጥር ነበር:: ጳውሎስም ትኩር ብሎ ተመልክቶት፣ *«አንተ ተንኮል ሁሉ፣ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፣ የዲያብሎስ ልጅ፣ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፣ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን?»* አለው:: *እግዚአብሔርን ስለ ተቃወመ በእውርነት ተቀጣ::*

*ራእይ 21:8* «የአስማተኞችና ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛ ዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው::»

*መተት* ወይም ጥንቆላ በሰዎች ላይ *ታላቅ* ፍርሃትን *ያስከትላል*:: ከዚህ ፍርሃት የተነሣ ሰዎች በእርሱ *ታሥረው* ለመላቀቅ ይሳናቸዋል:: ፍርሃት ሁሌም የሚመጣው ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም *(2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7፤ 1ኛ ዮሐንስ 4:16፣ 18)*:: ፍርሃትን በመቃወም ወደ እግዚአብሔር ልንመለስና የእርሱም እርዳታ ከእኛ ጋር እንደ ሆነ ማወጅ አለብን::

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ስታነቡ፣ የተጠቀሱት ሰይጣናዊ ተግባራት አሁን ያሉትን ቀድሞም የነበሩትን አሁኑኑ በመናዘዝ፣ እያንዳንዱን ከእነዚህ ልምዶች ጋር ያላችሁን ግንኙነት ለመተው የሚከተለውን ጸሎት ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጸልዩ:: ይህንኑ ጸሎት ደጋግማችሁ በመጸለይ እያንዳንዱን ልምምድ አውግዙት::

> *ጸሎቱ:- ጌታ ሆይ፣ በ---------- ውስጥ ተሳታፊ የነበርኩ መሆኔን እናዘዛለሁ:: በ---------- ልምምድ ውስጥ በማለፌ ይቅርታህን እጠይቃለሁ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ይህንን ልምምድ ላልደግም ጥዬዋለሁ::*

የጥንት ክርስቲያኖች በሐዋርያት *ሥራ 19:18-19* በተጻፈው መሠረት ያደረጉትን ልብ በሉ:: በኢየሱስ ክርስቶስ በአመኑበት ወቅት

ክፉ ድርጊቶቻቸውን በገሃድ ተናዘዙ:: የመተትና የአስማት ተግባር ያካሄዱ የነበሩ ሁሉ የመተትና የአስማት ማካሄጃ መሣሪያዎቻቸውን በሕዝብ ፊት አምጥተው በማቃጠል ይህንን ልምምድ መተዋቸውን በገሃድ አሳዩ:: እናንተም ከጠንቋዮች ወይም ከአስማተኞች ተቀብላችሁ በቤታችሁ ውስጥ ያስቀመጣችኋቸው ነገሮች ወይም መድኃኒት ካለ አሁኑኑ አውጥታችሁ መጣል አለባችሁ:: ማሰብ ያለባችሁ ከእነዚህ የሰይጣን ነገሮች ትንሽ የተባለውን አንድ ነገር እንኳን ብታስቀሩ፣ በዚያ ሳቢያ ሰይጣን በሕይወታችሁ ውስጥ እንዲሠራ ስለምትፈቅዱለት፣ ከእርሱ የተላቀቃችሁ አይደላችሁም::

*ቀጥሎ የተጻፉት ጠቃሚ ቃላት ሲሆኑ፣ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ተናገሩ:: የመተትን ወይም የአስማትን ነገር ሁሉ አልቀበልም:: ከሰይጣን የሚመጣ ነገርን ጨርሶ አልቀበልም:: በኢየሱስና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ እተማመናለሁ:: እኔ የእግዚአብሔር ነኝ:: የኢየሱስ ደም ያነጻኛል:: በዋጋ ተገዝቻለሁ::*

በቤታችሁ ውስጥ የጥንቆላ ወይም የመተት መገልገያ ዕቃዎች ካሉአችሁ ይህን የሚከተለውን ጸሎት ጸልዩ:-

*የሰማዩ አባቴ ሆይ፣ እኖርበት ዘንድ ይህን ቤት ስለ ሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ:: ይህ ቤት ከማንኛውም የሰይጣን ተጽዕኖዎች ነፃ እንዲሆን ፍላጐቴ ነው:: እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ የአንተ ልጅ ነኝ:: ሰይጣንና አጋንንቱ ሁሉ ይህን ቤት ለቅቀው እንዲሄዱ በኢየሱስ ስም አዝዛቸዋለሁ:: ዳግመኛ ወደዚህ አይመለሱ:: ጌታ ሆይ፣ መላእክትህ ይህን ቤት ከብበው ከሰይጣን ከሚመጣ ክፉ ነገር ሁሉ እንዲጠብቁት ታደርግ ዘንድ እለምንሃለሁ:: እኔን እንደምትንከባከብ ስለማውቅ አመሰግንሃለሁ::*

### 3. ከዘር የሚተላለፍ ውቃቢ፣ የሙታን መናፍስት፣ ማሟረት ወይም እርግማን

በርካታ ሰዎች የሞቱ ዘመዶቻቸው መናፍስት ሊያስቸግሯቸው እንደሚችሉ ያምናሉ:: አንድ ዘመድ የሆነ ሰው በሕይወት ሳለ ተገቢ እንክብካቤ ከተነፈገው፣ መንፈሱ ተመልሶ መጥቶ በሕይወት ያሉ ዘመዶቹን ማሠቃየትና መጉዳት ይችላል ብለው ያምናሉ:: የሞተው

ሰው መንፈስ ችግር የሚያስከትልባቸው ስለሚመስላቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የሞተ ሰው አስከሬን ማጠብ ይፈራሉ:: ሌሎች ደግሞ ሰው በሞተበት ቤት መኖር አይፈቅዱም:: ይህን የሚያደርጉት መንፈሱን ስለሚፈሩ ነው:: አንዳንዶቹ ደግሞ ለመንፈሱ ምግብ በማቅረብ የሟች ዘመድ መንፈስ እንዲረዳቸው ለማድረግ ይሞክራሉ:: ሌሎች ደግሞ የሙታንን መናፍስት ስለሚፈሩ መካነ መቃብርን አቋርጠው መሄድ አይፈልጉም:: የሞተው ባላቸው መንፈስ ተመልሶ መጥቶ ጉዳት የሚያደርስባቸው ስለሚመስላቸው፣ አንዳንድ ሴቶች ባሕላዊውን የመንጻት ሥርዓት ካልፈጸሙ ሥጋት ያድርባቸዋል::

ጂ ቫን ሪነን የተባለ ደራሲ *«Communicating Christ In Animistic Contexts»* (በባሕላዊ እምነት ዓውድ ውስጥ ለሚገኙ ክርስቶስን ማስተዋወቅ)፣ በሚለው በእንግሊዘኛ የተጻፈ መጽሐፋቸው ውስጥ ብዙዎች የሚያምኑትን እንደሚከተለው ይገልጻሉ:-

> ከቁሳዊ ዓለም በሞት የተለዩ ቢሆኑም፣ በሞት የተለዩ ቤተ ዘመዶች አሁን በሕይወት ካሉት ዘመዶቻቸው የበለጠ ኃይል ስላላቸው በምድር ላይ በሚኖሩ ዘመዶቻቸው ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል:: እነዚህ ቀደምት ሙታን የቤተ ዘመድ አባላት በሕይወት በነበሩ ጊዜ የደረሰባቸውን በደል መበቀል ይፈልጋሉ:: የእነዚህ የሙታን ቤተ ዘመድ መናፍስት በሕይወት በምድር ላይ ካሉ ዘመዶቻቸው ጋር በቀጥታ በሕልምና በሕይወት ባሉት ውስጥ በመንፈስ በመግባት በተዘዋዋሪ መንገድ ደግሞ በበሽታ አማካይነት ይገለጡላቸዋል:: አፍሪካውያን ብዙውን ጊዜ ሕመምን ለሕይወት ሲሉ እንክብካቤ ያልተደረገላቸው ሙታን አባቶች እንደሚላክ ቁጣ፣ ወይም ማኅበራዊ ሥነ ምግባርን ባለመጠበቁ በታመመው ሰው ላይ እንደ መጣበት አድርገው ያስባሉ:: አፍሪካውያን አሁንም ሙታን በመንፈስ እንደሚኖሩ በጥልቀት ስለሚያምኑ፣ ሙታንን ችላ ማለት በሕይወት ያሉትን ሰዎች ከመበደል እኩል እንደ ሆነ ይረዳሉ::

የሙታን መናፍስትን ስለ መጥራት *(ዘዳግ. 18:11፤ ኢሳ. 8:19)* በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን አስታውሱ:: ስለ እግዚአብሔር

ብቁነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው አጠቃላይ ቃል ለሙታን ቤተ ዘመዶች መናፍስት የሚቀርበውን ልመናም ሆነ አምልኮ ይቃወማል:: ክርስቲያን ከእርሱ በፊት የነበሩትን ቀደምት ቤተ ዘመዶች የሚያከብር ቢሆንም፣ ሊያመልካቸው ግን ፈጽሞ አይገባም:: (አንዳች ነገር ያደርሱብኛል ብሎ ሊፈራቸውም አይገባም::) አንድ ክርስቲያን ፍጹም ታማኝነቱንና አክብሮቱን ሉዓላዊ ለሆነ አምላክ ብቻ ማድረግ ይገባዋል::

ይህ ደራሲ በመጽሐፉ በገጽ 299 ላይ ጨምሮ ሲገልጽ:-

> «እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን እስራኤልን <የተመረጠች ርስቱ አደረጋት> *(ዘጸአት 19:5)::* ስለዚህም እስራኤል የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ስለሆነ ሌሎች አማልክትን እንዲያመልክ ፈጽሞ አልተፈቀደለትም *(ዘጸአት 20:3)::* ሕዝቡ ሌሎች አማልክትን ባመለኩ ቁጥር እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ጊዜ ቀናተኛ አምላክነቱን ገልጾላቸዋል *(ዘጸአት 20:5፤ ዘዳግ. 32:16)::* በርካታ ክርስቲያኖች እንደ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እያመለኩ የራሳቸውንም ጣዖታት ያመልካሉ *(2ኛ ነገሥት 17:33)::* እዚህ ላይ ሊተኮርበት የሚገባው ራስን በታማኝነትና በታዛዥነት አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ ነው:: በባህል እምነት የተያዙ ሰዎች ትልቁ ኃጢአት በአንድ በኩል እግዚአብሔርን እያመለኩ በሌላ በኩል የሙታን መናፍስትና ጣዖቶቻቸው የዕለት ተዕለት ችግሮቻቸውን የሚያቃልሉላቸው ይመስል እነርሱን መማጠናቸው ነው::»

እግዚአብሔር አምላካችን ሁሉን ቻይ አምላክ ነው:: እርሱ ጻድቅና መሐሪ አምላክ ስለሆነ ከሕዝቡ ጋር ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል:: ሰዎች ከሙታን መናፍስት ጋር ግንኙነት የሚያደርጉትና መናፍስቱን የሚፈሩት እነዚህ መናፍስት ከእግዚአብሔር በላይ ኃይል አላቸው ብለው ስለሚያምኑ ነው:: የሞቱ ዘመዶቻችንን ሕልም በምናይበትም ጊዜ ሆነ ሙት መንፈሶቻቸው በአሳባችን ሲመጡ፣ ከመፍራታችን የተነሣ ከእነዚህ አስደንጋጭ ነገሮች እግዚአብሔር በኃይሉ አያድነን ይሆን? ብለን እንጠራጠራለን:: *በኢሳይያስ 8:19* ላይ እግዚአብሔር:- «ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ

ሙታንን ይጠይቃሉን» ይላል:: እንዲሁም ኢሳይያስ በመናፍስት የሚታመኑትን እነዚህን ሰዎች በጨለማ የሚራመዱ ናቸው ይላል:: በሙታን መናፍስት የሚተማመኑ ሰዎች የሚያምኑዋቸው መናፍስት ከእግዚአብሔር የበለጠ ጥበብ ያሉዋቸው ስለሚመስሉዋቸው፣ ከእግዚአብሔር የላቀ ክብር ይሰጧቸዋል::

*በመዝሙር 49:5፣15* ላይ እንደተገለጸው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለእኛ በተሰጠው በእግዚአብሔር ኃይል መታመንን መማር አለብን:: እኛ ክርስቲያኖች በሰይጣን ግዛት ውስጥ ወይም በሰይጣን ሥልጣን ሥር መኖራችን ቀርቷል:: ስለዚህ አሁን የምንገኘው በእግዚአብሔር መንግሥትና በእግዚአብሔር ሥልጣን ውስጥ ነው *(ኤፌሶን 1:18-21፣ መዝሙር 31:15፣ 20)::*

በሌላ በኩል ደግሞ የተታለሉ ሰዎች ሊረግሙዋችሁ ይሞክሩ ይሆናል:: አንድ ሰው «እኔ ረግሜሃለሁና ታመህ ትሞታለህ» ቢለን በቀላሉ ፍርሃት ሊሰማን ይችላል:: ይህ የፍርሃት ሁኔታ እንዲቀጥል ከፈቀዳችሁለት፣ በሕይወታችሁ ለሰይጣን ስፍራ ትሰጡታላችሁ፣ ክፉ ነገርም ሊደርስባችሁ ይችላል:: በክርስቶስ ያገኛችሁትን ማንነታችሁን ከዘነጋችሁ ሰይጣን በሕይወታችሁ ውስጥ መሥራቱን ይቀጥላል::

ሰይጣንና አጋንንቱ አሁንም እንደ ሠሩ ናቸው:: አንዳንድ ሰዎች የክፉ መናፍስትን ኃይል ሲጠቀሙ፣ ሌሎች ደግሞ *የተለያዩ የእርግማን ስልቶችን በመጠቀም ይሠራሉ::* ነገር ግን እንደ እነዚህ ያሉትን እርግማኖች ለመቋቋም የሚያስችል የክርስቶስ ሥልጣንና ጥበቃ እንዳላችሁ አስታውሱ:: በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰይጣንን ሥራና የሰዎችን እርግማን ሁሉ መቋቋምና ማፍረስ ትችላላችሁ:: በሕይወታችሁ ውስጥ ሰይጣን ሊሠራ የሚጥረውን ክፉ ነገር ሁሉ የሚያሸንፍ ኃይል በኢየሱስ ደምና ስም ውስጥ አለ:: *1ኛ ዮሐንስ 4:16፣18፤ 5:18፤ ራእይ 12:10-11ን አንብቡ::*

በክርስቶስ የተቀዳጃችሁትን ስፍራና የኢየሱስን ኃይል የራሳችሁ ለማድረግ የመናፍስትንና የእርግማንን ተጽዕኖ መቋቋም አለባችሁ:: የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችሁ ለሰይጣን የእግዚአብሔር መሆናችሁን አሳውቁ:: ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስጡ::

ከዚያም በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣንና በኢየሱስ ስም፣ እንዲሁም በኢየሱስ ደም ኃይል ሰይጣንና ርኩሳን መናፍስቱ እናንተ ካላችሁበት ስፍራ እንዲወገዱ እዘዙዋቸው::

*ጸሎት:- ጌታ ሆይ፣ የአንተ ስለሆንኩ አመሰግንሃለሁ:: በእኔ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሰይጣንና ከሌሎች መናፍስት ኃይል እንደሚበልጥ አውቃለሁ:: በምፈራበት ጊዜ እንዲያበረታኝ ያ ኃይል የራሴ እንደ ሆነ አውጃለሁ:: የሰይጣንን ተጽዕኖ በሙሉ እቃወማለሁ:: የሰይጣንን ሥራ አልቀበልም፣ እቋቋመዋለሁ:: የእግዚአብሔርን እውነት የራሴ እንደ ሆነ አውጃለሁ:: ሰይጣንና አጋንንቱንም ከእኔ እንዲርቁ አዛቸዋለሁ::*

## *4. ራስን ማሳት (ራስን ማታለል)*

*በመዝሙር 51:6* ላይ ዳዊት እግዚአብሔር «የውስጥ እውነትን» እንደሚፈልግ መገንዘቡን ጠቅሷል:: የሰይጣንን ውሸቶችና ማታለያዎች መገንዘብ ከፈለግን፣ የእግዚአብሔር እውነት የውስጠኛው እኛነታችን አካል መሆን ይገባዋል:: ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ባመነዘረ ጊዜ ድርጊቱን ለመደበቅ ሞከረ:: በመጨረሻም ባለቤቷን ኦርዮንን እንዲሞት ወደ ጦር ግንባር ላከው:: ከውሸት ጋር መኖርን ስለ መረጠ፣ ይህ ድርጊቱ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋረጠበት::ነገር ግን ስለ ኃጢአቱ እውነቱን አውጥቶ ከተናዘዘ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነቱ ታደሰ፤ነጻነትንም አገኘ:: ከዚያ በኋላ ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር:- «በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው::» *(መዝሙር 32:2)::* ውሸትን አስወግደን እውነትን ለመናገር የቆረጥን መሆን ይገባናል *(ኤፌሶን 4:25)::*

መጽሐፍ ቅዱስ ራሳችንን ልናታልል የምንችልባቸውን ብዙ ሁኔታዎች ይጠቅሳል::

*ራሳችንን የምናታልለው - - -*

*- - - ኃጢአት የለብንም በምንልበት ጊዜ ነው፤ (1ኛ ዮሐንስ 1:8፣ 10)::* ማንም ሰው ቢሆን ኃጢአት ሠርቻለሁ ብሎ መናገር አይወድም::

ነገር ግን እውነተኛ ንስሐ ማለት ኃጢአታችንን መቀበልና በእግዚአብሔር ፊት በደለኞች መሆናችንን ማመን ነው። አስረው የሚይዙንን እንዲህ ያሉትን የሥጋ ነገሮች በምንናዘዝበት ወቅት፣ ነፃ መሆን እንችላለን።

*- - - ምንም ሳንሆን ትልቅ ስንመስል (ገላትያ 6:3)።* ሌሎች ሰዎችን በመመልከት ብቻ እኛ ከእነርሱ እንደምንሻል ማሰቡ ቀላል ነው። «እንደዚህ ሰውዬ ጠጪ አይደለሁም። እንደዚያኛው ሰውዬ አልዋሽም» እንል ይሆናል። ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር የለብንም። ራሳችንን ማነጻጸር ያለብን ከኢየሱስ ጋር ነው *(ዮሐንስ 13:15)።* ኢየሱስ የኖረው እንዴት ነው? ኢየሱስ የእኛ ምሳሌ ነው። ራሳችንን ከኢየሱስ ጋር ብናነጻጽር ምን ያህል ከንቱዎች እንደ ሆንን ይገባናል።

*. . . የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን የሚናገረውን ሳንፈጽም ስንቀር (ያዕቆብ 1:22፤ 4:17)።* የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና መታዘዝ ይገባል። ሰምቶ አለመታዘዝ ውጤቱ አጥጋቢ አይሆንም።

*. . . በዓለም መለኪያ ራሳችንን አስተዋዮች አድርገን ስንገምት (1ኛ ቆሮንቶስ 3:18፣19)።* በሕይወታችሁ ሁሉ ታላላቅ ውሳኔዎችን የምትወስኑት እንዴት ነው? የራሳችሁን ማስተዋል ትከተላላችሁ? ወይስ ጓደኞቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን ለማስደሰት ትሞክራላችሁ? በዓለም መለኪያ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ወደ ችግር ይመራሉ። እግዚአብሔር የሚሰጠውን የማስተዋል ጥበብ ልንሻ ይገባናል።

*. . . የዘራነውን የማናጭድ ሲመስለን (ገላትያ 6:7-8)።* አንዳንድ ክርስቲያኖች ኃጢአታቸው በሚያስከትለው መዘዝ ምክንያት የሚሠቃዩ አይመስላቸውም። ኃጢአት በሠሩ ቁጥር ንስሐ መግባት የሚችሉ፣ እግዚአብሔርም ይቅር የሚላቸው ይመስላቸዋል። በእርግጥ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፣ ሆኖም ኃጢአታችን ከሚያስከትልብን መዘዝ የተነሣ እንሠቃያለን፤ የዘራነውን እናጭዳለን። አንድ ሰው ቢያመነዝርና ለኃጢአቱ ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል፣ ግን የምንዝርና ኃጢአት ሲፈጽም በኤድስ በሽታ ሊያዝ ይችላል። ለኃጢአታችን ይቅርታ ልናገኝ እንችላለን፣ ግን ኃጢአት ደግሞ

በሽተኞች ሊያደርገን ይችላል:: ምንጊዜም ቢሆን ኃጢአት ውጤት አለው::

*....መጥፎ ጓደኛ የማያበላሸን ሲመስለን (1ኛ ቆሮንቶስ 15:33፤ ምሳሌ 13:20)::* አንዳንዶች ክርስቲያኖች ካልሆኑ ጓደኞች ጋር ሁልጊዜ በአንድነት ቢውሉም በክፉ *ሥራቸው* ተባባሪዎች የማይሆኑ ይመስላቸዋል:: እንዲህ ባለው ሁኔታ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: ይህን በምናደርግበት ጊዜ ሰይጣን ደስ ይለዋል፣ ምክንያቱም ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር አብረው የሚውሉ ብዙም ሳይቆዩ እነርሱ የሚሠሩትን እንደሚሠሩ ስለሚያውቅ ነው:: በኃጢአተኞች መንገድ አብረን የምንራመድ ከሆነ፣ ብዙ ፈተናዎች ይደርሱብናል፣ ሰይጣንም በሕይወታችን እንዲሠራ መግቢያ እንሰጠዋለን::

በሕይወታችሁ ውስጥ እውነት ስለሆኑት ነገሮች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዲህ ብላችሁ *ጸልዩ:-*

> *ጌታ ሆይ፣ ራሴን በ--------------- እንዳሳትኩ አውቃለሁ:: ይቅርታ እንድታደርግልኝ እጠይቃለሁ:: እንዲሁም የአንተን እውነት ማወቅና መከተል እፈልጋለሁ::*

### *5. ይቅርታ የማያደርግ መንፈስ (መራራ መሆን)*

በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ሰውን ይቅር አለማለት ከሰይጣን ወጥመዶች መካከል አንዱ ነው *(2ኛ ቆሮንቶስ 2:10-11)::* ክርስቲያኖች ኢየሱስን ይበልጥ በመምሰል እንዳያድጉ ለማድረግ ሰይጣን በዚህ ዘዴ ይጠቀማል:: ተበድለን እያለን የበደሉንን ይቅር ብንል፣ በዚህ *ሥራችን* ሌሎች የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይረዳሉ:: እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዳለን እኛ ደግሞ ሌሎችን ይቅር ማለት አለብን *(ኤፌሶን 4:31፣32፤ ቆላስይስ 3:13)::* ሰዎች በእኛ ላይ በደል ቢሠሩ፣ ይቅርታ ልናደርግላቸው ይገባል:: አለበለዚያ የምሬት *ሥር* በውስጣችን እንዲያድግ እንፈቅዳለን *(ዕብ. 12:15)::*

ኒል አንደርሰን የተባለ ደራሲ *"The Bondage Braker"* (ዘ ቦንደጅ ብሬከር) በተባለ መጽሐፍ ላይ ይቅርታን በተመለከተ ትምህርታዊ የሆኑ አሳቦችን አቅርበዋል:-

*«ይቅርታ ማለት መርሳት ማለት አይደለም:: ለመርሳት የሚሞክሩ ሰዎች መርሳት እንደማይችሉ በኋላ ይገነዘባሉ:: እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአታችንን ዳግም እንደማያስብ ይናገራል (ዕብራውያን 10:17):: ነገር ግን እግዚአብሔር በባሕሪው ሁሉን አዋቂ እንደ መሆኑ ሊረሳ አይችልም:: ኃጢአታችንን ዳግም አያስብም፣ አያስታውስም ማለት እግዚአብሔር ያለፈውን ኃጢአት ወይም በደል እኛን ለመጉዳት አይጠቀምበትም ማለት ነው (መዝሙር 103:12):: መርሳት ወይም ደግሞ አለማሰብ የይቅርታ ውጤት ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ ይቅርታ የማድረጊያ መንገድ ሊሆን አይችልም:: ያለፈውን ድርጊት እስታውሰን ለሰዎች የምንናገር ከሆነ፣ ለሰዎቹ ይቅርታ አላደረግንላችሁም ማለታችን ነው::*

*ይቅርታ ፈቃድን የሚፈትን ምርጫ ነው:: እግዚአብሔር ይቅር እንድንል ስለሚፈልግ እኛም የምናደርገው ተግባር ነው:: ይሁንና ይቅርታ ከእኛ የፍትሕ አስተሳሰብ ጋር ስለማይጣጣም ይቅር ማለት ይከብደናል:: ስለዚህ ስለተፈጸመብን ግፍ መበቀል እንፈልጋለን:: ዳሩ ግን እኛ ራሳችን ፈጽሞ እንዳንበቀል ታዘናል (ሮሜ 12:19-21)::»*

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ በሚበድሉን ሁሉ ሊፈርድባቸው ይችላል:: እኛ ልናደርገው የማንችለውን እርሱ ፍትሐዊ ብድራቱን ይከፍላቸዋል:: ይቅርታን በተመለከተ ዳዊት መልካም ምሳሌ ነው:: በዳዊት ላይ ስለ ቀናበት ሳዖል በዳዊት ላይ ተቆጣ:: ሳዖል ሊገድለው ሞከረ:: ዳዊት ግን ሳዖልን ለመግደል ዕድል ባጋጠመው ጊዜ፣ መበቀል ትክክል አለመሆኑን ስላወቀ ሊበቀለው አልፈለገም *(1ኛ ሳሙኤል 24:10፣ 12)::*

አንደርሰን አሁንም በመቀጠል እንዲህ ይላሉ:-

*«ሰዎችን ይቅር የምትሉት ለእነርሱ ብቻ ብላችሁ ሳይሆን፣ እናንተም ነፃ መሆን እንድትችሉ ለራሳችሁ ብላችሁ ነው::* ይቅርታ ማድረግ በእናንተና በበዳያችሁ መሀል ያለ ጉዳይ ሳይሆን፣ በእናንተና በእግዚአብሔር መሀል ያለ ጉዳይ ነው::

ይቅርታ ማለት ሌሎች ሰዎች ከፈጸሙባችሁ በደል ውጤት ወይም ጠንቅ ጋር ለመኖር መስማማት ማለት ነው። ይቅርታ ዋጋ የሚከፈልበት ድርጊት ነው። ስለዚህ ለተፈጸመብን ክፉ ምግባር ዋጋ እንከፍልበታለን። ብትወዱም ባትወዱም ከደረሰባችሁ በደል ውጤት (ጠንቅ) ጋር ትኖራላችሁ። እዚህ ላይ የሚኖራችሁ አማራጭ፣ በደላችሁን ተቀብላችሁ በይቅርታ መንፈስ በነፃ በመኖር ወይም በበቀል መንፈስ ይቅር ሳትሉ በመኖር መካከል መምረጥ ነው። ኢየሱስ እናንተን ይቅር ያላችሁ በዚህ ሁኔታ ነው። የኃጢአታችሁን ውጤት ወይም ጠንቅ በራሱ ላይ ተሸከመ።»

ኢየሱስ ስለ ዓለም ሁሉ ኃጢአት ሞተ። ኢየሱስ በመስቀል ሲሠቃይ በነበረበት ጊዜ ምን አለ? *(ሉቃስ 23:34)*። «የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ፣ ይቅር በላቸው» ነበር ያለው። ስለዚህ ኢየሱስ ለዋለልን ውለታ እርሱን ማመስገንና ማወደስ በአንጻሩ ደግሞ የበደሉንን ሰዎች «ኢየሱስ ይቅር እንዳለኝ፣ እኔም ይቅር ልልህ እወዳለሁ» ማለት ይገባናል። ይህን ማድረግ እውነተኛ ድል ይሆናል። ምሬትን በመቃወም ፍቅርንና ይቅርታ ማድረግን መርጠናል ማለት ነው።

አንደርሰን አስተያየታቸውን በመቀጠል:-

> *«ከልባችሁ ይቅር የምትሉት እንዴት ነው? ከልባችሁ ይቅር የምትሉት በመጀመሪያ ጉዳታችሁንና ጥላቻችሁን ይፋ አውጥታችሁ ስታስታውቁ ነው።* የምትሰጡት ይቅርታ ከልባችሁ ውስጥ ያልፈለቀ ከሆነ የተሟላ አይሆንም። ክርስቲያኖች እርስ በርስ በምናደርገው መጉዳዳት ውስጣችን ይቆስላል። ግን ይፋ አውጥተን በደላችንን አንናገርም። እግዚአብሔር ይህን በውስጣችን የተቀበረ የበደል ቂም ይፋ አውጥቶ መፍትሔ ይስጠው። ፈውስ ሊገኝ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

*ይቅርታ ማድረግ እስከሚሰማችሁ ድረስ አትጠብቁ- ይህን መሳዩ ስሜት ላይመጣ ይችላል::* ይቅርታ ለማድረግ ከወሰናችሁ በኋላ እንኳ የተበደለው ስሜት ለመፈወስ ሰይጣንም ይዞት የነበረውን እስኪለቅ ጊዜ ይወስዳል *(ኤፌ. 4:26፣ 27)::»*

ምናልባት አንድን ሰው ይቅር ካላችሁት በኋላ እንኳ ይህ ሰው በእናንተ ላይ በደል *መሥራቱን* ይቀጥል ይሆናል:: በዚህን ጊዜ *ታዲያ ምን ታደርጋላችሁ? በማቴዎስ 18:21* ላይ ጴጥሮስ፣ «ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?» ብሎ ነበር:: የኢየሱስ መልስ ግን *(ቁጥር 22)*፣ «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት!» የሚል ነበር:: እንዲህ ማለት ሰዎች የፈለገውን ያህል ቢበድሉንም፣ እኛ ግን ይቅርታ መስጠቱን መቀጠል አለብን ማለት ነው:: *ማቴዎስ 18:23-35ን* በተጨማሪ አንብቡ::

*1ኛ ዮሐንስ 4:20-21* ወንድሙን የማይወድና ይቅር የማይለው ማንም ሰው እግዚአብሔርን አይወድም ይላል:: ወንድሞቻችንን ይቅር ማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሳያ አስደናቂ መንገድ ነው:: ምናልባት ይህን ፍቅራችንን ሲመለከቱና ይቅርታችንን ሲቀበሉ፣ ያለፈውን መንገዳቸውን መለወጥና ወደ እግዚአብሔር መምጣት ይፈልጉ ይሆናል::

*ማቴዎስ 6:12፣14-15፣* ሌሎችን ይቅር ማለት በማንፈልግበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ይቅር ልትለን አይገባህም ብለን እንደ መንገር ነው::

*ማርቆስ 11:25* ይቅርታ የማያደርግ መንፈስ ይዘን መጸለይ አንችልም:: ኢየሱስ፣ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርብን ከመጸለያችን በፊት ይቅር እንድንል፤ ያን ካደረግን ደግሞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደምንቀበል ገልጿል::

የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል ብቃት ያለው ማንም የለም:: ስለዚህ በኃጢአታችን የተፈረደብን ነን:: ነገር ግን እግዚአብሔር ከፍቅሩና ከምሕረቱ የተነሣ ይቅር ብሎናል:: እኛም ለሌሎች ተመሳሳይ ፍቅር፣ ምሕረትና ይቅርታ ልናሳይ ይገባናል:: *ምሳሌ 10:12* አንብቡ:: ፍቅር በደልን ሁሉ ይሸፍናል::

*ጸሎት፡-* የሰማይ አባቴ ሆይ፣ ሁልጊዜ ይቅር ልትለኝ ፈቃደኛ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ፡፡ ሁልጊዜም ትታገሠኛለህ፡፡ ይህንኑ ትዕግሥትና ፍቅር እኔም ለሌሎች አሳይ ዘንድ እርዳኝ፡፡ ይቅር ያላልኳቸውን ሰዎች እንዳስታውስ እርዳኝ፡፡ በልቤ ውስጥ ምሬት እንዲኖር ስለማልፈልግ ይቅርታ ላደርግላቸው እፈልጋለሁ፡፡

ይቅርታ የምታደርጉላቸው ሰዎች ስሞች ትዝ ሲሉአችሁ፣ የስም ዝርዝራቸውን ጻፉ፡፡

ብዙውን ጊዜ የገዛ ራሳችንን ይቅር ማለት ይገባናል፡፡ ምናልባት የከፋ ነገር ታደርጉና እግዚአብሔር ይቅር የማይላችሁ መስሎአችሁ ለገዛ ራሳችሁ ይቅርታ ማድረግ ይከብዳችኋል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ምንጊዜም ይቅር ስለሚላችሁ፣ እናንተም ራሳችሁን ይቅር ማለት ይገባችኋል፡፡

ራሳችሁን ይቅር ማለት የእግዚአብሔርን የማንጻትና የይቅርታ ተግባር መቀበል ነው፡፡

ከምሬት መንፈስ ነፃ እንድትሆኑ አሁን በዝርዝራችሁ ውስጥ የጻፋችኋቸውን ሰዎች (ራሳችሁንም ጭምር) ይቅር በሉ፡፡ በዝርዝራችሁ ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ሰው ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፣

> *ጌታ ሆይ፣* (የበደላችሁን ሰው ስምን) ለ (የፈጸመባችሁን በደል ዘርዝሩ) በደሎቹ ይቅር እለዋለሁ/ እላታለሁ፡፡

አንድን ሰው ይቅር ስትሉ፣ ያ ሰው እናንተን መበደሉ ተሰምቶት ከሆነ ይቅርታ እንዳደረጋችሁለት መንገሩ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን እንደ በደላችሁ የማያውቅ ከሆነ መንገሩ ፋይዳ ላይኖረው ይችላል፡፡

### *6. ዓመፅ*

አሮጌው ተፈጥሮአችን ለባለሥልጣን መታዘዝን አይወድም፡፡ የራሳችን ጌቶች መሆን እንፈልጋለን፡፡ ግን ይህን የምናደርግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በቀባው ባለሥልጣን ላይ ዐመፅን ማለት ነው፡፡ በሰማይ

በነበረ ጊዜ ዐመፀኝነትና ትዕቢት የዲያብሎስ (የሉሲፈር) ታላላቅ ኃጢአቶቹ ነበሩ። በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር በመሆን መታዘዝ ስላልፈለገ፣ እግዚአብሔር ወደ መሬት ጣለው። አሁንም ሰይጣን ጠላታችን እንደ መሆኑ መጠን፣ እኛ የእርሱ የዐመፅ ተባባሪዎች እንድንሆን ይፈልጋል።

በእግዚአብሔር ፊት ዓመፅ እንደ ምዋርት፣ ትዕቢትም ጣዖትን እንደ ማምለክ ይቆጠራል *(1ኛ ሳሙኤል 15:23)*። ነገር ግን ለጌታው የሚገዛና ጌታውን የሚያስደስት አገልጋይ ልብ እግዚአብሔር ከእኛ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር በእኛ ላይ ሥልጣን ላላቸው እንድንጸልይና እንድንታዘዝ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በሥልጣን ላይ ላሉት እንዳንታዘዝ የሚፈልገው ከትእዛዛቱ አንዱን እንድንጥስ በጠየቁን ጊዜ ብቻ ነው *(የሐዋርያት ሥራ 5:27-29)*።

አሠሪዎች፣ ወላጆች እና ባሎች ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ በመጠቀም ኃጢአት እንድናደርግ ወይም ለእግዚአብሔር ባለን ታማኝነት ላይ እንድንደራደር ይፈትኑናል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ላይ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ልንታዘዝ አይገባም።

የሚከተለውን ዝርዝር ተመልከታችሁ፣ በየትኛው ላይ ታዛዥነታችሁን እንዳላሳያችሁ እግዚአብሔር ይገልጽላችሁ ዘንድ ጸልዩ።

1. *ለእግዚአብሔር መታዘዝ (መገዛት) አለብን (ያዕቆብ 4:7፤ ዳንኤል 9:5-6)*። እግዚአብሔር ክብርና ውዳሴ ሁሉ የሚገባው አምላክ ነው *(ኢሳይያስ 42:8)*። የኢየሱስ ታላቅ ፍላጐቱ የአባቱን ፈቃድ ማድረግ ነበር *(ዮሐንስ 5:30፤ 6:38)*። እኛም ሁልጊዜ ፈቃዱን ለመፈጸም በመሻት እግዚአብሔርን ማስደሰትና ማክበር ይኖርብናል።

2. *ለሕዝባዊ (ለምድራዊ) መንግሥት መገዛት አለብን (ሮሜ 13:1-7፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-4፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2:13-17)*። ለገዢዎቻችንና

ለመንግሥት ስንገዛና ለአገራችን ሕጎች ስንታዘዝ እግዚአብሔር ደስ እንደሚለው በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ተነግሮናል።

3. *ልጆች ለወላጆቻቸው መገዛት አለባቸው (ኤፌሶን 6:1-3)።* ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙአቸው እግዚአብሔር ይፈልጋል።

4. *ሴቶች ለባሎቻቸው መገዛት (መታዘዝ) አለባቸው (1ኛ ጴጥሮስ 3:1-4)።* አንዲት ሴት በምታገባበት ቀን ባሏን ለመታዘዝና ለማክበር ቃል ትገባለች። ይህ ለባሏ ለመገዛት (ለመታዘዝ) የምትገባው ቃል ኪዳን ነው። ስለሆነም ክርስቲያን ሰው ማግባቷ አስፈላጊ ይሆናል። አማኝ ላልሆነ ሰው መገዛት (መታዘዝ) ከባድ ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ሰው እግዚአብሔር የሚፈልገውን አይፈልግም። ይሁንና ከተጋቡ በኋላ ክርስቲያን የሆነች አንዲት ሴት ክርስቲያን ያልሆነ ባሏን ስታከብረውና ስትታዘዝለት በሚመለከትበት ጊዜ እርሱም ወደ እግዚአብሔር ያዘነብል ይሆናል።

5. *ሠራተኞች ለአሠሪዎቻቸው መታዘዝ አለባቸው (ኤፌ. 6:5-8፣ 1ኛ ጴጥ. 2:18-23)።* ሥራ ካለን፣ ለቀጣሪዎቻችን መታዘዝ አለብን። ሥራችንንም ለጌታ እንደምናደርገው በመቁጠር በሙሉ ልብ ማከናወን ይኖርብናል። ክርስቲያን ከማያምን ሰው በተሻለ ሥራውን ሲያከናውን የሚያዩት ሁሉ ጌታን እያገለገለ መሆኑን እንዲያውቁ ክርስቲያን ከማያምን ሰው የተለየ ሊሆን ይገባዋል።

6. *ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች መታዘዝ (መገዛት) አለብን (ዕብራውያን 13:17)።* በላያችን ላይ ባለሥልጣን ስለሚሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ መልካም ባሕሪና ችሎታ ያላቸውን መሪዎች መምረጥ አለብን። ከመረጥናቸው በኋላ ወዲያ ግን ልንታዘዛቸው ይገባል። ቢሆንም ከመምረጣችን በፊት መጸለይና የእግዚአብሔርን ምሪት መሻት ይገባናል። የግል ሕይወታቸውን አጥኑ። በቤታቸው ውስጥ አኗኗራቸው እንዴት ነው? የመሥሪያ ቤት ሕይወታቸውስ? ሰዎች ስለ እነርሱ ምን ይላሉ? ያላቸው መንፈስ የትሕትና ነው፣ ወይስ የትዕቢት?

ታዛገሮች ሳትሆኑ ለቀራችሁባቸው ጊዜያት እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቁ:-

ጌታ ሆይ፣ ------------- ጉዳይ ላይ ዓመፀኛ መሆኔን ተገንዝቤአለሁ:: ይህ ዓመፄን እባክህን ይቅር በለኝ:: ለቃልህ መገዛትንና መታዘዝን እመርጣለሁ::

## *7. ትዕቢት*

ትዕቢት ኃጢአት ነው *(ምሳሌ 8:13፤ 11:2፤ 16:18፣19፤ 29:23)::* ትዕቢት እንዲህ ይላል፣ «በራሴ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ:: የእግዚአብሔርንም ሆነ የማንንም ሰው እርዳታ አልሻም::» በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርነው ሕይወታችን በእርሱ ላይ የተደገፈ እንዲሆን ነው:: ትዕቢት ከእግዚአብሔር ተለይተን ለብቻችን እንድንኖር ያደርጋል:: ሕይወታችን እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባዋል:: ትዕቢት ራስን ከፍ ወደ ማድረግና ወደ ራስ ወዳድነት ይመራል:: ትዕቢት ዲያብሎስ በሰማይ የፈጸመው ኃጢአት ነው:: እርሱ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ማድረግ ፈለገ:: በእግዚአብሔር ስፍራ መሆን ፈለገ::

በሕይወታችሁ ውስጥ የትዕቢት ኃጢአት የተከሰተበት የተለየ ሁኔታ አለ?

*ትዕቢተኛ ከሆንኩ፣ የሚከተሉትን አደርጋለሁ:-*

.... እግዚአብሔር ከሚፈልገው ይልቅ ራሴ የምፈልገውን አደርጋለሁ *(ማቴዎስ 7:21)::*

.... በእግዚአብሔር ላይ ከመደገፍ ይልቅ፣ በራሴ ኃይል ወይም ብርታት ነገሮችን አደርጋለሁ *(ዮሐንስ 15:5፤ ፊልጵስዩስ 4:13)::*

.... ራሴን ከሌሎች ይልቅ የበለጠ አድርጌ እቆጥራለሁ *(ፊልጵስዩስ 2:3)::*

.... ጥፋቴን ለማመን ያስቸግረኛል *(1ኛ ዮሐንስ 1:8፣10)::*

.... ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ለማስደሰት እጥራለሁ *(1ኛ ተሰሎንቄ 4:1)::*

.... ይገባኛል ብዬ የማስበውን እውቅናና ዋጋ ለመቀበል እፈልጋለሁ *(ዮሐንስ 12:43፤ ሉቃስ 14:7-11)::*

*በሕይወታችሁ ውስጥ ያለ ትዕቢትን እግዚአብሔር ይቅር እንዲላችሁ በጸሎት ጠይቁት::*

## *8. የልምድ ኃጢአቶች*

የልምድ *ኃጢአቶችን* ማለትም በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው *(1ኛ ዮሐንስ 3:6-10፤ 5:18)::* አንዳንድ ሰዎች በጣም ይቆጣሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሁልጊዜ ይዋሻሉ፤ ሌሎች ደግሞ የሐሜት ወይም በድብቅ ሆነው ስለ ሌሎች ሰዎች የማንሾካሾክ ልምድ አላቸው:: ሌሎች ደግሞ በየጊዜው ዝሙት ይፈጽማሉ:: እነዚህ ዕለት ተዕለት የምንደጋግማቸው ኃጢአቶች በእስራት ውስጥ እንድንሆን ያደርጉናል:: ስለሆነም ኃጢአቶቹን መፈጸማችንን አምነን በእግዚአብሔር እርዳታ ደግሞ ላለማድረግ ወይም ለመተው ቃል መግባት አለብን::

እነዚህን ነገሮች በማድረጋችን ያዘንን መሆናችንን በቃል ከመግለጽ ይልቅ ድርጊቱን በማቆም በተግባር ማረጋገጥ አለብን:: «በኃጢአታችን ብንናዘዝ፣ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዓመፃ ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው::» የሚለው *የ1ኛ ዮሐንስ 1:9* መተማመኛ ቃል አለን::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ የዘልማድ ኃጢአቶች ተዘርዝረዋል:: *ገላትያ 5:19-21* የተነጋገርንባቸውን ዓይነት ነገሮች ዝርዝር ይዟል::

ከዚህ በታች የታወቁ የዘልማድ ኃጢአቶችና እነዚህን ኃጢአቶች በሚመለከት እንድታውቁ ሊረዷችሁ የሚችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቀርበዋል::

1. *ንግግር* - መዝሙር 19:14፤ 141:3፤ ምሳሌ 10:19፤ 12:18፤ 13:3፤ ማቴዎስ 12:36-37፤ ኤፌ. 4:29
   
   ሀ) *ቁጣ /ትዕግሥት ማጣት* - መዝሙር 37:7-9፤ ምሳሌ 12:18፤ 13:3፤ 14:29፤ 15:18፣28፤ 16:32፤ 19:11፤ 22:24-25፤ 29:11፤

መክብብ 7:8፣9፤ ኤፌ. 4:31-32፤ ቆላ. 3:12-13፤ ያዕቆብ 1:19-20

ለ) *መዋሸት /ማታለል-* መዝሙር 5:6፤ 34:13፤ 119:163፤ 120:2፤ ምሳሌ 6:16-19፤ 12:18-19፣ 22፤ 13:3፣5፤ 15:4፤ 26:28፤ ኤፌ. 4:25፣29

*ሐ) ወሬ* /አሉባልታ /ሐሜት/ ስድብ - *መዝሙር* 101:5፤ ምሳሌ 10:18፤ 11:13፤ 16:28፤ 20:19፤ 26:20፤ ኤፌ. 4:29፣31፤ ቆላ. 3:8-9

*2. ሴሰኝነት /ዝሙት/ የፍትወተ ሥጋ ምኞት* - ኢዮብ 31:1፣9-12፤ ምሳሌ 5፤6:23-26፣32፣33፤ ማቴ. 5:27፣28፤ ሮሜ 13:14፤ 1ኛ ቆሮ. 6:13-20፤ ኤፌ. 5:3፤ ቆላ. 3:5፤ 1ኛ ተሰ. 4:3-8፤ ቲቶ 2:11፣12፤ 1ኛ ጴጥ. 2:11፣12

*3. መጎምጀት* - ዘጸአት 20:17፤ መዝሙር 119:36-37፤ ምሳሌ 15:27፤ መክብብ 5:10-17፤ ማቴ. 6:19-21፤ ፊልጵ. 4:11፣12፤ ቆላ. 3:2፤ 1ኛ ጢሞ. 6:6-10

ራሳችንን ለእግዚአብሔር የጽድቅ መሣሪያዎች አድርገን ማቅረብ እንጂ፣ ሰውነታችንን ለዓመፅ ሥራ ላለማቅረብ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለብን *(ሮሜ 6:12-14)::* ኃጢአት ከእንግዲህ ወዲህ ገዢያችን ስላልሆነ፣ ኃጢአትን አሻፈረኝ ብለን ጽድቅን መምረጥ እንችላለን:: ሰውነታችንን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት ያደረግን ልንሆን ይገባናል *(ሮሜ 12:1)::*

*በሕይወታችሁ ውስጥ ቀንበር መኖሩን ካወቃችሁ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ:: ይቅርታ እንዲያደርግላችሁም ጠይቁት:: በየዕለቱ እነዚህን ሰንሰለቶች መጣል እንድትችሉ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ለምኑ::*

ነፃ ሆነን ለመገኘት በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለብን:: በክርስቶስ ስለ ተሰጠን ማንነት እውነቱን ያለማቋረጥ በማስታወስ፣ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ለብሰን ጸንተን መቆም ይገባናል:: ዕለት በዕለት ራሳችንን ለእግዚአብሔር ልናስገዛና የዲያብሎስን ሽንገላ ልንቃወም ይገባል (ያዕቆብ 4:7)::

የሚከተሉት ነጥቦች ነጻነታችሁን እንደ ጠበቃችሁ እንድትቀጥሉ የሚረዱአችሁ ናቸው:-

1. *ዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት::* ሰይጣንን፣ ኃጢአትንና ፈተናን እንድታሸንፉ ይረዳችሁ ዘንድ ጥቅሶችን በቃል አጥኑ (መዝሙር 119:9-11)::

2. *ዕለታዊ ጸሎት (ማቴዎስ 26:41፤ 1ኛ ተሰ. 5:17፤ ያዕቆብ* 5:16):: ኃጢአታችሁን ትናዘዙና ትተዉት ዘንድ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ ያለውን ኃጢአት እንዲያመለክታችሁ ወደ እርሱ ጸልዩ (1ኛ ዮሐ. 1:9):: እያንዳንዳችን ውጊያውን በየዕለቱ መዋጋት ይኖርብናል *(1ኛ ጢሞ. 6:11፣12፤ 2ኛ ጢሞ. 4:7፣8)::*

3. *ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አዘውትራችሁ ተገናኙ (ዕብ. 3:13፤ 10:23-25)::*

4. *ሊረዷችሁና ሊያበረቷችሁ የሚችሉ ጓደኞችን ምረጡ (መክብብ 4:9-12)::*

5. *«በክርስቶስ የእኔ ማንነት»* የሚለውን በቃላችሁ አጥኑ:: ይህም የሰይጣንን ውሸቶች ለማሸነፍ እውነቱን መጠቀም እንድትችሉ ይረዳችኋል:: መጥፎ አሳቦችንም ለመቃወም የምትችሉበትን ዘዴ ትማሩበታላችሁ *(2ኛ ቆሮ. 10:5፤ ፊልጵ. 4:8-9)::*

## *X. መልካም እርምጃ ተራመዱ፣ በመልካም ሁኔታ በነጻነት ጨርሱ*

ብዙዎቻችን ከክርስቶስ ጋር በሚገባ መራመድ ጀምረናል፣ በሚገባ ለመፈጸምም እንፈልጋለን:: ሩጫውን ለመሮጥና ኢየሱስ የሰጠንን አደራ ለማጠናቀቅ እንፈልጋለን *(የሐዋርያት ሥራ 20:24)::* ግን አንዳንድ ጊዜ ስለምንወድቅ፤ በሚገባ አንፈጽምም::

በጦርነት ላይ ስለሆንን በሚገባ ለመፈጸም ብርታትን መሻት ይገባናል:: በዙሪያችን ያሉ ነገሮች አስቸጋሪዎች ናቸው:: ብዙ

ሕመምና ሥቃይ እንዲሁም ወደ ኋላ እንድንመለስ የሚያደርጉን በርካታ ነገሮች አሉ:: ወደ ፈተና ውስጥ እንድንገባና በኃጢአት እንድንወድቅ፣ ሰይጣንና አጋንንቱ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ናቸው::

ስለዚህ እንዴት አድርገን ነው በድል የምንፈጽመው? *ዕብራውያን 12:1-3* በዚህ ጉዳይ የሚያግዘንን አሳብ ያቀርባል::

*ቁጥር 1፣* እንደ ደመና የከበቡን ብዙ ምስክሮች አሉ ይላል:: እነዚህ መልካም ፍጻሜ የፈጸሙ ሰዎች ምሳሌዎች ናቸው:: በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ አቤል፣ ሔኖክ፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ዮሴፍ እና ሙሴ የተጠቀሱ ሲሆኑ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነ ዳዊትና ጳውሎስ በርካቶች ሌሎችም አሉ:: በዘመናችንም በመልካም ሁኔታ የፈጸሙ ሰዎችን እናውቃለን:: የእነዚህን ሕይወት በምንመለከትበት ጊዜ በመልካም መፈጸም እንደሚቻል እንረዳለን::

*ታዲያ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?*

1. *«ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት ማስወገድ:-* ከእነዚህ ነገሮች ስለ ብዙዎቹ መነጋገራችን ይታወሳል:: ከተመለከትናቸውም መካከል የዚህ ዓለም የኃጢአት ነገሮች፣ ሰይጣናዊ ነገሮች ፣ ጥርጣሬ፣ ፍርሃት፣ መጥፎ አሳቦች፣ ይቅርታ የማያደርግ መንፈስ፣ አለማመን የሚሉት ይገኙበታል:: እነዚህ ነገሮች እኛን የሚያስሩና እድገታችንን የሚገቱ ናቸው::

2. *«በትዕግሥት መሮጥ::»* ልባችንን በእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ማድረግ ይኖርብናል:: ፈቃዱን ለማድረግ መፈለግና እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ብቻ ለመፈጸም መምረጥ ይገባናል:: ኢየሱስ ራሱን ለእኛ የሕይወት መመዘኛ አድርጎ አቅርቦልናል፣ እኛ ያለብን ኑሮውንና ድርጊቱን ማጥናት ነው:: እርሱ ሩጫውን በሚገባ ሮጦ እግዚአብሔር እንዲፈጽም የፈለገውን በሚገባ ፈጽሟል::

*እኛስ እንዴት ነው መሮጥ ያለብን?*

1. *ትኩረታችንን በኢየሱስ ላይ ማድረግ አለብን (ቁ.2)::* ኢየሱስ ምሳሌያችን ስለሆነ፣ እርሱን መመልከትና ከኋላችን ያሉትን ነገሮች መርሳት አለብን *(ፊልጵ. 3:12-14)::* ኢየሱስ ብዙ መከራዎችን

የታገሠው ብዙ ጊዜ ዓይኖቹ በእግዚአብሔር ላይ ስለሆኑ ነው:: በሚሠቃይበት ጊዜ ከፊት ለፊቱ ታላቅ ደስታ እንደሚጠብቀው ያውቅ ነበር:: እኛም በፊት ለፊታችን በመንግሥተ ሰማይ የሚጠብቀን ታላቅ ደስታ አለ:: የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች እንጂ የዓለም ዜጎች አይደለንም:: የምናልፍበትን ሁሉ ኢየሱስ ያውቃል:: ከምንችለው በላይ ምንም ዓይነት ፈተና እንደማይመጣብን እርሱ ቃል ገብቶልናል *(1ኛ ቆሮ. 10:13)::*

2. *«ከኃጢአተኞች በደረሰበት መከራ የጸናውን ማሰብ» (ቁ.3)::* አሳቦቻችን በኢየሱስና በኖረበት የኑሮ ዘይቤ ላይ ያተኩሩ ሲሆኑ፣ እኛም በዚያ መንገድ ለመኖር እንበረታታለን:: ከኢየሱስ ጋር በምንጓዝበት ጊዜ አንዝልም:: ምክንያቱም እርሱ በጕናችን ይጓዛል፣ በትክክለኛውም መንገድ ይመራናል::

*ኑ፣ በክርስቶስ የእኛ የሆነውን ነጻነት እንያዝ::*

# XI. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንድ ጠላታችሁን፣ ወገናችሁንም እወቁ

1. ስለ ሰይጣን የተጻፈውን የመጀመሪያውን ጥቅስ ከተመለከታችሁ በኋላ በአቅጣጫው ደግሞ ስለ እግዚአብሔር የተጻፈውን በመመልከት በሠንጠረዡ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ::

| *የሰይጣን ስም/ ስለ ሰይጣን ዝርዝር መግለጫ* | *የእግዚአብሔር ስም/ ስለ እግዚአብሔር ዝርዝር መግለጫ* |
|---|---|
| ማቴዎስ 3 | ያዕቆብ 1:13 |
| ዮሐ. 8:44 | ዮሐንስ 10:10፤ 14:6 |
| ዮሐንስ 12:31 | 1ኛ ጢሞ. 1:17፤ ራእይ 17:14 |
| ራእይ 12:10 | ሮሜ 8:1-2፣ 33-34 |
| 1ኛ ጴጥ. 5:8 | ዮሐ. 15:14-15 |
| ኤፌ. 6:12 | ዮሐ. 8:12፤ 1ኛ ዮሐ. 1:5 |

2. በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ስለ ሰይጣን ስልት ምን ተማራችሁ?
3. እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ መኖሩ ሰይጣንን እንድትቃወሙት እንዴት ይረዳችኋል? 1ኛ ዮሐ. 4:4፤ 1ኛ ቆሮ. 10:13
4. የእውነት፣ የብርሃን፣ የሕይወት፣ የፍቅር እና የጽድቅ አምላክ ከጎናችን ነው:: እርሱም ድልን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል:: ጠላታችን ዲያብሎስን የምንዋጋበትን ተግባራዊ መመሪያም

ሰጥቶናል:: የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ዓይነት ድርጊቶች ወይም አመለካከቶች እንዲኖሩን ይጠብቁብናል?

ሀ) ኤፌ. 4:27 ________________________________

ለ) ኤፌ. 6:10-20 ________________________________

ሐ) 2ኛ ጢሞ. 2:25-26 ________________________________

መ) ያዕቆብ 3:14-16 ________________________________

ሠ) ያዕቆብ 4:4፣7-10________________________________

ረ) 1ኛ ጴጥ. 5:8-9 ________________________________

5. የሰይጣን ነበልባላማ ፍላፃዎች እንደሚዘንቡባችሁ ሆኖ ይሰማችኋል? የእርሱ ውሸቶች አሳቦቻችሁንና እምነታችሁን እያቃወሱባችሁ ነው? ኢየሱስ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ቃል ተቋቋመው (ማቴ. 4:1-11):: ከዚህ ጥናት ጥቂት ጥቅሶችን መርጣችሁ በቃል አጥኗቸው:: «የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የመንፈስ ሰይፍ» በሰይጣን ፊት ጸንታችሁ እንድትቆሙ ይርዳችሁ::

## XII. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለት

### መጓዝ የሚገባንን ርቀት መጓዝ

*ከፊት ለፊት ያለው አስቸጋሪው መንገድ*

1. ሯጮች፣ መደበኛ መንገደኞች፣ እንዲሁም ተራ ተጓዦች እንኳ ከአንድ መነሻ እስከ መድረሻው ሊገጥሟቸው የሚችሉትን እንቅፋቶች ይገነዘባሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ በመንገድ ላይ ስለ ቀሩ ሯጮች የሕይወት ታሪክ ይነግረናል:: በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሱትን ሯጮችና ብርቱ ሩጫ እንዳይሮጡ እንቅፋት የሆኑባቸውን ነገሮች ለዩ::

| የምንባብ ክፍል | ሯጭ (ሯጮች) | እንቅፋቶች |
|---|---|---|
| መሳ. 3:5-6 | | |
| 1ኛ ነገ. 11:1-3 | | |
| 2ኛ ዜና 16:1-14 | | |
| 2ኛ ዜና 26:16-21 | | |
| ማቴ. 19:16-22 | | |
| ሉቃስ 5:59-62 | | |
| የሐዋ. ሥራ 5:1-11 | | |
| 2ኛ ጢሞ. 4:10 | | |
| 3ኛ ዮሐ. 1:9 | | |

2. ሩጫን በደንብ ስላለመሮጥ የሚከተሉት ጥቅሶች የሚሰጧቸው ሌሎች ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ሀ) ምሳሌ 5:11-14 ______________________

ለ) ሉቃስ 21:34 ______________________

ሐ) ዕብ. 6:12 ______________________

*በሚገባ መሮጥ*

3. አልፎ አልፎ የሚገጥሙአቸውን እንቅፋቶች ተቋቁመው ለእግዚአብሔር ክብር በመልካም የፈጸሙ የወንድና የሴት ምሳሌዎችን መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት ይዟል። እነዚህ ሯጮች በትዕግሥት እንዲጸኑ የረዷቸው አቋሞችና ድርጊቶች ምን ነበሩ?

| የንባብ ክፍል | ሯጭ (ሯጮች) | አቋሞችና/ ድርጊቶች |
|---|---|---|
| ዘፍጥ. 39:5-12፤ 50:15-21 | | |
| ዘዳግ. 34:10፤ ዕብ. 11:24 - 27 | | |
| ኢያሱ 11:15 | | |
| 2ኛ ሳሙ. 12:9፣ 13፤ መዝ. 51:1-4 | | |
| ዳን. 1:8፤ 6:10 | | |
| ሉቃስ 1:38 | | |
| ሮሜ 4:18-21 | | |
| ፊልጵ. 3:12-14 | | |

4. በሚቀጥሉት ጥቅሶች ጠንክሮ ለመሮጥ የሚጠቅሙ ምን ሌሎች መፍትሔዎችን ታገኛላችሁ?

ሀ) ኢዮብ 17:9 ____________________

ለ) መዝሙር 84:5-7 ____________________

ሐ) መክብብ 4:9-12 ____________________

መ) ሉቃስ 8:15 ____________________

ሠ) ሮሜ 5:3-4 ____________________

ረ) 1ኛ ቆሮ. 15:58 ____________________

ሰ) 1ኛ ጢሞ. 4:16 ____________________

ሽ) 2ኛ ጢሞ. 2:3-10 ______________________________

5. በሩጫ መደናቀፍ ማለት ምን እንደ ሆነ ንጉሥ ዳዊት ያውቅ ነበር:: በመዝሙር 37:23-24 ላይ የሰጠን ዋስትና ምንድን ነው?

______________________________________________

*ራሳችሁን ገምግሙ*

6. ወደ ጥያቄ 1 እና 2 ተመለሱ:: ከእነዚህ እንቅፋቶች ውስጥ በቀላሉ የምትጠቁት በየትኞቹ ነው?

7. አሁን ደግሞ ለጥያቄ ቁጥር 3 እና 4 የሰጣችኋቸውን መልሶች ተመልከቱ:: የቀረውን ሩጫችሁን በተሳካ ሁኔታ እንደምትሮጡ የሚያረጋግጡ ምን እርምጃዎችን መውሰድ ትችላላችሁ?

8. ሮሜ 15:5 እግዚአብሔር «የብርታትና የመጽናናት አምላክ» ነው ይላል:: የሚከተሉት ጥቅሶች ኢየሱስ ብርታትን ለመስጠት ስላለው ብቃቱ ወይም ሥልጣኑ ምን ይነግሩናል?

   ሀ) ዕብ. 2:17-18 ______________________________

   ለ) ዕብ. 12:2-3 ______________________________

9. በርትተን ለመሮጥ ዓይኖቻችንን ጽኑ በሆነው በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ አለብን:: ስለ ሩጫችሁ በጸሎት ለእግዚአብሔር ንገሩት:: በሩጫ ላይ ሊያደናቅፏችሁ ስለሚችሉ እንቅፋቶች ተናዘዙ:: እስከ ዘለቄታው ለመሮጥ ብርታት እንዲሰጣችሁ እርሱን ጠይቁ:: ከእናንተ በፊት ስለ ነበሩትና ስለ ሰጣችሁ በርካታ የብርታትና የጽናት ምስክሮች እርሱን አመስግኑ (ዕብ. 12:1):: ከዚያም በጥያቄ ቁጥር 7 መሠረት ስለ ገባችሁት ቃል ኪዳን ለእግዚአብሔር ንገሩትና ለገባችሁት ቃል ኪዳን ታማኞች መሆን እንድትችሉ ብርታት የሚለግስ ጸጋውን ይሰጣችሁ ዘንድ ለምኑት::